MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት
8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
**Tel: (202)-677-0094 Fax:**
**Web: http//www.moreshwegenie.org/**

**ሞወዐድ (ማክሰኞ፣ መጋቢት ፲፫ ቀን፪ሺህ፰ ዓም) ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ (ልዩ ዕትም)**

# ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ- የዘመናዊት ኢትዮጵያ አስተዳደር ቋሚ መሠረት ጣይ ፡-

## *ዝክረ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ከልደት እስከ ሕልፈተ ሕይዎት።*

**መግቢያ፡-**

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ክብር፣ ነፃነት፣ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ማንነት ሲሉ፣ እጃቸውን ለእንግሊዝ ጦር መሪ ጄኔራል ናፒየር ከሚሰጡ ሞትን በመምረጥ ሽጉጣቸውን ጠጥተው ለኢትዮጵያዊነት ዳብሮ መቀጠል የተሰው ሰማዕት ንጉሠ ነገሥት መሆናቸው ዓለም ያወቀውና ያደነቀው አንጸባራቂ የታሪካችን አንዱ አካል ነው። ቴዎድሮስ ከእርሳቸው የነበሩት ንጉሦች መሠረታቸውን ይፋት፣ ሐረርና አዳል ባደረጉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ጋር ባደረጉት ተከታታይ ጦርነቶች፣ ተያይዞም ከግራኝ ጋር በተካሄደው እጅግ አውዳሚ አሥራ አምስት ዓመታት ያስቆጠረ ጦርነት፣ በኋላም የግራኝን እግር በመከተል በተከሰተው የጋላ (ኦሮሞ) ወረራ የሕዝቡ አንድነት ላላቶ፣ የኢኮኖሚ አቅሙ መድቀቅ የተነሳ በተፈጠረው ሁለንተናዊ ድክመት የተከሰተውን የዘመነ መሣፍት አገዛዝ ዘመን የተፈጠሩ የዚያን ወቅት ኅብረተሰብ ልጅ ናቸው። ቴዎድሮስ አገሪቱ በየአካባቢው የጦር አበጋዞች ተሸንሽና፣ የዘውዱ የአንድነት ምልክትነቱና የሥልጣን ምንጭነቱ ጥያቄ ውስጥ ወድቆ ከ70 ዓመታት ላላነሰ በዘለቀው «ዘመነፍዳ» የብላ ተባላ ዘመን፣ በቆራጥነት ታግለው፣ የአገሪቱን አንድነት ትናሣዔ ያበሰሩ ጀግና መሪ መሆናቸው ማንም ሊጠራጠረው ያልቻለ ሥብዕና ባለቤት ናቸው። ለዘመናዊ ኢትዮጵያ አስተዳደር ጽኑ መሠረት የጣሉ፣ ከሁሉም በላይ የዘውዱንና የንጉሠ ነገሥቱን መብትና ሥልጣ መልሶ ተገቢ ቦታውን እንዲይዝ ያደረጉ ራዕየ ሠፊ፤ ብልኅ፣ አስተዋይ፣ ቆራጥና ጀግና ንጉሠ ነገሥት መሆናቸው ይታወቃል።

ይህ ደረቅ ሐቅ ይሁን እንጂ፣ ኢትዮጵያውያን ባለመታደል ይሁን፣ ወይም በእርግማን፣ ወይም በሌሎች በቅጡ በማናውቃቸው ምክንያቶች ለትውልድ ተከታታይነትና ቀጣይነት በሚያገለግሉ መልካም ሥራዎች ላይ መጨመር፣ መልካም የሠሩ ሰዎችን ማሰብና ማሞገስ፣ ባህላችን ባለመሆኑ፣ የዚህ ጀግና መሪ ራዕይ ቀጣይነት አጥቶ፣ እርሳቸው በከፍተኛ መስዋዕትነትና ወደር በሌለው ጀግንነት የገነቡት አንድነት ዛሬ ከ156 ዓመት በኋላ ወደኋላ ተጉዘን በቋንቋ ልዩነት ከዘመነ መሣፍንት በከፋ መልኩ ተከፋፍለን ስንናከስ ማየት ከችግርነቱ አልፎ፣ ባህላችን እየሆነ መምጣቱ ከማሳዘን አልፎ ያሳፍራል ። በዚህ ሁኔታ ከቀጠልን ኢትዮጵያ እንደ አገር፣ ኢትዮጵያዊነት እንደ ዜግነት መታወቂያነት የመቀጠላቸው ሁኔታ ምንም ዓይነት ማስተማመኛ ነገር የለም። ይህ ልዩነት ካለበት ካሁኑ ሁኔታ ሠፍቶ፣ ኢትዮጵያውያን ለመግባባት እንደ አፍሪካ ኅብረት፣ ተመድ ስብሰባዎች አስተርጓሚ የሚያስፈልገን ብቻ ሳይሆን፣ ባንድ አዳራሽ ለመሰብሰብ የምንችልበት ሁኔታ ሩቅ እንደሆነ የልዩነት ጉዞአችን ፍጥነት አመላካች ነው።

ይህ አሳዛኝ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት እንደ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ያሉትን የአንድነትና የኢትዮጵያዊነት ምሳሌ የሆኑ ሰዎችን ሥራዎች በማሰብ ትውልዱ ወደ ዕውነተኛው ኅሊናው ተመልሶ በቴዎድሮስ መንፈስና ራዕይ አገሩን እንዲመለከት የዳግማዊ ቴዎድሮስን ሕይዎትና ሥራዎች ለትውልድ ማስታወስ ጠቃሚነቱ የትውልድን ተከታታይነትና ተያያዥነት ስለሚፈጥር ጥቅሙ ዙሪያ ገባ ነው።

በመሆኑም ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በየዓመቱ በተለያዩ ዝግጅቶች ታስበው እንዲውሉ ስምምነት ካደረገባቸው ቀኖች አንዱ የሆነው፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ክብርና ነፃነት መጠበቅ ሲሉ ሕይዎታቸውን የሰጡበት ሚያዝያ 6 ቀን በዚህ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ ታስቦ ይውላል። በዝግጅቱ ከሚቀርቡት አንዱና ዋናው የዳግማዊ ቴዎድሮስ ታሪክና ለኢትዮጵያ አንድነት ያበረከቱት አስተዋጽዖ ይሆናል።

**ምዕራፍ አንድ፤**

**1 የካሣ ኃይሉ ትውልድና ዕድገት፣**

ካሣ ኃይሉ ከአባታቸው ኃይሉ ወልደጊዮርጊስና ከእናታቸው ከወይዘሮ አትጠገብ ጥር 6 ቀን 1811 ዓም ከጎንደር ከተማ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ ከምትገኘው ዳዋ ቀበሌ ተወዱ። የካቲት 16 ቀን 1811 ዓም በአባ ዐቢየ እግዚእ ቤተክርስቲያን ክርስትና ተነሱ። የክርስትና ስማቸውም ገብረ-ኪዳን ተባለ።( ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም 1996፣ 19)

እንደ ዕድል ሆኖ ካሣ በአባት ፍቅርና እንክብካቤ ለማደግ አልቻሉም። አባታቸው በተወለዱ ባመታቸው ማለትም በ1812 ዓም በሞት ተለዩዋቸው። በመሆኑም በዚያን ጊዜው ለነበረው የመንፈሣዊ ትምህርት ዕድሜ እስኪ ደርሱ ድረስ ያሳደጓቸው እናታቸው ወ/ሮ አትጠገብ ናቸው። ዕድሜአው ለቀለም ቆጠራ ሲደርስ፣ በወቅቱ የደንቢያ ገዥ ወደ ሆኑት አጎታቸው ደጃዝማች ማሩ (ማሩ ቀመስ ደንቢያ የሚባልላቸው) ሂደው ቸንከር ተክለሃይማኖት (ደንቢያ ጎርጎራና ቆላ ድባ መካከል) የመጀመሪያ ደረጃ የመንፈሳዊ ትምህርት ተከታትለዋል። (እንደላይኛው)

ካሣ ትምህርቱን በቸንከር ተክለሃይማኖት በአጎታቸው ደጃዝማች ማሩ ረዳትነት በሚከታተሉበት ወቅት፣ የዘመነ መሣፍንቱ ቁንጮ ራስ ይማም ጉግሣ ነበሩ። ደጃዝማች ማሩ የደንቢያ ገዥነትን የተሾሙት በእኒሁ ራስ ይማም ነው። ሆኖም፣ ደጃዝማች ማሩ በራስ ይማም አገዛዝ ላይ በማመጻቸው፣ አመጸኛው ማሩን ለማስገበርና ለመቅጣት ራስ ይማም ጉግሣ ጦራቸውን ከደብረታቦር አስከትተው ደንቢያ ገቡ። ማሩ የራስ ይማምን ጦር የሚመክት ኃይል የገነቡ ስላልነበሩ ደንቢያ ተወረረ፤ አድባራት ተቃጠሉ፤ አገር ጠፋ፤ መንደሮች ወደ ባድማነት ተለወጡ። ይህ ሁኔታ ካሣ ይማርበት የነበረው የቸንከል ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ከቃጠሎውና ከጥፋቱ ሊታደገው የሚችል አልነበረም። በመሆኑም ደብሩ ተቃጠለ። የደብሩ ካህናት ታረዱ። ከካሣ ጋር ይማሩ የነበሩት 48 ሕፃናት ተማሪዎች በአሳዛኝ ሁኔታ ተጨፈጨፉ። ካሣ ግን በተዓምር ተረፈ። (ገሪማ ታፈረ፣2ኛ ዕትም፣ 1996፣29)

ካሣ፣ በዘመኑ ብዙ ንግርቶች የተነገረለት በመሆኑ ያ እንዲፈጸም የአምላክ ፈቃድ ሆኖለት፤ ከዚህ መዓት በታምር የተረፈ ብቸኛ ሰው ሆነ። በመሆኑም አስተማሪዎቹና ጓደኞቹ በመገደላቸው፣ ቤተክርስቲያኑም በመቃጠሉና በመዘረፉ ትምህርቱን ሊቀጥል አልቻለም። ወደ ወንድሙ ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ፈንጃ ማርያም ሄደ ።(እንደላኛው)

ይህን በገሪማ ታፈረ የቀረበውን መረጃ የሚቃረኑ የተለያዩ ማስረጃዎች አሉ። ከሚቃረኑት ማስረጃዎች አንዱ፣ በአንድርዜይ ባርቲንስኪ እና ዮዓን ማንቴል-ኒየችኩ **«የኢትዮጵያ ታሪክ»** በሚል ርዕስ በውጭ ቋንቋ ተጽፎ፣ በአቶ ዓለማየሁ አበበ ወደ አማርኛ በተተረጎመው መጽሐፍ ገጽ 250 ላይ እንዲህ ይላል።

«ደጃዝማች ማሩ በማኅበረሥላሴ ገዳም ልጆቻቸውን የሚያስተምሩትን መኳንንት ለመበቀል ፈልገው፣ ወደገዳሙ በመሄድ፣ ተማሪዎቹን በጥይት ፈጁ። ካሣ ከእልቂቱ ተርፎ ወደ ቋራ ሄደ።» ይላል። እነዚህ እጅግ የተራራቁ መረጃዎች ናቸው። የቦታ፣ የአድራጊና የተደራጊ ከፍተኛ የሆነ መፋለስ ይታያል። አንደኛው ካሣ በራስ ይማም ሠራዊት ደንቢያ ሲወረር ይማርበት የነበረው ቸንከር ተክለሃይማኖት በዚሁ ሠራዊት መወረሩንና ተማሪዎቹ ሲገደሉ ካሣ በተዓምር መትረፉን ይነግረናል። በአንፃሩ በአቶ ዓለማየሁ የተተረጎመው መጽሐፍ፤ ካሣ ቋራ ማኅበረሥላሴ ገዳም ይማር እንደነበር፣ ገዳሙ በማሩ መወረሩን ይነግረናል። በሌላ በኩል በፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ የተጻፈው **«የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983»** በሚለው ፣ ካሣን ያሳደጉት አጎቱ ደጃዝማች ኃይሉ ክንፉ እንደሆኑ ይገልጻል። ክንፉ ኃይሉ የካሣ ወንድም እንጂ አጎት አይደሉም። ከቦታ፣ ከግዕዝ ዕውቀታቸውና ለታሪኩ ካለቸው ቀረቤታ አንፃር፣ ትክክለኛው የገሪማ ታፈረ ሊሆን እንደሚችል መገመት ስሕትተ አይሆንም።

ደጃዝማች ክንፉ ለካሣ ታላቅ ወንድማቸው ናቸው። በወቅቱ ደንቢያን፣ ቋራን፣ ጭልጋን እስከ መተማ ይገዙ ነበር። በዚህም የተነሳ የሱዳንን ጠረፍ ነቅተው ይጠብቁ የነበሩ የአገሪቱ ደንበር ሁነኛ ዘብ የነበሩ ናቸው። ክንፉ የጎንደርን ምዕራባዊ ዳርቻ ይገዙበት በነበረበት ወቅት ግብፅንና ሱዳንን አንድ አድርጎ ይገዛ የነበረው የኦቶማን ቱርክ ነበር። ቱርክ የኢትዮጵያን ደንበር እያለፈ በተደጋጋሚ በፈጠረው የመስፋፋት ትንኮሳ፣ ደጃዝማች ክንፉ ፊት ለፊት እየገጠሙ ድል በመንሳት ተስፋፊውን ቱርክ እያሳፈሩ የመለሱ ጀግና ሰው እንደነበሩ ይታወቃል።

ይህ የክንፉ የጠረፍ አካባቢዎች ገዥ መሆንና ከቱርክ ጋር በተደጋጋሚ እየገጠሙ ያስመዘገቡት ድል፣ ለካሣ የኋላ ፍላጎት መሳካት ብርቱ መሠረት የጣለ እንደሆነ ይታመናል። ካሣም በነበራቸው ጉብዝናና ሥርዓት አክባሪነት በወንድማቸው ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ዘንድ መወደድንና መፈቀርን አትርፈዋል። ጎበዝና ጀግናን ማን ይጠላል!

ይህ በሁለቱ ወንድማማቾች ማለትም በክንፉና በካሣ መካከል የተመሠረተው ፍቅርና መግባባት በነበረ መልኩ ሊቀጥል የማያስችል ሁኔታ ተፈጠረ። ሁኔታውም ለክንፉ፣ «ልጆችህ በእግርህ አይተኩም፣ አንተን የሚተካው ካሣ ነው» የሚል ንግርት በስፋት መነገር፣ ክንፉ በካሣ ላይ የምቀኝነትና የጠላትነት ስሜት እንዲያድርባቸው አደረገ። ከቅናት አልፎ ክንፉ፣ «ልጆቼ ጋረድ፣ መኮንን፣ ይልማ ቀርተው ፣እንዴት ካሣ ወንድሜ በእኔ ቦታ ይተካል» በማለት በካሣ ላይ ተንኮል ማውጠንጠን ያዙ።

ደጃዝማች ክንፉ ይህን ተንኮል በሚያውጠነጥኑበት ወቅት፣ ካሣን ሊያጠቁ የሚችሉበት አጋጣሚ ተፈጠረ። ሁኔታው እንዲህ ነው። ግብር ቀርቦ ሲበላ፣ እንደ ጥንቱ ሥርዓት ካሣ ለቁርጥ የሚሆን ሥጋ ተሸክሞ ተመጋቢዎቹ እየቆረጡ ይበላሉ። ከተመጋቢዎቹ አንዱ ደጃዝማች ክንፉ ናቸው። ምግቡ እየተባላ ባለበት ሰዓት አደን የሄዱ ሰዎች አውሬ ገድለው ግዳይ ጥለው ሲፎከርና ሲዘፈን ስለነበር፣ ካሣ ሥጋውን እንደያዘ ፊቱን ፉከራና ዘፈን ወደሚሰማበት አቅጣጫ ያዞራል። ክንፉ ሥጋ ሊቆርጡ ቀና ሲሉ ሥጋውን ከፊታቸው ራቅ ብሎ ያጡታል። ይህ ያናድዳቸውና ሥጋ ለመቁረጥ በያዙት ቢለዋ (ካራ) ካሣን ሆዱን ለመውጋት ወረወሩት። ባጋጣሚ ግን የተወረወረው ካራ ከካሣ ሆድ ሳይደርስ ሌላ ቦታ ወደቀ።

ይህ ድርጊት ያሳዘነውና ያበሳጨው ካሣ፣ ሥጋ ማስቆረጡን ትቶ፣ ከምግብ መመገቢያው ቤት ወጥቶ ውጭ ቆዝሞ በቆመበት መሀል፣ ከግብሩ ላይ የነበሩ ሰዎች ስለሁኔታው ሲወያዩ ጆሮው ላይ የውይይቱ ርዕስ ገባ። ይኸውም «ለጥቂት እኮ ነው የተረፈው፣ ወንድሙን ሊገድለው ነበር» ሲል አንደኛው ንግግር ይጀምራል። ሁለተኛው ይቀበልና ምክንያቱ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ያስከትላል። ጥያቄ ተቀባዩም፣ ደጃዝማች ክንፉ በሕዝቡ ውስጥ የሚነገረውን ትንቢት ስለሚያስጨንቃቸው ነው ሲል ይመልሳል። በሕዝቡ ውስጥ የሚነገረው ትንቢት ምንድ ነው ሲል ተከታይ ጥያቄ ያቀርባል። ትንቢቱማ «ልጆችህ በእግርህ አይተኩም፣ የሚተካው ካሣ ነው፣ እያለ አባይ ጠንቋይ ስለሚነግራቸው ቀንተው ነው፤» ይላል። ሌላው ያነሳና፣ « አንተ የተባለው ትንቢት ዕውነት ይመስልሃል?» ሲል ይጠይቀዋል። ተጠያቂውም ይመልስና «አዎ! ከቤተሰቡ ይነገራል፤ ምናልባት ሳይሆን አይቀርም» ይለዋል። (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም 1996፣ 30)

ካሣ ይህን የሀሳብ ልውውጥ ከሰማ በኋላ፣ ሌሊት ወንድማቸውን ደጃዝማች ክንፉን ሳይሰናበት ወደ ጎጃም ተጓዘ ። ጎጃም እንደገባ የወቅቱ ገዥ ለነበሩት ደጃዝማች ጎሹ የጌታ አደረ። በደጃዝማች ጎሹ ቤት ባሳየው ወታደራዊ ችሎታና ታማኝነት የተወደደና የተከበረ ሆነ። በዚህ ጊዜ ካሣ የቤተመንግሥትን ሥነ-ሥርዓትና የአስተዳደር ዘዴን ትምህርት ለመቅሰም ችሏል። የደጃዝማች ማሩን፣ የደጃዝማች ክንፉንና የደጃዝማች ጎሹን የአገዛዝ ዘዴ፣ አንድነትና ልዩነት እንዲያስተውል ረድቶታል።

ካሣ ጎጃም ከደጃዝማች ጎሹ ጋር እንዳለ፣ ወንድሙ ደጃዝማች ክንፉ ያርፋሉ። ካሣ የወንድሙን ሀዘን ከልጆቻቸው ጋር ሆኖ ለመውጣት በ1835ዓም ከጎጃም ወደ ጎንደር ተመልሶ ከመኮንን ክንፉ ጋር ተቀመጠ። ይሁን እንጂ፣ የዚያን ጊዜው የሥልጣን ትግል በሕግ ያልተገዛ በመሆኑ፣ ለሥልጣን የሚፋለሙት በአብዛኛው በወንድማማቾችና በሥጋ ዘመዳሞች መካከል ስለነበር፣ ይህም ባህል ሆኖ በክንፉ ልጆች መካከል የአባታቸውን ግዛት ለመግዛት እኔ እገዛ፣ እኔ እገዛ በማለት ወደ ከረረ ግብግብ ውስጥ ገቡ። ሁለቱ ወንድማማቾች ማለትም መኮንን ክንፉና ይልማ ክንፉ ደንቢያ ውስጥ ጀንዳ ከተባለው ቦታ ጦርነት ገጠሙ። በጦርነቱ ካሣ ከመኮንን ጎን ተሰልፎ ተዋጋ። ድሉ ግን የይልማ ሆነ። መኮንንና ካሣ የይልማ ምርኮኞች ሆኑ።(እንደላይኛው፣31)

ይልማ ክንፉ ምርኮኛውን የአጎቱን ልጅ ካሣ ኃይሉን ሊበቀለው አልፈለገም። በመሆኑም ምሕረት በመስጠት አብሮት እንዲኖር አደረገ። ካሣ ከይልማ ክንፉ ጋር በሚኖርበት ጊዜ አደን ያዘወትር ነበር። በዚህም የተነሳ አንድ ቀን ዝሆን ለማደን ከአቶ ቢተዋ ጋር ወደ ጫቆ ወረደ። ሚታ ደንበት በረሃ ውስጥ ባንድ ቀን ጀንበር ካሣ ሦስት ዝሆኖችን ገደለ። ቢተዋ ለመግደል አልቻለም። የአጋጣሚ፣ የችሎታ ወይም የዕድል አይታወቅም። ይህ ሁኔታ ቢተዋ በካሣ ላይ የምቀኝነት ስሜት አሳደረበት። «እኔ አንድ ሳልገድል እንዴት እሱ ሦስት ይገድላል? በማለት ተበሳጨ። ተበሳጭቶም አልቀረም፤ በምሣ ጊዜ ካሣ አብሮ ግብር እንዳይገባ ከለከለ።» ይህም ቢተዋ በካሣ ላይ ቂም የቋጠረበት እንደሆ ለካሣ መልዕክት አስተላላፊ ሆኖ ታየው። በመሆኑም ግዳዩን አውልቆ ለቢተዋ ጥሎ ከኮበልውኃ ተነስቶ ወደ ቋራ ገሠገሠ።

**2 የካሣ የሽፍትነት ሕይዎት፣**

ካሣ በቢተዋ ቅናት ምክንያት በተፈጠረበት የጠላትነት ስሜት ኮበልውኃን ለቆ ቋራ የገባ ዕለት የሽፍትነት ሕይዎት አንድ ብሎ የጀመረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የክንፉ ልጆች መኮንንና ይልማ ጀንዳ ላይ ካደረጉት ጦርነት በኋላ፣ ታርቀው በሰላም አብረው በመኖር ግዛታቸውን ማስፋት እንዳለባቸው አመኑ። ለዚህ ፍላጎታቸው መሳካትም ጎጃምን በቅድሚያ ማስገበር እዳለባቸው ወሰኑ። በዚህም መሠረት ኃይላቸውን አጠናክረው የጎጃሙን ገዥ ደጃዝማች ብሩ ጎሹን «መሸንቲ» ላይ ጦርነት ገጠሙ። ድሉ ግን የደጃዝማች ብሩ ጎሹ ሆነ። የክንፉ ልጆች የብሩ ምርኮኞች ሆኑ። ካሣ ከቋራ ተመልሰው ከክንፉ ልጆች ጋር ለተወሰነ ጊዜ ተቀምጠው ስለነበር በመሸንቲው ጦርነት ተካፍሎ ነበር። የወንድሙ ልጆች የብሩ ምርኮኛ ሲሆኑ፣ ካሣ ሸሽቶ አለፋ ገተርጊ ተደብቆ ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ወደ ጎጃም ተጉዞ ለደጃዝማች ጎሹ የጌታ አደረ።

ከደጃዝማች ጎሹ ጋር በኖረበት ጊዜ ጎጃምን አጠቃሎ የመግዛት ፍላጎት ያደረበት የጎሹ ልጅ ከአባቱ ጋር ጦርነት ገጠመ። እንጋጣ ላይ በተደረገው የአባትና የልጅ ጦርነት፣ ድሉ የጎሹ ሆነ። በዚህ ጦርነት ካሣ ባሳየው ጀግንነት አንድ ሰው ማርኮ፣ ሁለት ጦር ነቅሎ፣ ፈረሱ ቆስሎ ሲመለስ፣ ለጎሹ በጣለው ግዳይ፣ ፈረስና ጁህ ለምድ ለመሸለም በቅቷል።(እንደላይኛው)

ካሣ በ1835 ከጎጃም ሲመለስ የደንቢያ፣ የእቴጌ መነን ምስለኔ የነበረው ከወንድሙ ልጅ ቤት ወጥቶ ወደ ጎጃም እንዲሄድ ምክንያት የሆነው ቢተዋ ነበር። ካሣ ከቢተዋ ጋር በመኖር ላይ እንዳለ፣ ቢተዋ በአለቆቹ አጥፍተሃል ተብሎ ሲታሰር፣ ካሣ ሸሽቶ ለሁለተኛ ጊዜ የኢትዮጵያን አንድነት ትንሣዔ ሳያረጋግጥ ትጥቁን እንደማያላላ ለራሱ ቃል የገባ ያህል ቆርጦ ቋራ ገባ።

ካሣ ወደ ቋራ በሚጓዙበት ወቅት አለፋ ላይ በገብርየ የሚመሩ 12 ሽፍቶች ተቀላቀሉት። «ከቤት ዶሮ ሲታረድ፣ ከዱር ቆቅ ይያዛል» ዓይነት የሆነለት ካሣ፣ ቋራ እንደገባ፣ ከእቴጌ መነን ጋር ተጣልቶ የሸፈተ ይልማ ወሰን የተባለ ሰው ጋር ተገናኘ። በነዚህ የሰው ኃይል ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ኃይሉን በማጠናከር ላይ ያለው ካሣ፣ በየአካባቢው ከሸፈቱ ሰዎች ጋር ተባብረው የሽፍትነት ሥራቸውን ለመሥራት ውል ይገባሉ። በሽፍቶቹ መሀል የተገባው ውል እንዲህ የሚል ነው። (1) ጠላትን በአንድነት መዋጋት፣ (2) በየአካባቢያቸው ባሉ በሮችና ወንዞች የሚዘረፍን ንብረትና ገንዘብ ዕኩል መካፈል፤ የሚሉ ናቸው።

ይህን ውል የገቡ 70 ያህል ሽፍቶች የዘረፉትን ሀብት በገቡት ቃል መሠረት ሳያካፍሉ ይቀራሉ። ካሣ በውሉ መሠረት የዘረፉትን ንብረት እንዲያካፍሉ መልዕክተኛ ይልካል። ሽፍቶች « ወገኖቹ ገዙን፣ እርሱ ደግሞ በሽፍትነት ሊገዛን ነው፤ እርሱም ባካባቢው ይዝረፍ፤ እኛም በአካባቢያችን እንዝረፍ፤» በማለት ለተላከው መልዕክተኛ መለሱ። በዚህ የተናደደው ካሣ 70ውን ሽፍቶች ጦርነት በመግጠም ድል ነስቶ ሰባቱን በመያዝ ከጉልበታቸው ላይ እንዲቆረጡ አደረጉ።(ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም 1996፣33)

በነዚህ 70 ሽፍቶች ላይ የተጎናጸፈው ድል የወደፊት ጉዞው በኃይልና በጭካኔ የተሞላ እንደሚሆን አመላካች ነው። በሌላ በኩል ካሣ ለወስላታና ለከሃዲ ምረት የለሽ ርምጃ የሚወስድ መሆኑን፣ ወስላታ፣ ውሸታም፣ ፈሪና ቀጣፊ የማይወድ፣ ሐቀኛ፣ ቆራጥ፣ ጀግናና ብልኖችን አክባሪ እንደሆነ ያሳየ ነው። የካሣን ማንነትና ሥብዕና የቀረጸው ይህ የሽፍትነት ዘመኑ መሆኑን ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።

> ***«--ዘላቂ የሆኑት የካሣ ባሕሪያት ቅርጽ የያዙት በዚህ ዘመን ነበር። ከነዚህ ባሕሪያት አንዱ ምቾትና ብልጭልጭ ነገር አለመውደድ ነው። ካሣ ኋላም ቴዎድሮስ፣ የወታደሮቹን ኑሮ የሚጋራ መሪ ነበር። እንደገበሬ አርሶና ዘርቶ እንደወታደር ይዋጋ ነበር። ሌላው ባሕሪው ደግሞ ለፍትሕና ለእኩልነት መቆርቆር ነበር። እንደዝነኛው የእንግሊዝ ሽፍታ ሮቢን ሁድ ካሳም ከነጋዴዎች የዘረፈውን ገንዘብ ለገበሬዎች ማረሻ መግዣ ብሎ ይለግስ ነበር። በኋላ ከፉ መዘዝ ያመጣበትን የቤተክህነትን መሬት ወርሶ ወታደሮቹን ለመቀለብ መሞከሩም የዚሁ የማይላደል ስሜት አንዱ ነጸብራቅ ነው።» (ባሕሩ ዘውዴ፤ 2003፣28)***

**3 የካሣ የትዳር ሕይዎት፣**

ካሣ ከእቴጌ ተዋበች ዓሊ በፊት አቶ እንግዳወርቅ የተባሉ በሽፍትነት የታወቁ ሰው ልጅ ወ/ሮ ገሡሥ እንግዳወረቅ የተባሉትን አግብተው መሸሻ ካሣ እና አልጣሽ ካሣን መውለዳቸው ይታወቃል። በኋላ ላይም ከቤተ መንግሥቱ ጋር የጋብቻ ዝምድና የመሠረቱባትን ተዋበች ዓሊን አግብተዋል። ተዋበች በሞት ስትለያቸው የደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያምን ልጅ እቴጌ ጥሩወርቅን አግብተዋል። ከነዚህ ሌላ በዘመኑ ባህል በርካታ ቅምጦች(ቁባቶች) እንደነበራቸውው የተለያዩ መረጃዎች ያስረዳሉ። ካሣ (ቴዎድሮስ) ከሕግ ሚስታቸው ከጥሩወርቅ ልዑል ዓለማየሁ የተባለውንና በናፒየር ጦር እንግሊዝ አገር ተወስዶ ከዚያው በዘመድ ወገን ልልት የሞተውን መውለዳቸው ይታወቃል። በአጠቃላይ ቴዎድሮስ፤ ራስ መሸሻ፣ ልጅ ኃይሉ፣ ልጅ ተሰማ፣ ልጅ ይማም እና ወ/ሮ አልጣሽ የተባሉ ልጆች ወልደዋል። ሆኖም ቴዎድሮስ ሲነሱ በሰው አዕምሮ ቀድመው የሚመጡት ልጆቻቸው ዓለማየሁ፣ መሸሻና አልጣሽ ናቸው። የዚህም ምክንያቱ ዓለማየሁ ምርኮኛ ሆኖ ተወስዶ በዚያው መሞቱና ታሪኩ ለታሪክ ጸሐፊዎች ቅርብ መሆኑ ነው። መሻሻ በዳግማዊ ምኒልክ ራስ ተብለው፣ በእርሳቸው ዘመን ከነበሩት መኳንንቶች አንዱ መሆናቸውና ልጃቸው ደጃዝማች ካሣ መሸሻ በቀኃሥ ጊዜ በጎንደር ከነበሩት መኳንንቶች አንዱና የበርካታ ስም አስጠሪ ልጆች ወላጅ መሆናቸው ነው። አልጣሽ የዳግማዊ ምኒልክ የመጀመሪያ ሚስት መሆኗ እንደሆነ ይገመታል።

ምዕራፍ ሁለት፣

**4 የካሣ ከሽፍትነት ወደ አካባቢ ኃይልነት እያደገ መምጣትና በራስ ዓሊ አስተዳደር ያሳደረው ሥጋት፣**

ካሣ ወደ ፖለቲካው ማዕከል ማቅናት በጀመሩበት በ1830ዎቹ ኢትዮጵያ አምስት የፖለቲካ ማዕከሎች ነበሩ። አገሪቱ ይኸን ያህል የፖለቲካ ማዕከላት እንዲኖሩ ግድ ያደረገውም፣ አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ የማሳደር ሁለንተናዊ አቅማቸው ውስን በመሆኑ ነው። እነዚህ ማዕከላትም የሚከተሉት ናቸው። (1) ሸዋ፣ (2) ጎንደር፣ (3) ሰሜንና ትግሬ፣ (4) ደቡብ ኢትዮጵያ የወላይታና በአካባቢው ተመሥርተው የነበሩ ንጉሣዊ አገዛዞች፣ (5) ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የአምስቱ የጊቤ ወንዝ ዳርቻ ኪንግ ደምስ ናቸው። ከእነዚህ ተፎካካሪ ኃይሎች ጎን ለጎን በሥራቸው የነበሩ ታናናሽ ባላባታዊ የጦር አበጋዞች በየቀየው ነፍጥ አንግተው መንቀሳስ በገበሬዎና በነጋዴው የማምረትና የማከፋፈል ተግባር ላይ ከፍተኛ ችግር የተፈጠረበት፤ ሰላምና ተንቀሳቅሶ መሥራትን ከአስቸጋሪነት አልፎ የማይታሰብ ያደረገበት ሁኔታ የሰፈነበት የብላ ተባላ ዘመን ነበር። በጦር አበጋዞቹ መካከል አንዱ ሌላውን ለማስገበር፣ ሌላው ላለመገበር በሚከፍቱት ጦርነት አገሪቱ ወደ እርስ በርስ ጦርነትና ብጥብጥ የተለወጠችበትን ሁኔታ ያስከተለ ነበር። መንደሮች ተመዝብረውና ተቃጥለው ወደ ምድረበዳነት ተለውጠዋል። የጦርነቱ ግብ ዘረፋና ማስገበር በመሆኑ፣ ገበሬው መኖሪያውን እየለቀቀ ወደ ተራራዎችና ወራሪው ኃይል አይደርስበትም ተብሎ ወደሚገመተው አካባቢ በመሸሹ መንደሮች ሰው አልባ ሆኑ። በጥቅሉ ከማረስና ከመነገድ ሽፍትነት እንደመከበሪያና ንብረት ማፍሪያ ሆኖ በመታየቱ ሽፍታው የተበራከተበት ዘመን ነበር። ይህ ዘመን ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ፣ ሕግና ሥርዓት አስከብሮ የሚገዛ፣ ጠንካራ ኃይል ሕዝቡ ይፈልግበት የነበረ አጠቃላይ ሁኔታ የሰፈነበት ነበር። ይህም ነባራዊ ሁኔታ ነበር ለካሣ መነሳትና ወደ ፖለቲካ ማዕከሉ እንዲያቀና ምቹ መደላድል የሆነው።

ካሣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከደጃዝማች ክንፉ፣ ከደጃዝማች ጎሹ፣ ከመኮንን ክንፉ እና ይልማ ክንፉ ጋር ሲኖር ከቀሰመው ወታደራዊ ጥበብ በተጨማሪ፣ በራሱ ወሳኝነትና የጦር ሥልት ነዳፊነት በሽፍትነት ዘመኑ ባካበተው ወታደራዊ አመራር፣ ሥልት፣ ቁጥጥርና ክትትል ከደንቢ ምዕራዊ አቅጣጫ እስከ ሱዳን ጠረፍ ያለው አገር ገዥ ለመሆን በቃ። በዚህ ጊዜ «ግንጃር» በተሰኘ የጦር አዛዥ የሚመራ የሱዳን ሠራዊት መተማን ለመውረር በዝግጅት ላይ መሆኑ እንደተሰማ፣ እቴጌ መነን ካሣ ዘምቶ ዳር ድንበሩን እንዲያስከብር ትዕዛዝ ደረሰው። ካሣ የጦር ሰው፣ ግንጃርን ፊት ለፊት በጦርነት ከመግጠም ይልቅ፣ በዲፕሎማሲ ፍላጎትን ማሟላት በሚል ስሌት ግንጃርን በማግባባት ያለጦርነት ወደ መጣበት እንዲመለስ አድርጎ የአገሪቱን ዳር ድንበር አስከበሯል። ከግንጃር ጋር በፈጠረው መግባባትም ከፍተኛ ገጸ በረከትን ሰጠው። ካሣ ከግንጃር የተሰጠውን ገጸ በረከት ለመነን ላከ። መነን ካሣ በፈጸመው ተልዕኮና ባገኘው ድል ተደስተው ሚስቱን ፈትቶ የእርሳቸውን የልጅ ልጅ ተዋበች ዓሊን እንዲያገባ መፍቀዳቸውን ገሪማ ታፈረ ያስረዳሉ።(ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም 1996፤37) ሆኖም ካሣ ይህን የመነን ጥያቄ በዚህ ወቅት አለመቀበሉን ይነግሩናል። የተዋበችንና የካሣን ግንኙነት እነአንድርዜይ ባርትኒስኪ የሚሉን እንዲህ ነው።

ካሣ ወንድይራድን ገጥሞ ድል እንዳደረገው ሞሐመድ ዓሊ ለሁለተኛ ጊዜ እኤኤ 1846 በሙሣ ፓሻ የሚመራ ጦር ወደ ኢትዮጵያ አዘመተ። ጦሩም ጋላባትንና መተማን አልፎ ቋራና ደንቢያ ዘለቀ። ካሣ ይህ ሲሆን ወታደሮቻቸውን በሽምቅ ውጊያ ስልት አደራጅተው ወደ ተራራው አፈገፈጉ። በዚህ ጊዜ እቴጌ መነን፣ ለልጃቸው ሥልጣን ካሣ አስጊ መሆኑን በመገንዘብ፣ ወራሪውን የግብፅን ጦር ከመግጠም ይልቅ፣ ካሣን መግጠም እንዳለባቸው ወሰኑ። ለዚህም በምዕራብ በኩል የግብፅ ጦር ስላለ ካሣ በቀላሉ ሊሸነፍ ይችላል የሚል ግምት ገመቱ። በዚህ ዘመቻ፣ ጦሩን ለማበረታታት የመነን የልጅ ልጅ ተዋበች አብራ እንድትዘምት ተደረገ። ያጋጣሚ፣ ወይም የዕድል ወይም የመረጃ አለመጠናከር ካሣን ለመውጋት የተላከው የመነን ጦር እኤአ መስከረም 1846 ከሙሣ ፓሻ ወታደር ጋር በድንገት ተገናኘ። ሙሣም ሊወጋ የመጣው ካሣን ስለሆነ የርሱ ጦር መስሎት ለጦሩ እንዲያጠቃ ትዕዛዝ ሰጠ። በጦርነቱም የሙሣ ፓሻ ጦር የመነን ጦር ድል ነሳ። ተዋበችም ተማረከች። (ዓለማየሁ አበበ ትርጉም። 2003፣ 250-1)

ይህ ሁኔታ ለካሣ ለወደፊት ጎዞ መቃናት ሁለት ወሣኝ ተግባሮችን ማከናወን እንዳለበት ቁርጠኛ ውሣኔ ላይ እንዲደርስ አደረገው። እነዚህም፡-

> አንደኛ፣ ባገሪቱ ፖለቲካ ከፍተኛ ተደማጭነትን ለማግኘት በሙሣ ፓሻ በሚመራው የግብፅ ሠራዊት ላይ ወታደራዊ ድል መቀዳጀት፣
>
> ሁለተኛ፣ ከቤተ መንግሥቱ ጋር በመጋባት ተደማጭነትን ማትረፍ የሚሉት ናቸው።

በነዚህ ሀሳቦች በመጽናት፣ ካሣ የሙሣ ፓሻን ጦር ገጥሞ በመበታተን በምርኮ የያዛትን ተዋበችን በማስፈታት በሰላም ወደ ጎንደር እንድትሄድ አደረገ። ይህ ለካሣና ለተዋበች መጋባት መሠረት እንደጣለ ይታመናል። ተዋበች ካሣ በጭንቅ ጊዜዋ የደረሰላት ከመሆኑም በላይ በጀግንነቱና በቆራጥነቱ ከልብ እንደ ወደደችው በሕይወቷ የከፈለችው ዋጋ ከማንም በላይ ይናገራል። (እንደላይኛው 251)

ይህ ካሣ በመተማ ዘመቻ በሙሣ ፓሻ ሠራዊት ላይ ያገኘው ድል ከፍተኛ ዝናን አተረፈለት። የዝናው መግነን ለትንሹ ራስ ዓሊ ሥልጣን አስጊ እየሆነ መጣ። በመሆኑም መነን የልጇ ሥልጣን አደጋ ውስጥ ሳይወድቅ፣ የአደጋውን ምንጭ በእንጭጩ መቅጨት እንዳለባቸው በማመን በደጃዝማች ወንድይራድ የሚመራ ጦር ሂዶ ካሣን እንዲወጋና እጁን ይዞ እንዲመጣ ወሰነች። የዚህ ጦር መሪ የሆነው ወንድይራድም «ያን የኮሶ ሻጭ ልጅ እጁን ይዤው እመጣለሁ» የሚል ትዕቢትና ንቀት የተሞላበት ቃሉን ሰጥቶ ዘመተ። የጦርነቱ ገና መጫዎቻ ሜዳም ጉራምባ «ጫቆ ፣የበልውኋ» እንዲሆን ተወስኖ የካሣና የወንድይራድ ጦር ገጠመ። በጦርነቱ ድሉ የካሣ ሆነ። ወንድይራድ ተማርኮ ከካሣ ፊት ቀረበ።

ካሣ ወንድይራድ ወደ ዘመቻው ሲንቀሳቀስ ለመነን የገባውን ቃል ሰምቷልና እንዲህ የሚል አዋጅ አስነገረ። «ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛልና ኮሶ ያለህ እርዳኝ!» አሉ።

ወታደሩም የመሪውን ቃል አክባሪ ነውና በእጁ ያለውን ኮሶ ሰጠ። ከየሰው የተሰበሰበው ኮሶ ተደቁሶ በወፍራሙ እንዲበጠበጥ ተደረገ። ያን ወፍራም ብጥብጥ ኮሶ፣« እናቴ ከገበያ ኮሶ ሳይሸጥላት ቀርቶ እህል ስለታጣ ይህን ኮሶ ተመገብ አሉት፤» (ገሪማ ታፈረ። 2ኛ ዕትም 1996፣ 46)

ደጃዝማች ወንዲራድ፣ «ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ» ሆኖ፣ በወፍራሙ የተበጠበጠውን ኮሶ ደጋግሞ እንዲጠጣ በመገደዱ ለሕልፈተ ሞት በቃ። ይህ ለራስ ዓሊና ለመነን ታላቅ የራስ ምታት ፈጠረ። በመሆኑም የተጠናከረ ጦር በመላክ ካሣን ድል ለመንሳት ሌላ ዝግጅት ተደረገ።

በዝግጅቱም የእቴጌ መነን ፣ የራስ ዓሊ እና የውቤ፣ የፈታውራሪ እንግዳወርቅ ጦር ባንድነት በሹምተንቤን ወልደጊዮርጊስን አዝማችነት ካሣን እንዲወጋ ዝግጅት ተደረገ። ኅዳር 12 ቀን የሁለቱ ተፋላሚ ወገን ጦር «ጣቁሣ ሰቀላ ዋርካ» ላይ ገጠመ። ድሉ ያለጥርጥር የካሣ ሆነ። ከድሉ በኋላ ካሣ ድል የሆነውን የራስ ዓሊን አዝማቾች ተከትሎ የመጣውን ሠራዊት «የወደድክ ተከተለኛ፤ የማትፈቅድ በያገርህ ግባ» ብለው የወጋቸውን ሠራዊት አንዳች ጉዳት ሳያደርሱበት ለቀቁት። (እንደላይኛው፣ 46)

የመነን፣ የራስ ዓሊና የውቤ ጦር በካሣ ጦር ድል ተመታ የሚለው ወሬ እና የካሣ ዝና በስፋት በሕዝቡ ውስጥ ናኘ። ይህ ያበሳጫቸው እቴጌ መነን ራሳቸው ለመዝመት ወሰኑ። በመሆኑም ያላቸውን ሃያ ሺህ ሠራዊት አስከትተው በሰኔ ወር ካሣን ለመግጠም ለዚሁ ጦርነት ወደ ተመረጠው «ጣቁሳ የያሲን» ወደ ተባው ቦታ ዘመቱ። መነን በተለመደ ካሣን ማዋረጃና ማንቋሸሻ ይሆናል ያሉትን «ይህን የፍየል እረኛ፣ ቆለኛ» ወዴት አባቱ ይገባ ይሆን? በማለት ፍራትን ከድፍረት በቀላቀለ ስሜት ተጓዙ። ጦርነቱ በተጀመረ በጥቂት ሰዓት ውስጥ ካሣ እቴጌ መነን ለመያዝ በፋመው ጦርነት ውስጥ ሲገባ፣ የርሱ ወታደር ቀድሞ መነንን ከጭናቸው ላይ በጦር ወግቶ ማርኮ ግዳይ አቀረባቸው። ከሰኔ እስከ ነሐሴ ለሦስት ወራት በዋሻ ውስጥ በእስረኝነት እንዲቀሙጡ ሆነ።

የእናታቸው በጦር ምርኮኛነት ተይዞ ለብዙ ጊዜ መቆየት ያስጨነቃቸው ራስ ዓሊ፣«ከፍርቃ በመለስ እስከ አርማችሆ፣ ከጫጫ በመለስ እስከ ቋራ ፣ ያለውን አገር ግዛ፣ በምትኩ እናቴን ፍታልኝ» የሚል ሽምግልና ለካሣ ላኩ። ካሣም ለዓሊ ምርኮኛዋን እቴጌ መነንን በመፍታት፣ ከላይ የተጠቀሰው አገር ሕጋዊ ገዥ ሆነ። (ገሪማ ታፈረ 2ኛ ዕትም 1996፤ 47—48) በሌላ አባባል የእቴጌ መነን በካሣ መማረክ ለካሣና ለራስ ዓሊ ግንኙነት መንገድ ከፈተ። በዚህም መሠረት ካሣ ተዋበችን በ1840ዓም አገባ። የሁለቱ ጋብቻ ለካሣ ሁለት ጥቅሞችን እንዳስገኘ ይገመታል። አንዱ ከቤተ-መንግሥቱ ጋር በጋብቻ መዛመዱ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከበሬታን እንዲያገኝ ያስችለዋል። ሁለተኛው ተዋበችን ከግብፅ ወታደር ሙሣ ፓሻ እስር ያስለቀቃት በመሆኑ በጀግንነቱ ትወደው ስለነበር ፍፁም ታማኝ ባለቤቱ ሆና ለዘለቄታው ዓላማው መሳካት አጋር ሆናው ዘለቃለች።

በካሣና በራስ ዓሊ የተደረገው ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ የሰላም አየር ባካባቢው እንዲነፍስ ረዳ። ሆኖም፣ የካሣ ኃይል እየጎለበት መሄድ ያሳሰባቸው ራስ ዓሊ ኃይሉን ለመገደብ ፈለጉ። በዚህ ፍላጎታቸው መሠረትም፣ ከጎጃሙ ደጃዝማች ጎሹ ጋር ሆነው ካሣን ለመውጋት አቀዱ። ይህ ደግሞ ለካሣ የተሰወረ አልሆነም። የሁለቱን ጦር ባንድነት መግጠም ድል ማድረግ የሚቻል ያልመሰለው ካሣ፣ ጦሩን አፈግፍጎ ወደ ቋራ ወረደ። የካሣን ቋራ መግባት ያዩት ራስ ዓሊ፣ በደንቢያ ላይ ጎሹን ሹመው ወደ ጎንደር ተመለሱ። (ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 253)

ካሣ የራስ ዓሊንና የደጃዝማች ጎሹን የጋራ ጦር ፊት ለፊት ከመግጠም አፈግፍጎ ወደ ቋራ ከሄደ በኋላ ዓሊን ብቻውን አቁሞ በቀላሉ ድል ለመምታት አጋሮቹን ብሩ ኃይሉንና ጎሹ በየተራ ለመግጠም ፈለገ። በዚህም መሠረት በ1845 ዓም ካሣ ጣና ውስጥ ከምትገኘው «ደቅ» ከምትባለው ደሴት የመሸገውን የሜጫውን ገዥ ብሩ ኃይሉን ለመውጋት ዘመተ። ለዘመቻው መሳካትም ቁጥራቸው አምስት መቶ የሚደርሱ ታንኳዎች አዘጋጅቶው፣ በነርሱ ባሕሩን በማቋረጥ ከደሴቱ የመሸገውን ብሩ ኃይሉን ድል ነስቶ ተመልሷል። ካሣ ብሩ ድል ካደረገ በኋላ፣ በእቴጌ መነን ምርኮ ልዋጭ ባገኘው በደንቢያ ገዥነት በተሾመው ጎሹ ላይ ዘመቻ ለመክፈት ተዘጋጀ። የጦርነቱም ጉራምባ እንደሚሆን ቁርጥ ሆነ።

የ1845ቱ ኅዳር ወር የጉራምባ ጦርነት መነሻ ምክንያቱ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ የካሣ ግዛት የሆነውን ከፍርቃ እስከ መተማ ያለውን ግዛት ጎሹ ከጎጃም ጋር አጣምሮ እንዲገዛ ራስ ዓሊ መስጠታቸው ነው። ካሣም ግዛቴን አሳልፌ አልሰጥም ብሎ፣ በደጃዝማች ጎሹ ከሚመራው የጎጃም ጦር ጋር ገጠመ። ድሉም በጦር ሥልት የበላይነት የነበረው የካሣ ሆነ። በዚህ ጦርነት የካሣ ጦር መሪዎች አንዱ የሆነው ዝነኛው ገለሞ በጦር ጉንጬ ላይ ተገግቶ፣ ጦሩን ሳይነቅል በጥርሱ ይዞ ያዋጋበት ልዩ ትንግርት የታየበት ነበር። (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣ 1996፣ 53)

የጉራምባ ጦርነት በካሣ የበላይነት መጠናቀቅ ለራስ ዓሊ የራስ ምታት፣ የሆድ ቁርጠት ሆነባቸው። ይህንም «ሳይቃጠል በቅጠል» እንዲሉ፣ ከራሳቸውና ከውቤ ጦር የተውጣጣ ባለአምስት ነጋሪት ጦር(ማለትም በአምስት ደጃዝማቾች የሚመራ) በአስቸኳይ እንዲዘምት አዘዙ። በዚህም መሠረት ሚያዝያ 4 ቀን 1845 ዓም ደጃዝማች በለው፣ ደጃዝማች አቤ፣ ደጃዝማች ብሩ እና ደጃዝማች አሊጋዝ አዝማች የሆኑበት ጦርነት፣ ደንቢ ውስጥ «ድርማ ብችኝ» ላይ በአምስቱ ደጃዝማቾች የሚመራው የራስ ዓሊና የካሣ ጦር ገጠመ። ድሉ ምንጊዜም የድል ባለቤት ለሆነ ካሣ ሆነ። ግንቦት 1845 ዓም ካሣ ደብረታቦርን ወሮ አቃጠለ።

በድርማ ብችኝ ጦርነት ከሞቱትና ከተማረኩት የራስ ዓሊና የደጃዝማች ውቤ ጦር መሪዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

(1) ደጃዝማች በለው፣

(2) ደጃዝማች ብሩ አሊጋዝ፣

(3) ደጃዝማች ያለው፣

(4) ደጃዝማች አቤ፣

(5) ደጃዝማች በለጠ፣

(6) አንንት ብሩ፣

(7) ዐባይ ኮርማ፣

(8) አሊጋዝ ብሩ፣

(9) ደጃዝማች ገብሩ መድኃኒዓለም (ገሪማ ታፈረ 2ኛ ዕትም 1996፣ 54)

በዚህ የድርማ ብችኝ ጦርነት ከተማረኩት አንዱ የሆነው ሰቀልቱ እንግዳን ተቆራርጠው እንዲገደሉ ካሣ ወሰኑ። ሰቀልቴ እንግዳ የአሟሟታቸው ወይም የአገዳደላቸውን ሁኔታ እንዳወቁ በድፍረት ለካሣ የሚከተለውን ጥልቅ ሚስጢር ያለው ቃል ተናገሩ። «ጌታዬ እኛ ሊገዙ የመጡ መስሎን ነበር እንጂ፣ የወነዎን ቃርሚያ ሊለቅሙ የመጡ መሆኑ መች ገባን» አሉት። በሰቀልቴው እንግዳ አነጋገር ኅሊናው የተነካውና የአባባሉ ሚስጢር የተረዳው ካሣ፣ ሰቀልቴ እንግዳን ምሕረት በመስጠት አማካሪው እንዲሆኑ አደረገ። ሰቀልቴ እንግዳ ይህን ለማለት የደፈሩት፣ የካሣ ወንድም ደጃዝማች ከንፉ በአገዛዛቸው ዘመን አልገዛም እያሉ ያስቸግሯቸው ስለነበር አንድ እግራቸውን ቆርጠዋቸው ስለነበር ያን በማስታወስ፣«ቃርሚያ ሊለቅሙ ነው ወይ የመጡት» ማለታቸው በወንድማቸው የተፈጸመባቸውን የአካል ቅጣት በማስታወስ ቀሪውን ደግሞ ካሣ ሊያጠናቅቀው ነው ለማለት ነው።( ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣ 1996፣ 55)፣ ከድርማ ብችኝ ጦርነት በኋላ ራስ ዓሊ ኃይላቸውን አሰባስበው ጣና አጠገብ ዳግም ከካሣ ጋር ገጠሙ። ድሉ ግን አሁንም የካሣ ሆነ።(ዓለማየሁ አበበ ፣ትርጉም፣ 2003፣ 254)

**5 የአይሻል ጦርነት የዘመነ መሣፍንት ማክተሚያ፣ የኢትዮጵያ አንድነት ትንሣዔ ማብሰሪያ ፤**

«የጠሉት ይወርሳል፣ የፈሩት ይደርሳል» የሚሉት የአገራችን አባባል እውን ሆኖ፣ እቴጌ መነንና ልጃው ራስ ዓሊ የጠሉትና የፈሩት ባለንግርቱ ካሣ የዘመነ መሣፍንት ማክተሚያ፣ የኢትዮጵያ አንድነት ትንሣዔ ማብሰሪያ ከሆነው የትግል ምዕራፍ መደራሻ ላይ ቆሟል። ራስ ዓሊ  ካሣን በልዩ ልዩ መንገዶች አባብለው፣ በጦር ኃይልም አዋግተው የፍላጎታቸው ተገዥ የማድረጉ ሙከራና ጥረት የሰመረ አልሆነም።  በትንሹ ራስ ዓሊ ሥልጣን ሥር የሚተዳደሩትን የዘመነ መሣፍንት የአካባቢ ገዥዎች ተራ በተራ ድል በማድረግ ከፍተኛ ተሰሚነትና ዝና ያተረፈውን ካሣ በተልዕኮ ሳይሆን፣ ፊት ለፊት የመግጠሙ  የመጨረሻ ዕጣ የራስ ዓሊ ሆነ።  በመሆኑም የቀራቸውን ጦር አሰባስበው፤ ከጎጃምም  አስከትተው ካሣን በራሳቸው የጦር መሪነት ለመግጠም ወሰኑ። የጦርነቱ ቀንና ቦታ ተወሰነ። የጦሩ አውድማ «አይሻል»፣ የግጥሚያው ቀንም ሰኔ **23 /1846** ዓም ሆነ። ጦርነቱ በሁለቱም በኩል የሞት የሽረት ስለነበር ከፍተኛ የሆነ ደም መፋሰስ ሆነ። በሁለቱም ወገን ጀግኖች ወደቁ። የማታ ማታ ድሉ ግን የካሣ ሆነ። ራስ ዓሊ ተከታዮቻቸውን ይዘው  ወደ ንጉሥ ኃይለመለኮት ግዛት አንኮበር ሄዱ። በኋላ ላይም  ወደ ትውልድ አካባቢያቸው የጁ ተመልሰው እስከ ሕይዎት ፍፃሜአቸው ድረስ በዚያው ተደብቀው ኖሩ። የዘመነ መሣፍንቱ የሰሜን ኢትዮጵያ ዋና ተጠሪ ድል ሆኑ። የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ትንሣዔ ማብሰሪያው ደወል ከቅርብ ያስተጋባበት ዕለት ሆነ። የካሣ «የኢትዮጵያ ባል፣ የኢየሩሳም እጮኛ» ራዕይና ሕልም በመጨበጥ መልኩ ፈክቶ የታየበትን አጋጣሚ ፈጠረ። ምክንያቱም የአይሻል ድል ለካሣ ጎጃም፣ ቤጌምድርና ወሎ በቁጥጥራቸው ሥር የሆነበትን አጋጣሚ የፈጠረ ነውና!

ከሁሉም በላይ፣ ይህ ጦርነት ለካሣ ዓላማ መሣካትና በኋላ ላይም ለውድቀቱ ምክንያት የሆኑት የእንግሊዝ ዲፕሎማት በመሆን ከራስ ዓሊ ጋር የነበሩት ፕላውደንና ዮሐንስ ቤል ተማርከው ከካሣ እጅ ገቡ። እነዚህ ሰዎች ለካሣ ዕድገትም ሆነ በኋላ ላይ ለውድቀቱ ምክንያት  መነሻ የሆኑ በመሆኑ፣ ካሣ ሲነሳ ምንጊዜም አብረው ይነሳሉ።

ከአይሻል ድል በኋላ የካሣ ንግርት መፈጸሚያና የሰሜን ኢትዮጵያ ብቸኛ ኃይል ሆኖ ለመውጣት የቀረው፣ ከባምብሎ እስከ ቀይ ባሕር ያለው  አገር ገዥ የሆኑትና ለመንገሥ አቡነ ሰላማ የተሰኙ ጳጳስ ከግብፅ አስመጥተው የንግሥና ቀናቸውን በመጠባበቅ ላይ ያሉት ደጃዝማች ውቤ ናቸው። ካሣ ደጃዝማች ውቤን ከመግጠማቸው በፊት በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የሃይማኖት ልዩነት አስወግደው ቤተክርስቲያኗ የዓላማቸው ደጋፊ ለማድረግ ፈለጉ። ከፊታቸው የሚጠብቋቸውን ውቤንና ኃይለመለኮትን ድል ለማድረግም ሆነ፣ የሕዝቡን አንድነት አስተባብሮ ብቸኛ የሥልጣን ባለቤት ለመሆን ካሣ ላቀደው ታላቅ ዓላማ፣ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሚና እንደምትጫወት ግንዛቤ አገኝቷል።

**ምዕራፍ ሦስት፤**

**6 የካሣና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ግንኙነት፡-**

ደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያም የመንገሥ ፍላጎት ስለነባራቸው፣ አቡነ ሰላማ ሣልሳዊ የተሰኙ ጳጳስ ከግብፅ እስክንድርያ አስመጥተው ከጎናቸው አስቀምጠዋል። እኒህ አቡን ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የበላይ፣ የሕዝቡ መንፈሣዊ አባት ናቸው። የሚናገሩት ያላዳች ጥርጣሬ ትክክል ነው ብሎ አማኙ የሚቀበላቸው ናቸው። ይህን ውቤም ሆኑ ካሣ በሚገባ ያውቃሉ። በመሆኑም ደጃዝማች ውቤ፣ የንግሥና ቀናቸው ሲደርስ ፣በአባ ሰላማ ተቀብቶ ለመንገሥ ከግቢያቸው ሳይጠፉ እንዲቀመጡ አድርገዋል። በሌላ አባባል የጠበቀ ግንኙነት መሥርተዋል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የበላይ ኃላፊዎች፣ በታላላቆቹ መሣፍንት መካከል በሚደረገው ወሣኝ የሥልጣን ትግል አንዳቸውም ሊጠቀሙበት የሞከረ የለም። የቤተክርስቲያኒቱ ቁንጮ ከመሀል ሆኖ፣ በትግሉ ውስጥ የማሸነፍ አጋጣሚው ከፍ ያለ የሚመስለውን፣ ማለትም አንደኛ፣ የቤተክርስቲያኗን መብት በሚገባ ያስጠብቃል የሚለውን፣ ሁለተኛ፣ አቡኑ በመንግሥት ጉዳዮች ውስጥ ተደማጭነት እንዲኖረው ያደርጋል ብሎ የሚያስበውን የሥልጣን ተፎካካሪ በመደገፍ የራሱን ፍላጎት የሚያራምድ ነው።

በዚህም የተነሳ፣ አቡነ ሰላማ ወደ ተለያዩ የሥልጣን ተሻሚዎች በመሄድ ጠባቸውን ትተው ሁሉንም ችግሮቻቸውን በዕርቅ እንዲፈቱ የማግባባት ሥራ ይሠሩ ነበር። በዚህ ሂደት፣ የሥልጣን ተሻሚዎቹ ወደ ዕርቅ እንደማይመጡ ለመገንዘብ በመቻላቸው፣ በነበረው የሥልጣን ትግል የማሸነፍ ዕድሉ ከፍተኛ የሆነው የካሣ እንደሚሆን ተረድተዋል። ስለሆነም የቤተክርስቲያኒቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር ላነገቡት ዓላማ መሳካት ከካሣ ጋር መደራደር እንዳለባቸው በማመን ድርድር ማድረግን ሥራየ ብለው ያዙ።

ካሣም በበኩሉ፣ የሚችለውን ሁሉ አድርጎ ቤተክርስቲያኗን ከጎኑ ማሰለፍ ለዓላማው ስምረት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተረድቷል። ይህም በመሆኑ፣ ካሣ ለቀጣይቱ ኢትዮጵያ የሃይማኖት አንድ መሆን ከሚሰጠው ዘላቂ ጥቅም ባሻገር፣ አገሪቱን አንድ ለማድረግ ላቀደው ዓላማ ማስፈጸሚያ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው በመረዳቱ አቡነ፣ ሰላማ ያቀረቡለትን ሀሳብ የተቀበለው በደስታ ነው። ቤተክርስቲያኒቱ አገሪቱን አንድ በማድረጉ ሂደት የሚኖራትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ሕዝቡ በእምነት መከፋፈሉ ማቆም እንዳለበት ቁርጥ ውሳኔ አድርጓል። (ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 255-6)

በዚህ ሁለቱም ተስማምተዋል። ስምምነቱ የፀና እንዲሆንም አቡነ ሰላማ የሚከተሉት ተፈጻሚ እንዲሆኑላቸው ይፈልጋሉ። እነዚህም፡- **አንደኛ፣** ካሣ አቡኑ የሚከተሉትን የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት እንዲከተል፤

**ሁለተኛ፣** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ ያሉትን የእምነት ስብስቦች እንዲያወግዝ የሚሉ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ለካሣ ተስማምተውታል። በዚህ የካሣና የአቡነ ሰላማ ስምምነት መሠረት፣ እኤአ ሐምሌ 15 ቀን 1854(1847ዓም) ካሣ ሁሉም ኢትዮጵያውያን አንድ ዓይነት እምንነት እንዲከተሉ የሚያስገድድ ትዕዛዝ አወጣ። ይህን የማይቀበል በሞት እንደሚቀጣ አሳወቀ። (ዓለማየሁ አበበ ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 256)

ይህን ትዕዛዝ ተከትሎ በአቡነ ሰላማ ግፊት ካሣ በካቶሊክ ካህናትና በእምነቱ ተከታዮች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ጀመሩ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አብነ ሰላማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሁለተኛ ሰው የደብረ ሊባኖሱ እጨጌ ነው በማለት ውሣኔ ሰጡ። አቡኑ ይህን ሲያደርጉ ከእጨጌው ጋር አንድ ዓይነት ሃይማኖት የሚከተሉ አልነበሩም። ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት፣ ካሣ የሸዋውን ኃይለመለኮትን የፖለቲካ ጨዋታ ለመሥራት በማሰብ እንደሆነ ይታመናል። እኤአ 1840 የደብረሊባኖሱ እጨጌ የሚከተለው «የፀጋ» ሃይማኖት የሸዋ ብሔራዊ (ኦፊሴላዊ) ሃይማኖት ሆኖ ታውጇል። ካሣ የሚደግፉት ሃይማኖት «ካራ» ወይም ተዋሕዶ እምነት ነው።

**7 የቴዎድሮስና የቤተ-ክህነት ውዝግብ፥**

ቴዎድሮስ ደጃዝማች ውቤን ድል አድርገው ደረስጌ ማርያም የንግሥና ሥርዓታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ፣ ጎንደር መጥተው የንግሥና በዓላቸውን በፋሲል መናገሻ ለማክበር ጎንደር ገቡ። ሆኖም ማንን እናንግሥ? እያሉ በዘውዱ ላይ ተሰሚነት አለን ብለው የሚያምኑት ካህናት የቴዎድሮስን የትውልድ ሐረግ ከምኒልክ የሚስብ መሆን አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ጥያቄ አቀረቡ። አያይዘውም «መንገሥ የሚችለው ከነገሥታት የሚወለድ ነው፤ እርሰዎን የማን ልጅ ብለን እናንግሥ?፣ በቅድሚያ የማን ልጅ እንደሆኑ እንወቅ ፤ ንግሥናው የሚገባዎ ከሆነ እንቀበላለን፤ በኃይል የሚነግሡ ከሆነ ከደረስጌ ይልቅ ጎንደር በሆነ ነበር? ካለቦታው ከነገሡ በኋላ ለምን ይጠይቁናል? የሚል ጥያቄዎችን በማቅረብ ካሕናቱ ክርክር ከፈቱ። (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም ፣1996፣ 78-79)

ለቀረበው ክርክር ዕልባት ለመስጠት ጉዳዩ በጉባዔ እንዲታይ ተወሰነ። ለጉባዔው ቴዎድሮስን ወክለው የቀረቡት ተከራካሪ አንጋሹ አቡነ ሰላማ ሆኑ። አቡነ ሰላም ለጉባኤው የሚከተለውን የመከራከሪያ ነጥብ አቀረቡ። « እናንተ (ካህናቱ) እያላችሁ ያላችሁት ከሰሎሞን ግንድ አትወለድምና ዘውድ ለአንተ አይገባህም ነው የምትሉት። ለመሆኑ የነገሥታት አባት የምትሏቸው አበው የሰው ምንጭ አዳም አይደለም ወይ?» ሲሉ የፍጥረት ጥያቄ አቀረቡ። ለዚህ ጥያቄ ካህናቱ የሚያስተባብሉበት ሃይማኖታዊና ሥነ-ፍጥረታዊ ማስረጃ ስለሌላቸው መልሳቸው አዎ ሆነ። እንግዳውማ ቴዎድሮስ ከአዳም የሚወለድ መሆኑን ከተቀበልን፣ የዘውዱ ባለቤቶችም የአዳም ልጆች መሆናቸው ከታመነ፣ ዘውድ የአባቶቹ ነውና ቴዎድሮስ ሊነግሥ ይገባል » በማለት አስረዱ።(እንደላይኛው)

ሆኖም ካህናቱ በቀረበው አመክኖአዊና የሰውን ዘር ምንጭ መነሻ ያደረገ የመፋረጃ ሀሳብ ሊቀበሉ ባለመቻላቸው ክርክሩ የከረረ ሆነ። በክርክሩ መክረርና ካህናቱ ለቴዎድሮስ ንግሥና ዕውቅና ለመስጠት በጎ አዝማሚያ አለማሳየት የተነሳ፣ ቴዎድሮስ የሚከተለውን ርምጃ ወሰዱ።

(1) የካህናቱ መተዳደሪያ «ሪም» የተሰኘ የመሬት ሥሪት መሆኑን ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው፣« ሰማይ በጨረቃ፣ ምድር በጭቃ ነውና ከደሀየ ደጃፍ ማንም ሰው እንዳይደርስ፤ የመሬቱ ባለቤቶች እኔና ድሀየ ነን፤ ከዛሬ ጀምሮ መሬት በእጄ » ብለው አዋጅ አስነገሩ።

(2) አያይዘውም እስካሁን ድረስ በቤተክርስቲያኒቱ ቋሚ ሥርዓት ሆኖ በማገልገል ላይ ያለውን የቤተክርስቲያን አገልግሎት በሁለት ቄስና በሦስት ዲያቆን እንዲሆን ቁርጥ ያለ ውሳኔ ሰጡ። ከዚህ ውጭ ያለው በሌሎች የልማት ሥራዎች እንዲሠማራ ደንብ አወጡ።

(3) ካህናት ወደ ንጉሡ ሲቀርቡ ጥምጣማቸውን እንዲያወልቁ አዋጅ አስነገሩ። ካህናቱም « እኛም ዘውድ በእጃችን ብለው» በአመጹ ገፉበት። ካህናቱ የቴዎድሮስን መንገሥ አንቀበልም ብለው የወሰዱት አቋምና ቴዎድሮስም ንግሥናየን ካልተቀበላችሁና ካላወቃችሁ ብለው የወሰዱዋቸው ርምጃዎች ለብዙ ሰው ሕይዎት መጥፋት እና ለቴዎድሮስ አመራር ከፍተኛ መሰናልክ የፈጠረ መሆኑ ቢታወቅም፣ ቴዎድሮስ የፈለጉትን ከማድረግ ያገዳቸው አልሆንም። የቴዎድሮስ ሀሳብ መሬት የያዘ በመሆኑ ለዛሬው ትውልድም እያገለገለ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ቴዎድሮስ የሰውን ሀሳብ ተጋፊ ሳይሆኑ አድማጭ ስለነበሩ፣ በ1849 ዓም ላይ የጎንደር ካህናት ከንጉሡ ዘንድ ሲቀርቡ ጥምጣማቸውን የመፍታቱ ጉዳይ እንዲነሳላቸው ጥያቄ አቀረቡ። ካህናቱ ጥምጣማችን ክብራችን ነውና ወደ ንጉሡ ስንቀርብ እንዳንፈታ ይደረግ? የሚል ጥያቄ አቀረቡ። ቴዎድሮስም ጥያቄውን ካዳመጡ በኋላ፣«እናንተ ቤተመቅደስ ትስገቡ ጥምጣማችሁን የምትፈቱት ለምንድነው? ብለው ጥያቄ አቅራቢዎቹን ጠየቁ። ተጠያቂዎቹም «ታቦቱ እግዚአብሔር ያደረበት ስለሆነ ለርሱ ክብር ነው» የሚል መልስ ሰጡዋቸው። ቴዎድሮስም አስከትለው፣ « በእኔ ላይ እግዚአብሔር አላደረም ወይ? እግዚአብሔር በእኔ ላይ አድሮ አይደለም ወይ አገሩን ሁሉ የምገዛው?» ሲሉዋቸው ካህናቱ ባንድ ድምፅ አዎን፤ የሚል መልስ ሰጡ። እታዲያ በዚህ ከተስማማን ለምን አዋጅ አንሳ ትሉኛላችሁ? ካሉ በኋላ ፣«እኔ ሥርዓት ለማስተማር ብዬ እንጂ፣ ብትጠመጥሙ ችግሬ አይደለም በማለት ከንጉሡ ዘንድ ሲቀርቡ ጥምጥማቸውን እንደጠመጠሙ መቅረብ የሚችሉ መሆናቸውን በመፍቀድ ላቀረቡት ጥያቄ አዎንታዊ መልስ በመስጠት ቀሳውስቱን አሰናብተዋል። (እንደላይኛው፤ 79-80)

ከዚህ የካህናቱና የቴዎድሮስ ውይይት ጋር ተያይዞ፣ ካህናቱ የሪም መሬታቸው እንዲመለስላቸው ጠየቁ። የሪም መሬት ማለት ከዲያቆን እስከ መሪጌታ ላሉት የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ማደሪያ የሆነ መሬት ነው። ቴዎድሮስ ለቀረበላቸው የሪም መሬት የመመለስ ጥያቄ፣ « እኔና ሠራዊቱ ምን እንብላ? ካህናቱ እኩሌታውን የመስቀል መሬት፣ እኩሌታውን እሪም፣ ጉዳም፣ እያላችሁ ይዛችኋል፤» ብለው ለካህናቱ ጥያቄውን በጥያቄ መለሱ። ከካህናቱ አንዱ ተነስቶ ቴዎድሮስ ላቀረቡት የእርሳቸውና የሠራዊታቸው ማደሪያን በተመለከተ እንዲህ የሚል መልስ ሰጠ።

- «አራት ወር ጎንደር ተቀምጠው፣ አርማጭሆን፣ ጠገዴን፣ ወልቃይትን፣ ሰሜንን፣ ትግሬን ያስገብሩ፤
- «አራት ወር አሪንጎ ተቀምጠው፣ ቤጌምድርን፣ ላስታን፣ የጁን፣ ወረሂመኖንን ያስገብሩ፤
- «አራት ወር ይባባ ተቀምጠው፣ ሜጫን፣ አገውን፣ ዳሞትን፣ ጎጃምን ያስገብሩ፤» አላቸው።

ካህኑ ለእርሳቸውና ለሠራዊታቸው መተዳደሪያ እንዲሆን ላቀረበው ሀሳብ፤ ቴዎድሮስ እንዲህ በማለት መለሱለት። «ቆማጣ ቆመጥማጣ እኔ ብቻየን በሆንኩልሽ ጊዜ እንደ ዐፄ ኢዮአስ በኻሽ አንቀሽ ለመግደል ነው?» ሲሉ በቁጣ የቀረበውን ሀሳብ አጣጣሉት።

ሌላው ደብተራ በበኩሉ እንዲህ አላቸው፤« ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ብሎ ቅዱስ ዳዊት ተናግሯል፤» ሲላቸው፣ ፈጥነው፣ «እንግዲያውስ ሌዊን ለክህነት፣ ይሁዳን ለመንግሥት ሲመርጥ፣ ከአሥራት በኩራት በቀር ምን አላችሁ?» ብለው ሞገቱት። እነዚህ የቴዎድሮስ የአቋም መልሶች በሥነ-መንግሥትና በሥነመለኮት ያላቸው ዕውቀት የጠለቀ መሆኑን ከማሳየታቸውም በላይ፣ ንጉሥ ሆነው ከዜጎች ጋር በዕኩልነት ግራ ቀኝ ቆመው መከራከራቸው በሰዎች ዕኩልነትና በሀሳብ የበላይነት የሚያምኑ መሆናቸውን ያሳያል።

ሆኖም በቴዎድሮስና በካህናቱ መካከል የተነሳው ክርክር ቀጥሎ ጃንተከል ከዋርካው ሥር ኢየሱስ ክርስቶስን ዳኛቸው አድርገው ወንጌሉን ከዙፋን ላይ አኑረው ሲከራከሩ፣«ፍትሐ ነገሥት ከቤተ መቅደስ የገባ አይወጣም» የሚል ቃል አለ በማለት ተከራከሩ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ፤ «አንድ ሺህ አንባቢ፣ አንድ ሺህ ተርጓሚ » ብለው ተቆጥተው «የወደዳችሁትን በአልጋው አስቀምጡ፣ እኔም እንደመሳፍንቱ እየዞርኩ እበላለሁ፤» ብለው ከጉባዔው ሲነሱ ሠራዊቱ እርሳቸውን ተከትሎ ተነሳ። የንጉሡ አነሳስ የቁጣና የእልክ በመሆኑ በጎንደር ካህናት ላይ ፍርሃትና ድንጋጤን ፈጠረ። ሁለቱ የያዙት አቋም የተራራቀ ጠርዝ መሆን ለዘለቄታው ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በመገንዘብ ይመስላል፣ ቴዎድሮስ ጉባዔውን ትተው ከመሄድ ተቆጥበው ወደ ውይይቱ በመግባት በተፈጠረው ሰጥቶ የመቀበል ዘዴ ሁሉቱም ከያዙት ጫፍ ወደ መሀል መንገድ ገቡ። በዚህም መሠተረት « እሪም ባለበት አገር ፈሰስና ዳኝነት ለንጉሡ እንዲሆን» ተስማምተው በካህናቱና በቴዎድሮስ መካከል የነበረው የጥቅምና የሙብት ውዝግብ ለጊዜው ዕልባት አገኘ። ካህናቱ ግን ጊዜ የሚጠብቁ እንጂ፣ በእርቁ የተደሰቱ አልነበሩም። በመሆኑም በኋላ ላይ በቴዎድሮስ ላይ ላመጹ የአካባቢ ባላባቶችና ካህናቱ ያበረከቱት ድጋፍ ለውድቀታቸው መፋጠን የጎላ ድርሻ እንዳበረከተ ይታወቃል። (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም 1996፣ 80-81)

ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር ያደረጉት ክርክርና ውይይት አመራራቸው በሕግ የሚገዛ፣ በአመክንዮ የተገራ፣ ጥልቅ መንፈሳዊና ዓለማዊ ዕውቀት የጨበጡ፣ የሕዝብን ድምፅ የሚያዳምጡ እንደነበሩ መገንዘብ ይቻላል።

**ምዕራፍ አራት፥**

**8 የዘውዱ ክብርና ሥልጣን ወደ ነበረበት መመለስና የኢትዮጵያ አንድነት ትንሣዔ መበሰር፥**

**8.1 የደርስጌ ማርያም የካሣና የደጃዝማች ውቤ ጦርነትና ውጤቱ፣**

ካሣ ትንሹ ራስ ዓሊን ሰኔ 23 ቀን 1846 ዓም አይሻል ላይ ድል ካደረጉ በኋላ ፊታቸውን ያዞሩት ወደ ስሜን ነው። ደጃዝማች ውቤ ከራስ ወልደሩፋኤል ጀምሮ በተከታታይ ስሜን የገዛው ባላባታዊ ተከታይ ከመሆናቸውም በላይ፣ ቅድመ አያቶቻቸውና አባቶቻቸው ያልገዙትን ከተከዜ እስከ ቀይ ባሕር ያለውን የዛሬውን ትግራይና ኤርትራን (ባሕረ ነጋሽ ወይም ምድሪ ባሕሪን) አጠቃለው ለረጅም ጊዜ የገዙ በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ ሀብት፣ ሠራዊት፣ የአስተዳደርና የአመራር ጥበብ ያካበቱ መሆናቸው ይታወቃል። ከሁሉም በላይ የመንገሥ ፍላጎት ያላቸውና ይህን ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሁሉም ዘርፍ ሠፊ ዝግጅት ያደረጉ ናቸው። ይህ ሁለንተናዊ ዝግጅት ለካሣ የተሰወረ አልነበረም።

በመሆኑም ከውቤ ጋር የሚደረገው ጦርነት ለካሣ ፍላጎት መሟላት ወይም አለመሟላት የመጨረሻው ምዕራፍ በመሆኑ በሁሉም አቅጣጫ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ዝግጅትና እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለበት ካሣ ተገንዝቧል። በዚህ መሠረት ስለጦርነቱ አሰላለፍና ዝግጅት፣ አይሻል ጦርነት ላይ ከራስ ዓሊ የተማረኩት እንግሊዝያውያን፣ በተለይም የካሣ የልብ ወዳጅ የሆነው ቤል የምክር አገልግሎት ሰጥቷል። የሁለቱ ኃያላንና የወዲፊቷን ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ወሳኝ ለመሆን ላለቸው ዓላማ መሳካት ወሳኝ ድርሻ የሚኖረው የጦርነት ቀን የካቲት 5 ቀን 1847 ዓም እንዲሆን ተወሰነ።

ቤል(ዮሐንስ) ከውቤ ጋር ለሚደረገው ጦርነት የካሣ የጦር አሰላለፍ እንደሚከተለው እንዲሆን ምክሩን ሰጠ። ምክሩንም ሲሰጥ እንዲህ በማለት ጀመረ።« የዛሬው ጦርነት ትልቁን የዕድገት ተራራ የምንወጣበት ነው።» ይልና የጦሩ አሰላለፍ እንዲህ ይሁን በማለት አስረዳ።

1 « መሳፍንቱና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ወደፊት፤

2 በሁለተኛው ረድፍ ወይም መሥመር በሥልጣንና በሙብት ከመሣፍንቶቹና ከከፍተኛ ባለሥልጣኖቹ የሚከተሉት፣

3 በሦስተኛው መሥመር ጌታዬ (ካሣ) እና ታማኝ አሽከሮቻዎን ይዘው ይሰለፉ ፡» ሲል የጦሩን የውጊያ አሰላለፍ ገለጸ።

ለዚህ የቤል ምክር ካሣ የሰጡት አስተያየት እንዲህ የሚል ነበር።

1. አንደኛ «አንተ(ቤል) እንደምትለው በአንደኛና በሁለተኛ መሥመር እንዲሠለፉ የመደብካቸው ታላላቅ መሣፍንትና ሹማምንት የእኛን መውደቅና እኛ ስንደመሰስ የእኛን ቦታ ለመያዝ የሚመኙ ናቸው። ስለዚህ በብዙ መጠራጠርና ምኞት የሚዋኙ ስለሆነ፣ ለእኛ ክብር ሲሉ ጠንክረው ይዋጋሉ ማለት ዘበት ነው።»
2. «በሦስተኛ የመደብካቸው ታማኞቻችን ደግሞ፣ እኛን አምነው ነው የሚኖሩት፤ እኛ ብንወድቅ ውድቀታቸው፣ ብናጠቃ ማጥቃታቸው፣ መሆኑን ስለሚረዱ ጠንክረው እንደሚዋጉ የተረጋገጠ ነው። አሁን በዚህ ጦርነት ብንወድቅ መውደቃቸውን፣ ብናጠቃ የድል በር መክፈታችን ስለሆነ የቀረበልንን የጦር ገፈታ ግንባር ቀደም ሆነን የምንቀምሰው እኔና አሽከሮቼ መሆን አለብን። ይህን በማስታዎሻህ ጻፍ!» (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም ፣ 1996፣ 62)

ካሣ እንዲህ በማለት የቤልን የጦርነት አሰላለፍ ከመሠረቱ ቀየሩት። የካሣ የጦርነት ሥልት አዋቂነታቸው የሚመነጨው የተዋጊውን ማንነትና ሥነልቦና በቅጡ የተረዱ መሆኑ ነው። የድላቸው መሠረትም ራሳቸውን የየጦርነቱ ግንባር ቀደም ተሰላፊ ማድረጋቸው ነው። በዚህም መሠረት ደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያምን ለመግጠም የወጣው ወታደራዊ ዕቅድና እንቅስቃሴ በካሣ እና በታማኝ ሰዎቻቸው ግንባር ቀደም ተሰላፊነት ተጀመረ። በጦርነቱ ብዙ ሰዎች ተሰው። ድሉ ግን የካሣ ሆነ።

ካሣ ደጃዝማች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ ጊዜ ሳያባክኑ እዚያው ደረስጌ ማርያም፣ ውቤ ለንግሥና ባሠሯት ቤተክርስቲያንና ከግብጽ ባስመጧቸው አቡነ ሰላማ ተቀብተው ዘውድ ጭነው ነገሡ። የንግሥናቸውን ስምም፣ ወደ ስሜን ለጦርነት ሲጓዙ ለወታደሮቻቸው «ስሜን ስሜን እነግርሃለሁ፣ ተከተለኝ» ሲሉ ባስታወቁት መሠረት፣ ስማቸው « ቴዎድሮስ » መሆኑን አሳወቁ። ይህም ስም የመረጡበት መሠረታዊ ምክንያትም ቀደም ሲል «ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሲይዝ፣ በኢትዮጵያ ሠላም፣ ፍትሕና ብልጽግና ይሰፍናል፣ አገሪቱ በጥንካሬዋ በመላው ዓለም ዝና ታተርፋለች፣ እርሱ ሲሞት በኢትዮጵያ ለሺህ ዓመታት የሚዘልቅ የደስታና የብልጽግና ዘመን ይሆናል።» የሚል ትንቢት ስለነበር፣ ይህን ትንቢት የምፈጽመው እኔ ነኝ ለማለትና በሕዝቡ ዘንድ ታማኝነትንና አክብሮት ለማግኘት የመረጡት ስም እንደሆነ ይታመናል። (ዓለማየሁ አበበ ፣ትርጉም፣ 2003፣257)

ሌላው ምክንያት ቀዳማዊ ቴዎድሮስ የሚባል ንግሥ በነበረበት ወቅት አገሪቱና ሕዝቧ ሰላማቸው የተረጋገጠበትና አንፃራዊ ብልጽግናም የታየበት፣ በዚህም የተነሳ በሕዝቡ አክብሮትና ፍቅር የተቸረው እንደነበር ካሣ በመገንዘባቸው፣ የእርሱን ፈለግ ተከታይ ነኝ ብለው የሕዝቡን አመኔታና ክብር ለመቀዳጀት የተጠቀሙበት ነው የሚሉም አሉ። ዳግማዊ ቴዎድሮስ መባላቸው፣ ያላንዳች ጥርጥር፣ ቀዳሚው ቴዎድሮስ መኖሩን ገላጭ ነው።

ከዚህ ላይ መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች፣ ካሣ ቴዎድሮስ የተሰኘውን ስም በየትኛውም ምክንያት ይምረጡ፣ በተግባር በአገሪቱ ሰላም፣ ፍትሕና ብልጽግና ሰፍኗል ወይ? አገሪቱ በጥንካሬዋ በመላው ዓለም ዝና አትርፋለች ወይ? ለሺ ዓመታት የሚዘልቅስ የደስታና የብልጽግና ዘመን ተገኝቷል ወይ? የሚሉት ናቸው።

በእርግጥ በቴዎድሮስ ዘመን በመላ አገሪቱ ሰላም የሰፈነበት ሁኔታ አልነበረም፤ የእርሳቸው ሕይዎት ያለፈው ካንዱ አካባቢ ወደ አንዱ በመዘዋወር የሰላምና የአንድነት ፀር የሆኑ ቡድኖችንና ግለሰቦችን በመታገል ነው። ለመጭዎቹ ዘመናት እንደተባለው ሺህ ዘመን የዘለቀ አይሁን እንጂ፣ የአገሪቱ አንድነት፣ ሰላም፣ መረጋጋትና ነፃነት እንዲሰፍን ያስቻሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ መሠረቶችን ጥለው ማለፋቸው ዕውነት ነው። የአርሶ አደሩ መብት እንዲከበር፣ ዕዳው የታወቀ እንዲሆን፤ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍን የጣሉት መደላድል ቀላል ነው የሚባል አይደለም።

የአገሪቱን ዝና በዓለም ዙሪያ መናኘት በተመለከተ ከቴዎድሮስ አነሳስ እስከ ሕይዎታቸው ፍፃሜ ድረስ ኢትዮጵያን በአንድ ማዕከላዊ አስተዳደር ሥር እንድትመራ የከፈሉት ዋጋ ለዝናዋ መጉላት የመጀመሪያውን በር የከፈተ ነው። ከናፒየር ጋር ያደረጉት ጦርነትና ለሕይዎታቸው ፍጻሜ ማግር የወሰዱት ለክብርና ለታሪክ ኩራት በጠላት ከመማረክ ሞትን በክብር መምረጥና ራሳቸውን በራሳቸው ያጠፉበት ሁኔታ ለኢትዮጵያ ዝና መናኘት የበኩሉን ከፍተኛ ሚና እንደተጫዎተ መገንዘብ ይቻላል።

ከእርሳቸው ሞት በኋላ የተተኩት ዐፄዎች በእርሳቸው የአንድነት ዓላማ ጸንተው መግፋት የተገኘው አንድነት ዳብሮ መቀጠል ለዝናዋ ዋናው ማሳያ ነው። ከዚህበተጨማሪ የሚከተሉት ድርጊቶች ለኢትዮጵያ ዝና በዓለም ላይ መናኘት ዋና ተጠሾች ናቸው።

- ጉራና ጉንደት ላይ በዐፄ ዮሐንስ 4ኛ በተስፋፊዋ ግብፅ ጦር ላይ የተቀዳጁት ድል፤
- ዶጋሊ ላይ ራስ አሉላ አባ ነጋ የምድረ ባሕሪ ገዥ ለቅኝ ግዛት የቋመጠችውን የጣሊያን ጦር ላይ ያስመዘገቡት አኩሪ ድል፤
- በ1888 ዓም ዳግማዊ ምኒልክ በኢጣሊያ ቅኝ ገዥ ኃይል ዐድዋ ላይ የተጎናጸፉት አንጸባራቂ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ድል፣
- በ1928 ማይጨው ላይ ከጣሊያ ፋሽስት ጦር ጋር ያደረገው ተጋድሎ፣
- ከ1928 እስከ 1934 በፋሽስት ጣሊያን ላይ የተካሄደው የአርበኝነት ተጋድሎ፣
- ከሊግ ኦፍ ኔሽን እስከ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት(ተመድ) ድረስ ብቸኛ አፍሪካዊት ነፃ አገር ሆና የድርጅቶቹ አባል መሆን፣
- ለአፍሪካ አገሮች ነጻነት መቀዳጀት ካበረከተችው ጎሊናዊና ቁሣዊ ድጋፍ በተጨማሪ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሠረትና ጽሕፈት ቤቱ አዲስ አበባ እንዲሆን ያበረከተችው ድርሻ፣
- በስፖርቱ ዓለም በተለይም አበበ ቢቂላ፣ ማሞ ወልዴ፣ ምሩፅ ይፍጠር፣ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ደራርቱ ቱሉ የመሳሰሉት የማራቶን ጀግኖች ያስመዘገቡት ድል ኢትዮጵያ ዝናዋ በዓለም ላይ እንዲናኝ አድርጓል።
- በዚህ ረገድ ትንቢቱ አልያዘም የሚያስብል አይደለም። አንፃራዊ በሆነ መልኩም ከምኒልክ ሕልፈት እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን መወገድ ድረስ ያሉት ከግማሽ ምዕተ ዓመታት በላይ ሰላም የተገኘበት፣ አገሪቱም ወደ ዘመናዊ ዓለም የተሸጋገረችበት ዘመን በመሆኑ ትንቢቱ ባዶ ነው አያሰኝም።

ምዕራፍ አምስት፡-

## 9 የቴዎድሮስ ተከታታይ ዘመቻዎችና ውጤታቸው፡-

### 9.1 የቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ፤

ቴዎድሮስ ደጃዝማች ውቤን ድል ከመቱ በኋላ የአገሪቱ ብቸኛ ባለሙሉ ሥልጣን ንጉሠ-ነገሥት ለመሆንና ላቀዱት ታላቅ የኢትዮጵያ አንድነት ዓላማ መሳካት የቀራቸው ከአገሪቱ ዕምብርት ላይ ሆኖ፣ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከቀሩት አካባቢዎች የበለፀገ ኢኮኖሚ ባለቤት የሆነው፣ ምርኮኛ እስረኛቸው፣ ያሳደጉት፣ ደጃዝማች ብለው ልጃቸውን አልጣሽን የዳሩለት፣ በ1857ዓም ከመቅደላ አምልጦ ባባቱ

ወንበር ሸዋ ተቀምጦ፣ የሸዋን ንጉሥ የሆነው ምኒልክ ነው። ሸዋ ከ1764ዓም ጀምሮ ከማዕከሉ ራሱን አግሎ ወደ ደቡብ ከበው ከያዙት ጋሎች (ኦሮሞዎች) ጋር እየተዋጋና ግዛቱን ወደ ደቡብ በማስፋት የቆየ መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም የቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ በቀላሉ የሚታይ አልሆነም። ጉዳዩን ያከበደው የሁለት ነገሮች መጣመር ነው። አንደኛው ሸዋ በኢኮኖሚ የተሻለና የደረጀ አስተዳደራዊ ጠገግ የመሠረተና ለዘውዱ ሕጋዊ መብት ያለው ከልብነድንግል ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለሥላሴ ወራሽ ጋር የሚገጥም መሆኑ ነው። ሁለተኛው  ምኒልክ ከወሎዋ ኦሮሞ ገዥ ከወርቂት ጋር ለመረዳዳት የተስማሙ መሆኑ ነው።(ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 257)

ይህም በመሆኑ የሁለቱን ኃይል በአንድ ላይ መግጠም ለድል ሊያበቃ አለመቻሉን ቴዎድሮስ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተው፣ ነጣጥለው ለመምታት ወሰኑ። በዚህም መሠረት የቅድሚ ዘመቻቸውን በወርቂት በሚመራው ሠራዊት ላይ ወሎ እንዲሆን አደረጉ። ቴዎድሮስ የወርቂትን ሠራዊት ገጥመው ድል ካደረጉ በኋላ፤« ለዓላማቸው ዳር መድረስ የማይወስዱት የጭካኔ ዓይነት ሊኖር እንደማይችል ማሳያ የሆነ ዘግናኝ ርምጃ ወሰዱ። በጦርነቱ የተማረከውን ሁሉ እጁን እየቆረጡ ወደ ወሎ መሀል እንዲሄድ አዘዙ።» (እንደላይኛው፣ 257)

ዳግማዊ ቴዎድሮስ ወሎን በሰቀጠጠ የአካል ቅጣት ካስገበሩ በኋላ፣ ሸዋን ለማስገበር ጥቅምት 10 ቀን 1848 « ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት » ብለው ዘመቱ።  በዚህ አመቻ፣ ቴዎድሮስ አቡነ ሰላማን አስከትለው፤ ከፍተኞቹ የተክሕኖ መኳንንት ከሠራዊቱ በፊት እንዲጓዙ አድርገው መንዝ ገቡ።  በአቡነ ሰላማ አማካኝነት የመንዝ ሕዝብ ግርግር ሳይፈጥር ገባላቸው። የሣህለሥላሴ እናት ወ/ሮ ዘነመወርቅ፣ የግሸው መኮንን ሀብተ ማርያም፣ የኤፍራታው መኮንን አቶ በድሉ በሰላም ገቡላቸው። ቴዎድሮስ መንዝ በሰላም ከገባላቸው በኋላ፣ ጉዞአቸውን ወደ ንጉሥ ኃይለመለኮት መቀመጫ አንኮበር ሲያቀኑ፣ ጉር ሥላሴ ላይ፣ በአቶ ሀብቱ የሚመራው የንጉሥ ኃይለመለኮት ሠራዊት ጋር ተጋጩ። በዚህ ግጭት አቶ ሀብተ- ማርያምና ወታሮቹ፣ ከቴዎድሮስ የተወሰኑ ወታደሮች ሞቱ። (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣ 1996፣ 106)

ቴዎድሮስ ከጉር ግጭት በኋላ ንጉሥ ኃይለመለኮትን ለማስገበር ወደ መናገሻ ከተማቸው አንኮበር ሲጓዙ፣ ኃይለመለኮት ኃይላቸውን መዝነው  እኤአ ጥቅምት 26 ቀን 1855 አንኮበርን አቃጥለው መሸሻቸው ተሰማ። በቃጠሎው ቤተመንግሥቱና የከተማይቱ ግማሽ ክፍል ወደመ።(ዓለማየሁ አበበ ፣ትርጉም፣ 2003፣ 258)   ኃይለመለኮት ከተማቸው አንኮበር በጠላት እጅ ከምትገባ መቃጠሏን መርጠው አቃጥለው ከወጡ በኋላ፣ እኤአ ኅዳር 8 ቀን 1855 በድንገት አረፉ። በዚህም የተነሳ የሸዋ መኳንንት  የንጉሣቸውን እረፍት በሚስጢር ይዘው የቴዎድሮስን ጦር  እኤአ ኅዳር 9 ቀን 1855 ገጠሙ። «መሪ የሌለው ሠራዊት፣ ንጉሥ የሌለው ንብ አንድ ነውና»፣ የሸዋው ጦር በቀላሉ በቴዎድሮስ ድል ሆነ። አንኮበር በቴዎድሮስ እጅ ገባች። አንኮበር በቴዎድሮስ እጅ ስትገባ፣ እኤአ 1842 ሻለቃ ሐሪስ ለንጉሥ ሣህለሥላሴ የሰጣቸው ሁለት መድፎች በቴዎድሮስ እጅ ገቡ።(እንደላይኛው፣ 258)

የአሁኑ የቴዎድሮስ የሥልጣን ባላንጣ፣ የዚያን ጊዜው የ11 ዓመት ከ11 ወር ዕድሜ የነበረው፣ ብቸኛው የንጉሥ ኃይለመለኮት ልጅ ሣህለማርያም (ምኒልክ) በዚህ ጦርነት አልተሳተፈም። መኳንንቱ ምኒልክን በአልጋው አስቀምጠው ቴዎድሮስን ለመውጋት ወሰኑ። በውሣኔአቸው መሠረትም የጦርነቱ አውድማ በረከት እንዲሆን ሆነ።

የበረከት ጦርነት  ኅዳር 30 ቀን 1848 ዓም በቴዎድሮስ እና በምኒልክ የጦር አበጋዞች መካከል የተደረገ ነው። በቴዎድሮስ ወገን ራስ እንግዳ፣ ቢትወደድ ብሩ እና ቢትወደድ ውቤ  የጦሩ አዝማቾች ሆነው ተሰለፉ። በጦርነቱ የምኒልክ ሠራዊት ድል ሆነ። የሸዋ መኳንንት በጦርነቱ ድል እንደሆኑ፣ ምኒልክን ይዘው ወደ ምንጃር ሸሹ። በዚህ ጦርነት አቶ ሸሽጉን ጨምሮ በርካታ ጀግኖች ሲሰው፣ አቶ በዛብህ (በዙ አባደክር) እና አቶ አንዳርጋቸው ተማረኩ። ምኒልክን ይዘው የሸሹት መኳንንቶች  ከቴዎድሮስ ጋር ሌላ ጦርነት ማድረግ እንደማያዋጣ ተረድተው፣ ምኒልክን ለቴዎድሮስ ለማስረከብና እጅ ለመስጠት ወሰኑ። በውሣኔአቸውም መሠረት እጅ ሰጡ። ( ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፤ 1996፣ 108)

ቴዎድሮስ የምኒልክን እጅ መስጠት ካረጋገጡ በኋላ ደብረሊባኖስን ለመሳለም በምንጃር በኩል አድርገው ተጓዙ። በጉዞአቸውም የአካባቢው ጋላ(ኦሮሞ) ተከታይ ሠራዊታቸውን እያደፈጠ ገደለባቸው። ይህን ተቋቁመው ደብረሊባኖስን ተሳልመው ጉዞ ወደ አንኮበር ሲመለሱ፣ ራስ እንግዳ የመርድ አዝማች ስብስቴ ከተማ  በሆነችው «ሐር አምባ» በኩል እንዲያልፍ አደረጉ። የዚህን የንቅናቄ ትዕዛዝ የሰማው ሠራዊት «ኢየሩሳሌም ወስዶ ሊያስፈጀን ነው» የሚል ጉርምርምታ ድምፅ ማሰማት ጀመረ። የዚህ ጉርምርምታ መሠረቱ ቴዎድሮስ «የኢትዮጵያ ባል፣ የኢየሩሳሌም እጮኛ» እያሉ አንዳንድ ጊዜ ይፎክሩና ይናገሩ ስለነበር፣ ጉዞው ያ ሳይሆን አይቀርም የሚለውን የፈጠራ  ወሬ የቴዎድሮስ ጠላቶች የሆኑት ካህናት በሠራዊቱ ውስጥ ሆን ብላው በመንዛታቸው ነበር።

የዚህ የጉርምርምታ ወሬ ፈጣሪዎች ሆነው የተገኙት የክህነት ሥልጣን የሌላቸው ከዳሞት የመጡ የጎጃም ሰዎች መሆናቸው ታወቀ። ሰዎቹ እንደቄስ በመጠምጠም፣ ወታደሩ በሰፈረበት ቦታ ሌሊት ሌሊት እየዞሩ፣« ለዚህ ንጉሥ እንጨት የሰበረ፣ ውኃ የቀዳ፣ ሣር ያጨደ፣ የተከተለ ውግዝ ይሁን፤ ይህ ቃል የእኛ ሳይሆን፣ የአቡነ ሰላማና የእጨጌ ወልደማርያም ነው።» በማለት ግዝት አስተላለፉ። (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም 1996፣ 109)

ዐፄ ቴዎድሮስ ከደብረሊባኖስ ተጉዘው ቶራ መሥክ በሠፈሩበትም ወቅት እነዚህ ሰዎች የተለመደ የቅስቀሳና ጡሩን የማሳመጽ ሥራቸውን ቀጠሉ። በዚህም መሠረት ቴዎድሮስ «እባብ ከበዛበት አገር ወስዶ ሊያስጨርስህ ነው፤ እንዳትከተለው!» በማለት ግዝታቸውን አጠናካረው ቀጠሉ። ይህ ሁኔታ ሲከታተል የነበረ በቴዎድሮስ ዓላማና አመራር ከልቡ የሚያምን፣ የተባለውንና የሰማውን ለቴዎድሮስ ነገረ። የሰዎቹ ማንነት ተጣርቶ እንዲያዙና ለፍርድ እንዲቀርቡ ታዘዘ። በተደረገው ማጣራት ሰዎቹ ከጎጃም ከዘመቱትና ታላላቅ ከሚባሉት ሰዎች መካከል መሆናቸው ተረጋገጠ። የሰዎቹ ማንነት ከታወቃ በኋላ፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ « ከፉ የመከረ ምን ይገባዋል?» ብለው ጠየቁ። የተጠየቀው የቴዎድሮስ መኳንንት በአንድ ድምፅ «ሞት ይገባቸዋል» ሲል ድምፁን ሰጠ። በዚህም መሠረት ወሬውን ሲያዘምቱ የነበሩ ሁለቱ ሰዎች እና ተከታዮቻቸው የነበሩ 48 ሰዎች በነፍጥና በጎራዴ ተቆራርጠው እንዲገደሉ ሲሆን፣ የወሬው አመንጭዎች ጎጃም ቡሬ ገበያ በስቅላት እንዲቀጡ » ሆነ። (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም ፣1996፤ 110—111)

ቴዎድሮስ ቶራ መሥክ ላይ ይህን ውሣኔ ሰጥተው፣ የንጉሥ ኃይለመለኮት ተከታይ የነበረው የሸዋ መኳንንት ከቶ የገባላቸው መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ፣ ምኒልክን አሥረው ወደ መቅደላ ላኩ። የንጉሥ ሣህለሥላሴን ልጅ፣ ልጅ ኃይሌን፣ « መርዕድ አዝማች » ብለው የሸዋን ግዛት እንዲያስተዳድር ሹመው ጉዞ ወደ ቤጌምድር አደረጉ።

ቴዎድሮስ የአገር አንድነቱን በመሣሪያ ኃይል አረጋገጡ። እያንዳንዱ ባላባት የቴዎድሮስን መሪነት በግድ ተቀበለ። ልቦናውን ግን የሰጣቸው አልነበረም። ቴዎድሮስን ከዙፋን ዘርጥጦ ለመጣል ሁሉም ማድባቱን አልተወም። በመሆኑም እኤአ 1855 እስከ 1857 ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ብቻ በቴዎድሮስ ላይ 17 ጊዜ የግድያ ሙከራዎች ተገርጎባቸዋል። በግድያ ሙከራዎቹም ብዙን ጊዜ ቆስለዋል።( ዓለማየሁ አበበ ትርጉም፣ 2003፣ 259)

**9.2 የዐመዴ በሽር ማመጽና በወሎ ሕዝብ ላይ ያስከተለው ዕልቂት፡-**

በ1849 ዓም ዐመዴ በሽር ወሎ ውስጥ በአገዛዛቸው ላይ አመጸ። ቴዎድሮስ አማፂውን ዐመዴ በሽርን ለማስገበር ከደብረታቦር ተነስተው በጨጨሆ አድርገው ኮሬብ ገቡ። የቴዎድሮስን ኮሬብ መግባት የሰማው አማፂው ዐመዴ በሽር ፊት ለፊት መግጠሙ እንደማያዋጣው በመገንዘብ ኮሬብን ለቆ ሸሸ። በዚህ ዘመቻ ላይ እንዳሉም የመቅደላው ሹማቸው ሊበን መክዳቱን ሰሙ። በዚህ የተበሳጩት ቴዎድሮስ ጉዞአቸውን ወደ መቅደላ አድርገው፣ በሊበን ቦታ የወርቂትን ልጅ ዓመዴ ዓሊን ሹመው ወደ ጋይንት የመልስ ጉዞ አደረጉ። (እንደላይኛው 113)

በዚሁ ዓመት ምሕረት መጋቢ ወር ላይ ቴዎድሮስ ለሁለተኛ ጊዜ ከዙራምባ ተነስተው ወደ መቅደላ ተጓዙ። የጉዞአቸው ዓላማም መቅደላን የመጨረሻ ምሽጋቸው ለማድረግ ባላቸው ዕቅድ መሠረት አምባውን በሰው ኃይል ለማጠናከር እንደሆነ ይታሰባል። በዚህም መሠረት ቀደም ሲል ለአንባው አስተዳዳሪነት ሹመውት የነበረውን አመዴ ዓሊን ሽረው በቦታው ግራዝማች ዓለሜን፣ አፈንጉሥ ወርቁን፣ ባሻ ቢሰውርን፣ ቀኛዝማች ጣዩን እና አምስት ሃምሳ አለቆችን ሾመው ተመለሱ። የእርሳቸውን መመለስ የተረዳው አማፂው ዐመዴ በሽር አምባውን ለመቆጣጠር ከግራዝማች ዓለሜ ጋር ጦርነት ከፈተ። በዚህ ጦርነት ዐመዴ በሽር 106 ሰዎች ከነግራዝማች ዓለሜ ወገን ገድሎ አመለጠ።

ዐመዴ በሽር የቀሰቀሳቸውና የዓላማው ተካታይ ያደረጋቸው የእምቢላጤ ሰዎች በቴዎድሮስ ተከታዮች ግድያ ፈጸሙ። አመጽ ቀሰቀሱ። ይህ ድርጊት ያበሳጫቸው ቴዎድሮስ፣ **ከጊንባ እስከ ደጋላስ፣ ከአምራ ገደል እስከ ጨሬ ያለው አገር ያለምሕረት** እንዲደመሰስ ትዕዛዝ ሰጡ። ሕዝብ አለቀ። ንብረት ተዘረፈ። በተመሳሳይ ሁኔታ **ተኩለደሬ** የተባለው አካባቢ የዐመዴ በሽር ደጋፊ ሆኖ በመገኘቱ በሙሉ እንዲጠፋ ሆነ። «ለተባባሰው ማጭድ አታውሰው» ሆኖ ነገሩ፣ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሰነቁት የብልጽግና ራዕይ መሰናከል የሆኑ የአካባቢ ባላባቶች በየቦታው የሚፈጥሩት አመፅ ለመደምሰስ ከቦታ ቦታ ሲንከራተቱ፣ የዓላማቸው አጋር፣ የትግላቸው ቀኝ እጅ የነበሩት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ዓሊ፣ ቴዎድሮስ **«ግራኝ ሜዳ »** ላይ ሠፍረው ከነበረበት ቦታ ነሓሴ 13 ቀን 1850 ዓም አረፉ። ይህ ለቴዎድሮስ ከፍተኛ ሀዘንና ከባሕሪ መለወጥ ጋር ያስከተለ ክስተትን ትቶ እንዳለፈ ይታመናል። ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚሰጡዋቸው ውሣኔዎች ሁሉ ጭካኔ የተሞላባቸው በመሆኑ በየቦታው ላአማጺያኑ መበራከት አስተዋጽዖ እንዳደረገ ይታመናል።(እንደላይኛው 123—124)

ቴዎድሮስ የባለቤታቸውን አስከሬን ከነሐሴ 13 ቀን 1850 ዓም እስከ ጥቅምት 1 ቀን 1851 ዓም ባሉት 47 ቀኖች በአልጋ አስይዘው ያደረጉት ረጅም ጉዞ እንዴት አድካሚና አሰልች እንደነበረ የሚረዳው በተግባር ያየ ብቻ ነው። የክረምቱን፣ ውኃ ሙላት፣ ጭቃ፣ ዝናብና ውሽንፍር ተቋቁመው ከግራኝ ሜዳ እስከ ግሸን ማርያም ድረስ መጓዝ እጅግ ከባድ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል። ቴዎድሮስ ይህን ሁሉ ተቋቁመው የሚያከብሯቸውና የሚወዷቸውን ባለቤታቸውን አስከሬን ግሸን ማርያም በክብር እንዲያርፍ አድርገዋል። ይህ ለባለቤታቸው የነበራቸውን አክብሮትና ፍቅር የቱን ያህል እንደነበር የሚያሳይ ቢሆንም፤ አስከሬኑን ተሸክሞ ይጓዝ በነበረው ሠራዊታቸው ላይ በሁሉም ዘንድ ደስታን የፈጠረ ነበር ለማለት ያስቸግራል።

ቴዎድሮስ ለባለቤታቸው የነበራቸውን አክብሮትና ፍቅር በቀብራቸው ዕለት እንዲህ ብለው ማስለቀሳቸው ይታወቃል።

**«ብዙ ሥራ ዐዋቂ ትናንት ተቀበረች፣**

**መድኃኒቱን ምሣ ታበላኝ ነበረች፤**

**እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ፣**

**እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ፤»**

ቴዎድሮስ ዐመዴ በሽርን በቀላሉ ሊያዝላቸው አልቻለም። በመሆኑም ኅዳር ወር 1853 ዓም ዐመዴን ለማስገበር ወይም ለመደምሰስ ወደ ወሎ ዘመቱ። ዐመዴ በሽምቅ ውጊያ እንጂ፣ ፊት ለፊት የመግጠም አቅም ስላልነበረው፣ ቴዎድሮስ መጣ ሲሉት ሸሸቱን ቀጠለ። በዚህም የተነሳ የርሱ ደጋፊ ነው ያሉትን **ከጉራምባ ጀምሮ እስከ ገነቴ እና ጨለቃ ወንዝ** ያለው እስከ **ሸዋ ድንበር ያለው** አገር እንዲመታ አዘዙ። እንደተለመደው ሕዝብ አለቀ። ንብረት ተዘረፈ።

ዳግማዊ ቴዎድሮስ ዐመዴ በሽርን ለማደን ወሎ በቆዩበት ጊዜ ውስጥ፣ የሸዋው ገዥ መርዕድ አዝማች ኃይሌ፣ 1000 (አንድ ሺ) ፈረስ፣ 788 በቅሎ፣ እልፍ (ሺ) ብር፣ አንድ ሺ ሸማ፣ በርካታ ሰንጋ፣ ብዛት ያለው ልግም ልብስና ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ግብር ይዞ መጥቶ ተገናኘ። በዚህም አድራጎቱም ቴዎድሮስ ተደሰቱ። መርዕድ አዝማች ኃይሌ ለቴዎድሮስ ያበረከተው ግብርና ሥጦታ ከልብ የመነጨ እንዳልሆን የሚያጋልጥ ክስ ሥራህብዙ የተባለ ሰው ክስ መሠረተበት። ክሱም እንዲ የሚል ነው። «መርዕድ አዝማች ኃይሌ የዐመዴ በሽርን መላክተኛ ተቀብሎ ካነጋገረ በኋላ፣ ልብስ አልብሶ ሰዷል፤» ይህም የርሱ ተባባሪነቱን ያሳያል ሲል የክስ ጭብጡን አስያዘ።

መርዕድ አዝማች ኃይሌ፣ ከሥራህብዙ ለተሰነዘረበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ተጠየቀ። መርዕድ አዝማች ኃይሌ ከዐመዴ በሽር መልዕክተኛ መምጣቱን አምኖ፣ እንዲተባበረው ላቀረበለት ጥያቄ ግን ፈቃደኛ አለመሆኑን ፣ ለመልዕክተኛው ግን ልብስ ማልበሱን አምኖ ተናገረ። ቴዎድሮስ ይህን እንደሰሙ፣ «ለዚህ ዓይነቱ ድርጊት ምን ማድረግ ይሻላል?» ብለው ለመኳንንቶቻቸው ጥያቄ አቀረቡ። ጥያቄ የቀረበላቸው መኳንንቶችም «ሊቀጣ ይገባል» በማለት ድምፅ ሰጡ። ቴዎድሮስም መርዕድ አዝማች ኃይሌ በእሥራት እንዲቀጣ ወሰኑ።

የመርዕድ አዝማች ኃይሌ ጉዳይ በዚህ ከተቋጨ በኋላ፣ ቴዎድሮስ ለሸዋ ማን ቢሾም እንደሚሻል ለሥራህብዙ ጥያቄ አቀረቡለት። ሥራህ ብዙም ለሸዋ ዳርጌን ቢሾሙት ይሻላል ሲል አስተያየቱን ሰጠ። ቴዎድሮስም «ዳርጌን ሸዋ ይወደዋል ወይ?» ሲሉ ጠየቁት። እርሱም መለሰና አዎ« እጅግ ደስ ይለዋል፣ ሰላምም ይሆናል» አላቸው። ቴዎድሮስም ሥራህብዙ የሰጣውን አስተያየት ተቀብለው ዳርጌን የሸዋ ገዥ አድርገው ሾሙ።

ዳርጌ የሸዋ ገዥ እንዲሆኑ ከተሾሙ ከሦስት ቀን በኋላ፣ ጃራ የተባለ ሰው ተነስቶ በሥራህ ብዙ ላይ ክስ መሠረተ። የክሱ ጭብጥም እንዲህ የሚል ነው። «ሥራህ ብዙ ለዳርጌ ብር ሰጥቶ ውስጥ ለውስጥ ተማምሏል» የሚል ነው።ሥራህብዙ ይህን ስለማድረጉ ሲጠየቅ ካደ። ከሣሹ ጃራም የዋዛ አይደለምና፣«ገንዘብ ለመስጠትህ፣ ውስጥ ለውስጥ እንደተማማክ በፈረስ ጠጉር ቁጥር ልክ፣ ከነ ለጓሚው፣ ከነማጭዱ፣ ከነሥርዓቱ ፈረስ እሰጥ» ብሎ ቆመ። ይህ ድርጊት የማያወላዳው እና የሚመሰከርበት እንደሚሆን የተረዳው ሥራህ ብዙ፣ ድርጊቱን መፈጸሙን አመነ። ዳርጌም ስለሁኔታው ሲጠየቁ ሥራህብዙ እንዳለው ያደረጉ መሆኑን አምነው አስረዱ። በዚህ ድርጊት ያዘኑት ቴዎድሮስ ዳርጌን እንዲታሰሩ አደረጉ። ሥራህብዙን ወቅሰው ለቀቁት።(እንደላይኛው፣128—129)

ዳግማዊ ቴዎድሮስ የዳርጌንና የሥራህ-ብዙን ሁኔታ መዝነው፣ ዳርጌን በእሥራት፣ ሥራህብዙን በተግሳጽ ከቀጡ በኋላ፣ የወረኢሉው ገዥ ዐመዴ ብሩ፣ ዓሊ አደራ የተባለው የለገጎራው ገዥ፣ «ከዐመዴ በሽር ጋር በሚስጢር ተነጋግሯል?» የሚል ክስ መሠረተ። ክስ የቀረበበት ዓሊ አደራ፣ የተመሠረተበትን ክስ አምኖ፣ ዐመዴ ብሩም ከዐመዴ በሽር ጋር መነጋገሩን መልሶ አጋለጠ። በተመሳሳይ ሁኔታ ዐመዴ ብሩም አመነ። በዚህ ሁኔታ የተገረሙት ቴዎድሮስ ሁለቱም እንዲታሰሩ ወሰኑ።

የለገ ጎራው ገዥ ዓለ አደራ ከዐመዴ በሽር ጋር የሚስጢር ንግግር አድርጓል ተብሎ ተከሶ በሰጠው የእምነት ቃል እንዲታሰር ከተደረገ በኋላ፣ ዐመዴ በሽር በለገ ጎራው መውጣትና መግባት አዘወተረ። ዐመዴን በሽርን ለመውጋት ቴዎድሮስ ሀሳብ ቢኖራቸውም፣ ሕዝቡ ከእርሱ ጋር የወገነ መሆኑን በመገንዘባቸው፣ አገሩ እንዲቃጠል ወሰኑ። ንብረት ተዘረፈ። ሕዝብ አለቀ። ቴዎድሮስም ወታደሩ ከዘረፈው ሁለት ሁለት ከብት ለራሱ ወስዶ፣ ከዘረፈው ውስጥ ሁለቱን እጅ ለንጉሡ ገቢ እንዲያደርግ አወጁ። (እንደላይኛው 129)

ቴዎድሮስ አከታትለው የዐመዴ በሽር ደጋፊ ነው የተባለውን **ጨፋን ወረሩ**። ሕዝቡን መቱት። በዚህ ወረራ የተገኙትን ባሪያዎች ሠራዊታቸው እንዳይሸጥ እና እንዳይለውጥ አማሉት። በቁስም አስገዘቱት። ይህም ለሁለተኛ ጊዜ ማለትም ከባሶ በኋላ የባሪያ ነፃነት ያወጁበት አጋጣሚ መሆኑ ነው። ጨፋ ለሸዋ አዋሳኝ በመሆኑ፣ የጨፋን መወረር የሰማው የምሥራቅ ሸዋ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ

ሕዝብ 13 ቀን የሚፈጅ የእግር መንገድ በመጓዝ መሰደዱ ተሰማ። በማስከተልም ቃሉን ለመውረር ከቦሩ ሜዳ ወደ ገራድ ተጓዙ። ገራድ ላይ ሆነውም ለተከታይ ሠራዊታቸው «ቃሉን ዲና ብየሃለሁ፣ ዝረፈው፣ ልጅና ሽማግሌ አትግደል፤ ከሚዋጋህ በቀር አማኙን አትንካ» ብለው ትዕዛዝ ሰጡ። በዚህ ወረራ ብዙ ሕዝብ ተጎዳ። ንብት ተመዘበረ። (እንደላይኛው፣ 131)

ቴዎድሮስ ከቃሉ ዘመቻ በኋላ ወደ ዋድላ ሄዱ። ወደዚህ የሄዱበትም ጋፋት ላይ ያሠሩትን «ሶባስቶፎል» የተሰኘውን መድፍ ወደ መቅደላ ለማውጣት መንገዱን ለማሠራት ነበር። በዚህም መሠረት ከጨጨሆ በር እስከ ቤተሆር ያለውን መንገድ ሰንደል ለተሰኘ የነምሳ ተወላጅ ቀያሽነት እንዲሠራ አደረጉ። ለዚህ መንገድ ሥራ የአካባቢው ሰው ባለመተባበሩ፣ የዋድላውን ምስለኔ፣ ይመርን ገርፈው በማሰር ለመንገድ ሠሪው መኃንዲስ ሰንደል የራሳቸውን በቁሎ ከነመጣምርና ኮራቻዋ፣ ቀሚሷን፣ ሱሪያቸውን፣ አንድ ሺ ብር፣ አድርገው ሸለሙት። ከሰንደል በመንገድ ሥራው ለተሰለፉት እንግሊዛውያን ዜጎች በንደር፣ ኪንድለን እና ማዬር ስድስት መቶ ብር በመስጠት ሥራውን እንዲያቀላጥፉ አበረታቷቸው።

ዳግማዊ ቴዎድሮስ ዳውንት መሄድና በመንገዱ ሥራ ላይ ትኩረት መስጠታቸው ዐመዴ በሽር ከተደበቀበት ለመውጣት ምቹ ሁኔታ የፈጠረለት መስሎ ታየው። በዚህም የተነሳ የቴዎድሮስን ሹመኛ ፋሪስ ቃሲምን በማሳደድ ከመቅደላ በሥተምሥራቅ ከምተገኘው ጠዳት አፋዛዝ ላይ አደረሰው። የዐመዴን ወደ መቅደላ መጠጋት ያወቁት ቴዎድሮስ የካቲት 28 ቀን 1852 ዓም ከዋድላ ደላንታ ገሥግሠው ጠዳት አፋዛዝ ሲደርሱ እንደተለመደው ዐመዴ በሽር ሸሽቶ ጠፋ። ቴዎድሮስ ዐመዴን ለመያዝ ወይም ለመግጠም ባደረጉት ክትትል «ከዐማራው አገር አሶል ወረዳ ገብቶ ሕዝብ እየደበቀ ያኖረዋል» የሚል መረጃ ደረሳቸው። በዚህም የተነሳ አገሩ እንዲወረር አዘዙ። በምርኮ የተያዘውን ፤ ክርስቲያን ክርስቲያኑን እየለቀክ እስላም እስላሙን ባርያ አድርገህ ግዛው» ብለው ለሠራዊታቸው ትዕዛዝ ሰጡ። (እንደላይኛው ፣132) የዚህም ውሣኔአቸው መሠረቱም ዐመዴ በሽር የእስልማና ሃይማኖት ተከታይ ስለነበር እስላሙ የርሱ ደጋፊ ሆኖ ስላገኙት ነው።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ አንድ እስላም ክርስቲያን ገድሎ ተከሶ ከእርሳቸው ዘንድ ይቀርባል። ለምን እንደገደለው ሲጠየቅ፣ « ንጉሥ ሆይ! ደሜን በከንቱ አላፈስም፣ የገደልኩበት ምክንያት ካፊርና እስላም ጥንት ከመሐመድ ጀምሮ፣ እስከ ግራኝ፣ ከግራኝ እስከ ዛሬ ድረስ ደመኞች ነን፤ በዚህም የተነሳ ገደልኩት» ብሎ መለሰላቸው። ቴዎድሮስ የተከሳሹን መልስ ካዳመጡ በኋላ፣ በጥይት ተደብድቦ እንዲገደል ወሰኑ። ሞት የተፈረደበት እስላምም « የመሐመድ ባርያ» ብሎ በመፈከር ሞቱን በፀጋ ተቀበለ።

ቴዎድሮስ ሰውየው ሊገደል ሲል «የመሐመድ ባሪያ» ብሎ መፈከሩን ሲሰሙ፣ በሁኔታው በመገረም፣ «ከዐመዴ ጋር የተጣላነው በግዛት(ሥልጣን) መስሎኝ ነበር፤ ለካ ጠባችን በሃይማኖት ነው፤ በሃይማኖት የተነሳ ደመኞች በመሆናችን ነው ለካ ጠባችን የከረረው፤» በማለት ዐመዴ በሽር ከእርሳቸው ጋር ጠብ የፈጠረው በሥልጣን ሳይሆን፣ በሃይማኖት መሆኑን ከሰውየው አባባል ለመረዳት እንደቻሉ እንገነዘባለን። የዐመዴ በሽር ከቦታ ቦታ እየተሽሎከለከ ለብዙ ጊዜ የመቆየቱ ሚስጢርም ይኸው ከሃይማኖቱ ጋር በተያያዘ አማኙ ሕዝብ መከታና ጠለላ ስለሆነው እንደሆነ ቴዎድሮስ ሳይገነዘቡ አልቀሩም።(እንደላይኛው፣ 133)

ቴዎድሮስ ዐመዴ በሽርን ለመያዝ ያደረጉት ጥረት ሳይሳከ ትኩ ብርሌም የርሱ አጋር ሆኖ በአገዛዛቸው ላይ አመጸ። እነዚህን አማጽያን አሳዶ ለመያዝ ተደብቀውበታል ወደሚባለው አማራ ሳይንት ዘመቱ። በዚህ ዘመቻ ሁለቱ አማጽያን ተከበቡ። እንደተለመደው ዐመዴ አመለጠ። ደጃዝማች ትኩ ብርሌ ግን ተያዙ። ትኩ ብርሌ ቴዎድሮስን ለመውጋት በጠላትነት ሲሰለፉ፣ ሁለቱ ልጆቻቸው ደግሞ ከቴዎድሮስ ጎን ሆነው አባታቸውን ይወጋሉ። አንዱ ልጃቸው በፋመው ጦርነት አባቱን አቁስሎ በመማረክ ለቴዎድሮስ አስረከበ። ቴዎድሮስ አባታቸውን ለማረኩት ታማኞቻቸው፤ «ካባታቸው እኔን ወደው ይኸን ያህል ተጋድሎ ካደረጉ ያባታቸው ግዛት ይገባቸዋል ብለው መረቁላቸው።

በዐመዴ ማምለጥ የተበሳጩት ቴዎድሮስ የተደበቀበትን ቦታ ሲያጣሩ፣ **አማራው አገር ማሻ ውስጥ እንዳለ** ዐወቁ። ወደ ማሻም ተጓዙ። ዐመዴ ከማሻ ወደ አያታ ሸሸ። ይህ ሰው ከቦታ ቦታ እየተሽሎከለከ አልጨበጥ በማለቱ ፣ቀደም ሲል «ዐመዴ በሽርን፣ ያበላ፣ ያጠጣ፣ ይቀጣል» የሚል አዋጅ አስነግረው ስለነበር፣ ይህን አዋጅ አላከበረም ያሉትን **ከኩሉ እስከ ገነቴ ያለ**ውን አገር እንዲዘረፍ አዘዙ። ዐመዴንም ከቦ ለመያዝ ሠራዊታቸውን በሁለት ከፍለው አለበት፣ ይኖርበታል የተባለውን አካባቢ እንዲከበብ አደረጉ። ለዚህም እግረኛው በቆላው፣ ፈረሰኛው በደጋው እንዲሰማራ አደረጉ። በዚህ የከበባ ሥልት ብዙ ወሎዬ እየተማረከ ተያዘ። በምርኮ ከተያዘው ሰው ውስጥ ተዋጊውን፣ የጦር መሣሪያ የያዘውን እየመረጡ 787 ሰዎች መስከረም 13 ቀን 1852 ዓም ከገበያ መሀል ሁለት ሁለት እጁን በመቁረጥ ቀጡት። በአጠቃላይ ቴዎድሮስ ዐመዴ በሽርን ለመያዝ ሰባት ጊዜ ወሎ ዘምተዋል። (እንደላይኛው፣ 137)

### 9.3 ቴዎድሮስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ሸዋ መዝመት፤

ቴዎድሮስ በንጉሥ ኃይለመለኮት መሞትና በነጋሲ ልጃቸው ምኒልክ ምርኮኛ መሆን የተነሳ፣ ሸዋን በቀላሉ ካስገበሩ በኋላ፣ የንጉሥ ሣህለሥላሴን ልጅ «መርዕድ አዝማች» የሚል ማዕረግ ሰጥተው ኃይሌን ገዥ ማድረጋቸው ይታወቃል። ሆኖም መርዕድ አዝማች ኃይሌ ከዐመዴ በሽር ጋር በፈጠረው ሚስጢራዊ ግንኙነት ታስሮ ከኃላፊነቱ መነሳቱን ከፍ ሲል ተመልክተናል። ቴዎድሮስ ዳርጌን በእግሩ እንዲተካ ቢያደርጉም ፣በተመሳሳይ ሁኔታ ከዐመዴ በሽር ጋር ንክኪ አለው የሚል መረጃ ቀርቦ፣ ዳርጌም ያን ማስተባበል ባለመቻሉ መታሰሩን አይተናል። በዚህም የተነሳ ለሸዋ ገዥ እንዲሆን የተደረገው በረከት ላይ ከምኒልክ ጎን ቆሞ የጀግንነት ሥራ ሠርቶ የተማረከው በዛብህ (በዙ አባደክር) ነው። ይሁን እንጂ፣ የሣህለሥላሴ ልጅ፣ ልጅ ሰይፉ ለሁሉም የሸዋ ገዥዎችም ሆነ ለቴዎድሮስ አገዛዝ ፈቃደኛ ስላልነበር፣ ኃይሉን ውስጥ ለውስጥ ሲያደራጅ ከርሞ በመጨረሻ አሻፈረኝ በማለት ዱር ገባ።

የሰይፉን መሸፈት ቴዎድሮስ እንዳወቁ፣ የተለመደ ዘመቻቸውን በ1852 ዓም ወደ ሸዋ አደረጉ። ቴዎድሮስ ሸዋ እንደገቡ ሰላ-ድንጋይ ላይ ወታደሮቻቸው ከእርሳቸው ትዕዛዝ ሳይቀበሉ፣ ሕዝቡን ከፉኛ በመዝረፋቸው ተበሳጭተው የ37 ተከታዮቻቸውን እጅና እግራቸው እንዲቆረጥ አደረጉ። (ይህ ድርጊት ጭካኔ ይመስላል። ነውም። ግን ለዕውነት የቆመና ታላቅ ራዕይ አንግቦ ለሚንቀሳቀስ እንደቴዎድሮስ ላለ መሪ ዕውነት ማሳያ ሌላ መንገድ በወቅቱ ስለሌለ፣ ቴዎድሮስ ሕግና ሥርዓት ለማስተመር ሲሉ ፍርዳቸው ለሁሉም ዕኩል መሆኑን ማሳያ እንደሆነ አመላካች ተግባር ነው)

ጥቅምት 2 ቀን 1852 ዓም የሰይፉና የቴዎድሮስ ጦር ገጠመ። በጦርነቱ የቴዎድሮስ ኃይል ያየለ መሆኑን የተገነዘበው ሰይፉ፣ ስለሁኔታው ለጦሩ ሳያሳውቅ ታማኞቹን ይዞ ሸሸ። ጦሩ የአዝማቹን የሰይፉን መሸሽ ሳያውቅ ገትሮ ተዋጋ። ሆኖም፤ የሰይፉ ጦር በአስተባባሪ ጉድለት የማታ ማታ ድሉ የቴዎድሮስ ሆነ። ለድሉም ወሳኙን ሚና የተጫወተው፣ የቴዎድሮስ ጦር የአንኮበርን ቅጥር ሰብሮ መግባቱና ከተማውን መቆጣጠር መቻሉ ነው። በዚህ ጦርነት ቴዎድሮስ አራት መድፎች፣ በርካታ ነፍጥ(ጠብመንጃ)፣ እና በርካታ ንበረት ከቤተመንግሥት ዕቃዎች ጋር ከቴዎድሮስ እጅ ገባ። ድሉ የቴዎድሮስ ቢሆንም፣ ጦርነት ነውና የቴዎድሮስ የሻለቃ ጦር አዛዥ የነበረው ጋላ ብሩ ሁለት የመቶ ጦር አዛዦች፣ ቁጥራቸው ያልታወቁ ወታደሮች ሲሞቱ 200 ቆስለዋል። በሌላ በኩል ከሰይፉ ጋር ሆኖ ሲዋጋ የነበረና የተማረከ 700 ሰው እጅ እግሩ እንዲቆረጥ ተደርጓል።(ገሪማ ታፈረ፤ 2ኛ ዕትም፣1996፣138—139) ይህ ሁላ ሆኖ ሰይፉን መያዝ አልተቻለም። በዚህም ጊዜ ነው ገጣሚዎች እንዲህ በማለት የተቀኙት፤

> **«ይህ ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ፤**
>
> **የሸዋን መኳንንት እጅ ነስተውት ሄዱ፤» የተባለው።**

### 9.4 የጋረድ መሸፈትና የቴዎድሮስ ከሸዋ መመለስ፥

ቴዎድሮስ ሰይፉን ለማስገበር ሸዋ በዘመቱበት ጊዜ፣ በትግሬና በሰሜን አገው ንጉሤና አገው ተሰማ የተባሉ ወንድማማቾች ሸፍተው በቴዎድሮስ ሹመኞች ላይ ፀጥታ አደፈረሱ። በተመሣሣይ ሁኔታ የቴዎድሮስ የወንድም ልጅ ጋረድ ክንፉ ከነአገው ንጉሤ ጋር በመተባበር አመጸ።

ጋረድ፣ በወገራ፣ ቆላ ወገራ፣ ደባርቅና ጠለምት ያሉትን የቴዎድሮስን ሹሞች ወግቶ ድል በመንሳት አካባቢውን ተቆጣጠረ። ከአገው ተሰማ ጋር ሆኖ፣ ደንቢያ ውስጥ ጭሕራ ባሕሪ ግንብ እየተባለ ከሚጠራው ቀበሌ ከባላምባራስ ገልሞና ከአፍንጮ እንግዳ ጋር ጦርነት ገጥሞ ድል በማድረግ፣ በደንቢያ ላይ ደጃዝማች መኮንን ሹመኛው አድርጎ ሾመ። የቴዎድሮስ ሹመኛ ይመር ንጉሤ፣ ከጋረድ ጋር አንቃሽ ላይ ጦርነት ገጥሞ ይመር ንጉሤ ድል ሆኖ ተገደለ። ጋረድ በዚህም ላይ አላቆመም። ፕላውደን የተባለው የእንግሊዝ ቆንስል ታሞ ለሕክምና ከቴዎድሮስ አስፈቅዶ ወደ አገሩ ሲጓዝ ሰሜን፣ ሊማሊሞ ጋራ ሥር ድብባሕር ከተባለው ቦታ ላይ ይዞ ጥር ወር 1853 ዓም ገደለው።(ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣1996፣139—140)

ይህ ሁኔታ ያሳሰባቸው ቴዎድሮስ የሸዋን ዘመቻ አቋርጠው ወደ ጎንደር ጉዞ ጀመሩ። የቴዎድሮስን መመለስ የሰሙት ደጋፊዎቻቸው፣ ባላምባራስ ገለሞና አፍንጮ እንግዳ ኃይላቸውን በማስተባበር በነርሱ ላይ ጋረድ የሾመውን ደጃዝማች መኮንን ገጥመው ድል በመንሳት ገድለው በግዛታቸው ላይ የበላይነታቸውን አረጋገጡ። በዚህ የድል ዜና የተባራቱት ቴዎድሮስ ጋረድን ለማደን ጎንደር በሰላም ገቡ። ቴዎድሮስ ጋረድን ለማደን ያደረጉት ጥረት ሰመረ። ጋረድ ሊማሊሞ ጋር ሥር ጨው በር የመሸገ መሆኑን ደረሱበት። በመሆኑም በወርሃ ጥቅምት 1854 ዓም የቴዎድሮስና የጋረድ ጦር ጨው በር ላይ አይቀሬውን ጦርነት ፊት ለፊት ገጠሙ። ሁለቱም ጀግንነት በደማቸው የሰረጸ ነውና የበላይነቱን ለመቀዳጀት የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ። ጋረድ የአጎቱን ጀግንነት፣ ከአዳኝነት እስከ ጦር ግንባር ያለውን ጠንቅቆ የሚያውቅ በመሆኑ፣ በጋለው ጦርነት ውስጥ ተሸሎክሉኮ በመሄድ ቴዎድሮስን ቀድሞ ለመግደል ሲያልም፣ አኳኋኑን ቀድሞ ያየው የቴዎድሮስ ወዳጅ እንግሊዛዊው ቤል፤ ተሽቀዳድሞ በሽጉጥ ጋረድን መትቶ ጣለው።

የጋረድን አሟሟት እና ማን እንደገደለው ከጎኑ ሆኖ ያይ የነበረው የጋረድ ወንድም ወዲያውኑ ቤልን ገደለው። የጋረድ መሞት የጦርነቱን ፍፃሜ አበሰረ። ቴዎድሮስ ጦርነቱን በድል ቢቋጩትም፣ የፕላውደን እና ከሁሉም በላይ የቤል መገደል የእግር እሳት ሆነባቸው። ለዚህም በጋረድ ተከታዮች ላይ የወሰዱት እርምጃ ከቂም በቀል የዘለለ ነበር። በመሆኑም ቴዎድሮስ፣ ከጋረድ ጋር ሆኖ የወጋቸውን የጋረድን ተከታይ ወታደር እጅና እግሩ እየተቆረጠ ደባርቅ ገበያ እንዲሰቀል አዘዙ።( እንደላይኛው፣ 141) ከዚህ ላይ ቴዎድሮስ ሁለት ፍርድ ፈረዱ፤ የአካል ቅጣት፣ ከዚህ ላይ ሥቅላት። የሚፈለገው ሰዎቹን መግደል ከሆነ ሥቅላቱ በቂ በሆነ ነበር። ቴዎድሮስ ከቆሙበት ቦታ ቆሞ ላላየ ሰው ድርጊቱን አረመኔአዊ ሊለው እንደሚችል መገመት ይቻላል። ከዓላማው አንፃር ሲታይ ደግሞ ከዚህ የተሻለ አማራጭ ለጊዜው ለቴዎድሮስ አልታያቸውም። ነባራዊ ሁኔታውም ሁሉም የሚጋሩት በመሆኑ፣ ቴዎድሮስን ከዚያ ነጥሎ ማየት ያስቸግራል።

ይህ ጦርነት ሕዝቡን ያሳሰበ ስለነበር የጋረድን ሞት ተከትሎ እንዲህ ተገጠመ፣

> **« ጋረድ ሞተ እንኳን ተቀበረ፣**
>
> **ያንተ ወንድም ነውና እፈርው እንፈራው ነበረ፤»**

የጋረድ አጋሮች ሆነው በቴዎድሮስ አገዛዝ ላይ ያመጹት በተለምዶ አገው ንጉሤና አገው ተሰማ (ተሰማ ሣህሉ) የሚባሉት ናቸው። ንጉሤ አባቱ የአገው ተወላጅ የሆነው ወልደሚካኤል ሲሆን፣ እናቱ የደጃዝማች ውቤ እናት የወይዘሮ ምንትዋብ እህት የሚወለዱ ናቸው። አገው ተሰማ የተባለውም የንጉሤ ወንድም ነው። አገው ንጉሤ ከጋረድ ጋር ተባብሮ በሰሜንና በጎንደር አካባቢ ያሉትን የቴዎድሮስን ሹሞች ድል ነስቶ ራሱን ደጃዝማች ነኝ ብሎ ሾሚል። ቴዎድሮስ ጋረድን ድል ከነሱ በኋላ ትኩረታቸውን በንጉሤ ላይ አደረጉ። በመሆኑም ወደ ትግሬ ዘምተው ወንድማማቾቹን ደጃዝማች ንጉሤ ወልደሚካኤልንና ተሰማ ሣህሉን ገጠሙ። በዚህ ጦርነት ንጉሤ ተማረከ። ንጉሤ ተማርኮ ቴዎድሮስ ፊት እንደቀረበ፣ በፈጸመው ክህደት እጅና እግሩ ተቆርጦ በስቅላት እንዲገደል ተወሰኖ ይኸው ተግባራዊ ሆኖበታል።

ወንድሙ ተሰማ ሲሸሽ ተንምቤን ላይ ተይዞ እጅ እግሩ ተቆርጦ በስቅላት እንዲሞት ተደርጓል። የሁለቱ አጋር የነበረው ብሩ አባ ደራ የተባለው እጄን አልሰጥም ብሎ ሽጉጡን ጠጥቶ ሞተ። ይህ የብሩ አባደራ አሟሟት ለቴዎድሮስ ሲነገራቸው፣ **«ቆማጣ ቆመጥማጣ፣ ከእኔ ልብ ያለውን ማን ነገረው?»** ብለው በጀግንነት አሟሟቱ ተደንቀዋል። ጀግና ለጀግና አድራጎት ዋጋ ይሰጣልና!

ደጃዝማች ንጉሤ የቴዎድሮስን የአካል ቅጣት አጥብቆ የሚጠላ ነበር ይባላል። በመሆኑም በቴዎድሮስ ላይ አምጾ በእርሱ ሥር ይተዳደር ከነበረው የትግሬ እና የሰሜን አካባቢ ነዋሪ የሆነ ግለሰብ ጥፋት አጥፍቶ ለፍርድ ከእሱ ዘንድ ሲቀርብ፤« እባክህ ወዳጄ እጅና እግር በዝናብ አይበቅልም፤ ግረፍና ልቀቀው» እንዳለ ይነገርለታል። (እንደላይኛው 159-160)

ቴዎድሮስ ንጉሤንና ተሰማን ድል ነስተው የሕይዎታቸውን ፍፃሜ ካረጋገጡ በኋላ፣ተከታያቸው የነበረውን፣ የትግሬ ሕዝብ አክሱምና በየአካባቢው ባለው ገዳም እየገባ ደወል እየደወለ እንዲጠብቅ አዋጅ አስነገሩ። በዚህ መሠረት የተሰበሰበውን የንጉሤ ተከታይ የነበረውን ሰው፣ በነፍጥና በሰይፍ እንዲደበደብ አድርገው በትግሬና በሰሜን ላይ ጊዜአዊ የበላይነታቸውን አረጋግጠው በድል ተመልሰዋል። ይህ ግን ቴዎድሮስ አንድነትን ለማምጣት የድል መሠረት ከጣሉበት ከአይሻልና ከደርጌ ጦርነት ጋር ሲነፃፀር፣ ለውድቀት ጉዞአቸው መንሸራተት ከፍተኛ ድጥ ያሚለጩበት ሆኖ የሚታይ ነው። ምክንያቱም እርሳቸውን ሊወጋ የመጣው በጀኔራል ናፒየር የተመራው የእንግሊዝ ጦር የመረጃ፣ የሥንቅ፣ የመጓጓዣ እና የሰው ኃይል የተጠናከረ ድጋፍ ያገኘው ከትግሬ ሕዝብ ዘንድ መሆኑን ስንገነዘብ፣ ይህ በደጃዝማች ንጉሤ ተከታይ የትግሬ ሕዝብ ላይ የወሰዱት ርምጃ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።

### 9.5 የሜጫና አገው ምድር ገዥ ደጃዝማች ብሩ በቴዎድሮስ ላይ ማመጽ፣

ደጃዝማች ብሩ የሜጫና አገው ምድር ገዥ በቴዎድሮስ ላይ አመፀ። አሚፀኛውን ለማስገበር ቴዎድሮስ በገብርዬ የሚመራ ጦር ላኩ። ለጦሩ ግን አንድ ጥብቅ መመሪያ ሰጡ። እንዲህ የሚል። «እኔ ሳልደርስ ጦርነት እንዳትከፍቱ » የሚል። ሆኖም ገብሬ ተክሉ የተባለው ስማዬ፣ የገብርዬ ጭፍራ መመሪያውን ጥሶ፣ ቴዎድሮስ ጦርነት ወደ ሚደረግበት ቦታ ሳይደርሱና ጦሩም እንዲዋጋ መመሪያ ከመስጠታቸው በፊት ቀድሞ ጦርነት ጀመረ። ጦርነቱን ለመጀመር ምክንያት ያደረገውም « የጦርነት ድግሥ ለጌታየ አላቀይም» የሚል ነው። ገብርየም የጦርነቱ አጀማመር ከተሰጠው መመሪያ ውጭ መሆኑን ቢያምንም፣ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ማስቆም መልካም ሊሆን እንደማይችል በማመን በጦርነቱ ቀጠለ። ድሉም ለገብርዬ ሆነ።

ከድሉ በኋላ ቴዎድሮስ ደርሰው፣« እኔ ሳልደርስ ጦርነት እንዳይጀመር ትዕዛዝ ሰጥቸ አልነበር? » ሲሉ ገብርየን ጠየቁ። ገብርየም ለቀረበለት ጥያቄ፣ አዎ! ጃንሆይ፣ ግን ገብሬ ተክሉ «ለጌታዬ የጦር ድግስ አላቆይም» ብሎ ጀመረው። እኛም ከተጀመረ ብለን ገፋንበት ሲል መለሰ። በገብሬ ተክሉ አባባል ልባቸው በደስታ የተሞላው ቴዎድሮስ፣ ገብሬን አስጠርተው፣ «ምን ውለታ ውለንሃል?» ቢሉት፣ «ባለቤኔቻ ጥሩ ፈረስ ሸልመውኛል» ሲል የተዋለልትን ተናገረ። ቴዎድሮስ መልሰው «ራስ ብየሃለሁ» ብለው « የራሳቸውን ወርቅ ወለባ አውልቀው ከራሱ ሰኩለት።» ይህ ቴዎድሮስ ላገራቸው በታማኝነት ለሚያገለግሉና ለጀግኖች ያላቸውን ክብር በዚህ መልክ ይገልጹት እንደነበር ማሳያ ነው።(ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣1996፣ 162)

**ምዕራፍ ስድስት፤**

**10 የቴዎድሮስ ሥብዕና**

**10.1 የቴዎድሮስ ነገሮችን ፈጥኖ የመረዳት ችሎታና ብልኅነት።**

ቴዎድሮስ ነገሮችን ከሩቅ የመመልከት፣ የነገሮችን ፍሬ ነገር ፈጥኖ የመረዳት ችሎታ የነበራቸው መሪ ነበሩ። ይህ ችሎታቸው ጎልቶ ከታየባቸው አጋጣሚዎች ውስጥ የሚከተሉት ለአብነት የሚጠሰቁ ናቸው። የዘመኑ ደብተራዎችና አዝማሪዎች የሚወዱትንና የሚጠሉት ሰው፣ በውስጠ ወይራ፣ በቅኔ፣ በዝግሬ ማሸሚጠጥና ማሞገስ የችሎታቸው ዓይነተኛ መገለጫ ነበር። ዛሬም ፈጽሞ የጠፋ አይደለም። በዚህም መሠረት ቴዎድሮስ በዘመናቸው የነበሩ ደብተሮች በልዩ ልዩ መንገዶች አሞግሰዋቸዋል። አሸሚጠዋቸዋል።

1. ቴዎድሮስ ካህናቱ ንግሥናቸውን ላለመቀበል በወሰዱት አቋም የተነሳ፣ የቀሳውስቱ የመተዳደሪያ የነበረውን «የሪም መሬት» ቀምተው የመንግሥት ማድረጋቸው ይታወቃል። በዚህም ካህናቱ በቴዎድሮስ ላይ ቂም ቋጥረዋል። አለቃ ፋንታዬ የተባሉ የፍትሐ-ነገሥት ተርጓሚ ነበሩ። አለቃ ፋንታዬ ከቴዎድሮስ የ50 ብር ደመወዝተኛ ናቸው። ቴዎድሮስ ለፋንታዬ ደመወዛቸውን እንዲከፈሉ ካደረጉ በኋላ እንዲህ የሚል ምክር ይለግሷቸዋል። በደመወዘዎ « ብሉበት፣ ጠጡበት፣ እናንተ የምታውቁት የምንሰጣችሁን ደመወዝ ከመሬት መቅበር ነው፤ይህ ዓይነት ልማድ አይጠቅምም፤ መቼ እንደምንሞት አናውቅምና እንሥራበት» ይሏቸዋል። አለቃ ፋንታ ነገሩን ወደሌላ አዙረው፣ «ጃንሆይ! የት እናደርሰዋለን ብለው ነው? መሬቱስ ቢሆን በእጇዎ አይደል!» የሚል መሬቱን ቀምተውናል ፣ መሬቱም የርሰዎ ነው፣ እኛ መሬት የለንም የሚል አግቦአዊ መልስ ይሰጣሉ። ቴዎድሮስ ነገሩ ምን ማለት እንደሆነ አውቀውና ታዝበው ምን ሳይሏቸው ቀሩ።
2. ቴዎድሮስ የጠላት ከበባ ሲበዛባቸው ካህናቱን ሰብስበው፣አገራችን የሚወር ጠላት በአራት ገጽ(አቅጣጫ) መጥቷል። በሦስት ገጽ በኩል የመጣውን እኔና ገብርዬ እንመልሰዋለን። አራተኛውን ገጽ እናንተ ወግታችሁ መልሱልኝ፤ በዚህ በኩል ባይሆን እርዱኝ፤ መሬታችንን ያዘብን እያላችሁ ብታማርሩኝ የሚጠቅም አይደለም። መሬት የሚገኘው ደም በማፍሰስ ነው አሉዋቸው። ካህናቱ ከቴዎድሮስ ለቀረበላቸው ጠላትን ተባብረን እንዋጋ ለሚለው ጥሪ የሰጡት መልስ እንዲህ የሚል ሆነ። «እኛ ዕቀበ ንግሥ ወሠራዊት ለንጉሥነ ቴዎድሮስ» እያልን በጸሎት እንዋጋለን እንጂ፣ካባት ያልቆየ ሕግ ለምን ይተክሉብናል(ተዋጉ ይሉናል)፤ እንዴትስ ካህን ይዘምታል? በማለት የዘመቻውን ጥሪውን ይቃወማሉ። ቴዎድሮስ ለዚህ የካህናቱ እምቢታ «እንግዳውስ መሬት በእጇ» ብለው ካህናቱን ያሰናብታሉ። ከዚህ በኋላ የፍትሐ ነገሥቱን ሊቅ አለቃ ፋንታን አስጠርተው « ደብተራ ጠግቦ ዝመት ቢሉት አይዘምትም፣ እንዲያውም በከንቱ ያደክመኛል» እያሉ አዋዩዋቸው። አለቃ ፋንታዬ አንስተው፣ « እርግጥ ነው ጃንሆይ! ደብተራ ያለቅጥ ጠግቦ መሬት ለቆ!» የሚል ለሁለተኛ ጊዜ ደብተራው መሬቱን በቴዎድሮስ ተቀምቷል የሚል ትርጉም ያለው መልስ ይሰጧቸዋል። የዚህን መልስ ትርጉም የተረዱት ቴዎድሮስ አሁንም ምንም ሳይሉ አለቃ ፋንታን አሰናበቱ፣
3. ቴዎድሮስ ከታቦቱ ሁሉ የሚወዱት መድኃኒዓለምን ነው። በዚህም ምክንያት የደብረታቦሩን መድኃኒዓለም ያሠሩ እርሳቸው ናቸው። ጽላቱን ያስመጡት ከአዴት መድኃኒዓለም ነው። ቤተክርስቲያኑ ታንጾ እንደተጠናቀቀ፣ መጋቢት 27 ቀን ጽላቱ(ታቦቱ) ገባ። በዐፄ ኢያሱ ለደብረ ብርሃን ሥላሴ የተበረከተውን ደወል በሰው ጉልበት አሸክመው ለደብረታቦር መድኃኒዓለም እንዲሰጥ አድርገዋል። ይህ እንደተከናወነ፣ ቴዎድሮስ ለሁለት ተከታታይ ጊዜ በቅኔ ሥራዎቻቸውን የሚያጣጥሉ መልስ የሰጧቸውን አለቃ ፋንታን አስጠርተው፣ ስለቤተክርስቲያኑ ሥራ አስተያየታቸውን እንዲሰጡዋቸው ጠየቋቸው። አለቃ ፋንታም ተዘዋውረው ካዩ በኋላ፣« አዎ ! ጃንሆይ፣ በቂ ነው፣ ለአምስት ልዑካን ይበቃል» አሏቸው። ይህ የተለመደ ሽሙጣቸው ቴዎድሮስ የቤተክርስቲያኑ መንፈሳዊ አገልግሎት በሁለት ቄስና በሦስት ዲያቆን ይሰጥ ብለው የወሰኑትን የሚያቃልል ምጸት በመሆኑ፣ ካለፉት ሁለት ትችቶቻቸው ጋር ተዳምሮ የቴዎድሮስን ትዕግሥት የተፈታተነ በመሆኑ፣ እንዳለፉት ሁሉ በትዕግሥት ሊያልፏቸው

አልወደዱም። በመሆኑም፣ «አንተ ደብተራ ዛሬ ተገናኘን» ካሉ በኋላ የጦር አለቃውን አስጠርተው፣ ገበያው ሳይፈታ ግራሪያ ገበያ ላይ ስቀሉት ብለው ትዕዛዝ ሰጥተው የአለቃ ፋንታ ሕይዎት ፍጻሜ እንዲሆን አድርገዋል።

4. ቴዎድሮስ እንደባህል ሆኖ፣ በርካታ ቁባቶች ነበሯቸው። ከቁባቶቻቸው መካከል አንዷ ደንቢያ ውስጥ ትኖር የነበረችው ጓሩት የምትባለዋ ነበረች። ይህች ሴት ከቴዎድሮስ ለመሰወር ብላ ጣና ሐይቅ «ደቅ» ደሴት ውስጥ ገብታ ትደበቃለች። ቴዎድሮስ አፈላልገው ሊያገኟት አልቻሉም ነበር። ሆኖም ሴትዮዋ ደቅ ውስጥ መኖሯን የሰማ አዝማሪ፣ቴዎድሮስ በተገኙበት ቦታ እንዲህ በማለት ዘፈነ፤ « ወድቃ ተሰብራ ያለውሉ፣ ጓሩት ደቅ አለች አሉ፤» ይላል። ይህን ቴዎድሮስ እንደሰሙ፣ ወይጦውን አዘው በታንኳ ጓሩትን ከተደበቀችበት እንድትመጣ አድርገዋል። ( ከላይ ከ1 እስከ 4 ተራ ቁጥር ለተጠቀሱት ምንጭ ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣ 1996፣ 82-84)

**10.2 የቴዎድሮስ ለዕውነት የመቆም ባሕሪይ፣**

ማንም ሰው ለዕውነት የቆመና ለዕውነት እንደሚሞት ባፉ መናገሩ የተለመደ ነው። ቴዎድሮስ ለሐቅና ለዕውነት የተለየ ትርጉና ዋጋ የሚሰጡ ናቸው። ለዚህ አባባል ለአብነት ዕውነትን ለመፈለግ ያደረጉትን ጥረት ያሳያል። ነገሩ እንዲህ ነው። አንድ ከ10 ዓመት በላይ ያገለገላቸው ታማኝ አሽከራቸው፣ ይኸን ያህል ዓመት አገልግየዎ ከድህነት አላወጡኝም የሚል ስሞታ ያቀርብላቸዋል። እርሳቸውም፣ እኔን 10 ዓመታት አገልገልግሎ ከጓደኞቹ በታች የሆነበት ምክንያት ለማወቅ የራሳቸው የዕውነት ማግኛ ዘዴ ፈለጉ። ፈልገው ያገኙት ዘዴም ይህ ነው። ሁለት አገልግል አዘጋጁ። ባንደኛው አገልግል ብር ሞሉበት፤ ሁለተኛውን ባዶውን አደረጉና አሥር ዓመታት አገልግየ ደኸየሁ ያላቸውን አሽከራቸውን አስጠርተው፣ በል ከነዚህ አገልግሎች አንዱ ብር አለው፤ ሌላው ባዶ ነው፤ ብር የያዘውን የመረጥክ እንደሆን፣ እውነትም እኔ በድየኻለሁና የአገልግሎትክን ዋካ እክሳለሁ፤ ባዶውን የመረጥክ እንደሆነ፣ የበደለህ ዕድልህ ነውና እኔን አታማም ፤ ይሉና ቃል አስገብተው የፈለገውን አገልግል እንዲመርጥ ፈቀዱለት። እርሱ ግን ዕድሉ ይሁን አጋጣሚው የመረጠው ባዶውን ሆነ። ቴዎድሮስም በእድሉ እንዲያዝን እንጂ፤ እርሳቸውን እንዳይወቅስ አስጠንቅቀው እንዳሰናበቱት ታሪካቸው ያስረዳል።

ደጃዝማች ተድላ ጓሉን ለማስገበር ጎጃም የተደጋገመ ዘመቻ አድርገዋል። ተድላ ኃይሉን እያየ ሙተራ ጅብላ ተራራ እየገባ አልያዛቸው ይላል። ተድላን በዘዴ አዘናግተው ለመያዝ ፈለጉና የማሳሳቻ ዘመቻ አወጁ። አዋጁም የሚለው «ሸዋ ዘምቻለሁና ተከተሉኝ» የሚል ነው። ቴዎድሮስ ይህን በይፋ አስነግረው፣ እርሳቸው የተወሰነ ኃይላቸውን ይዘው ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ይኖሩበታል ተብሎ ወደ ሚገመተው ዘመቱ። በደረሱበት አንድ ቤት ገብተው ባለቤቷን ምግብ እንድትሰጣቸው ጠየቋት። ባለቤቷም ምግቡን አቅርባላቸው እየተመገቡ ሳለ፣ የማን ወታደሮች እንደሆኑ ጠየቀቻቸው። ቴዎድሮስም የደጃዝማች ተድላ ጓሉ መሆናቸውን ነገሯት። አያይዘውም «ይህ ዕብድ ንጉሥ ወዴት ሄደ ይባላል?» ሲሉ ጠየቋት። ሴትዮዋ ወይ በተፈጥሮ አዋቂ፣ ወይም ሃይማኖተ ጥኑ መሆን አለባት፣ ለጠየቋት ጥያቄ የሰጠችው መልስ፣« ዕብድስ እናንተ፤ እግዜር ቀብቶ ያነገሠውን ንጉሥ  ዕብድ ይባላል እንዴ?» ብላ መለሰችላቸው።  በዚህም የሕዝቡን ሥነልቦና ለመረዳት እንደቻሉ መገንዘብ ይቻላል።

ቴዎድሮስ ጎጃምን፣ ቤጌምድርን፣ ስሜንና ወሎን ለማስገበር ካንዱ ወዳንዱ ሲንከራተቱ፣ ወደ ትግራይ ሳይዘምቱ ቆይተው ነበር። በዚህም የተነሳ የትግሬ ባላባቶች፣« ተከዜን ከተሻገረ የመንግሥቱ ፍጻሜ ይሆናል» እያሉ ያስወሩ ስለነበር፣ ይህም ለቴዎድሮስ የተደበቀ ባለመሆኑ ተባለ የሚባለውን እንደ ሰው ሁሉ ይሰሙታል።  ከመባል አልፎ በሕዝቡ የሚነገር፣ እንዲህ የሚል በትግሬዎች በኩል ተገጥሞ ይነገር ነበር።

**« የዐባይነን ውኃ በቅል ይጠጡታል፤**

**የተከዜን ውኃ ለምን ይፈሩታል? »**

ይህ በትግሬ ባላባቶች የሚነገረው ነገር ውሸት መሆኑን ለማሳየት፣ ትግሬን ለማስገበር ባደረጉት ጉዞ፣ ተከዜ ወንዝ ሲደርሱ «ከወራጁ ውኃ በጎሽ ዋንጫ አስቀድተው ጠጡ።» ቀጥሎም  አብተው የተባለውን ዓለም አጫዋች (አዝማሪ) አስጠርተው ትግሬዎቹ ላሉት ማርከሻ የሚሆን ግጥም እንዲህ በል አሉት፤

**«ተከዜን ሲሻገር ይሞታል እያሉ፤**

**መጽሐፉ ታጠበ ያባይ ጠንቋይ ሁሉ፣**

**ወርሒን ስንደግመው እንግዲህ ምን ይሉ?»** ወርሒ በትግራይ የሚገኝ ወንዝ ነው።

አብተው ከዚህ አከታትሎ እንዲህ ሲል ገዘመ።

**«በቴዎድሮስ የለም ጋሻ፣**

**ማረስ ይሻላል በማረሻ፤**

**ማረስ ይሻላል መገበር፣**

**እጅ እግር ይዞ ለመኖር፤**

**አላርስም ያሉ አልነገድ፣**

**ተመለመሉ እንደ ግንድ።»**

ቴዎድሮስ ለፍትሕና ለዕኩልነት የቆሙ ሰው ነበሩ። በ1850 ዓም ጎጃም ዘምተው በነበረበት ወቅት ባሶ ገባያን ጎበኙ። ባሶ በዚያን ጊዜ ከነበሩት የንግድ መስመሮችና የባርያ ገበያዎች አንዱ የነበረ ነው። በዚህ ገበያ ለሽያጭ የቀረቡ በርካታ «ባርያዎችን» አገኙ። ሁኔታው ያሳዘናቸው ቴዎድሮስ፣ ሁሉንም በነፃ እንዲለቀቁ ካደረጉ በኋላ ወደፊትም የባርያ ሽያጭ እንዲቀር አዋጅ አስነገሩ። ይህ አዋጅ ካስነገሩ በኋላ ነፃነት ያጎናጸፏቸውን ባሮች አስከትለው ጉዞ ወደ ቤጌምድር አደረጉ። ጋይንት ውስጥ ጉና ተራራ ሥር ባደረጉት ሠፈራ፣ ከባሶ ገበያ አብረዋቸው የመጡትን ባርያዎች ሰብስበው «እያንዳንዱ ከመካከሉ የወደዳትን እንዲያገባ፣ እንድታገባ» ፈቀዱ። ከነበሩት ባሮች አንዷን ለወዳጃቸው እንግሊዛዊ ቤል(ዮሐንስ) ለሁሉቱም ራሳቸው አባት ሆነው ኢጋብተዋል።(ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣ 1996፣ 117) ለፍትሕና ለዕኩልነት መቆም ከዚህ የተሻለ በምን ይገለጻል?

ቴዎድሮስ በ1850 ዓም ላይ ጋይንት አውራጃ ዙርአምባ ማርያም አምባ ላይ ሠፍረው በነበረበት ወቅት፣ ሠራዊታቸው በገበሬው ቤት ተመርቶ እንዲኖር አደረጉ። ሆኖም ሰው ከሰው ሲገናኝ ጠባዩ ለየቅል በመሆኑ፣ አንዱ ተሠሪ የቴዎድሮስ ወታደር፣ የተሠራበትን ገበሬ ገደለው። የሚች ወገኖች ለቴዎድሮስ አቤቱታ አቀረቡ። አቤቱታ የቀረበላቸው ቴዎድሮስ፣ ወታደሩን ሰብስበው፣ የገዳዩን እንዲያወጣ ጠየቁ፡ አዘዙ። ወታደሩ ግን ባንድ ድምፅ ገዳዩን አናውቅም የሚል መልስ ሰጠ። ይህ ለቴዎድሮስ ፍትሕ አሰጣጥ አጣብቂኝ ውስጥ ያስገባ ሆነ። ቴዎድሮስ ግን የፍትሕ ሰው በመሆናቸው ፍትሕ ጠያቂዎቹ ያለበቂ መልስ እንዲመለሱ አልፈለጉም። በመሆንም፣ ወታደሩ የገዳዩን ማንነት አላውቅም ካለ፣ በየገበሬው ቤት ተሠርቶ እንዲኖር ያደረኩ እኔ፣ «ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ» የሚል ትዕዛዝ የሰጡሁ እኔ ስለሆንኩ፣ «ደመኛችሁ እኔ ነኝና ግደሉኝ፤» ሲሉ ለአቤቱታ አቅራቢዎቹ መለሱ።

አቤቱታ አቅራቢዎቹ ከቴዎድሮስ ለቀረበላቸው የእኔን ግደሉ መልስ አዳምጠው፣ «እኛ እግዚአብሔር የቀባውን ንጉሥ እንዴት እንገድላለን?» የሚል መልስ ሰጡ። አቤቱታ አቅራቢዎቹ በሰጡት መልስ የተደሰቱት ቴዎድሮስ፣ አመስግነው፣ የደም ካሣ ከፍተኛ ገንዘብ ሰጥተው የሚችን ዘመዶች እንባ በማበስ ፍትሕ እንዲያገኙ ማድረጋቸው በዚያን ጊዜ ቀርቶ ዛሬ ይደረጋል የማይባል ነው። በ1997 ምርጫ ላለቁ ወገኖቻችን ተጠያቂዎች ለፍትሕ አልቀረቡም። የሚች ወገኖችም የደም ካሣ አላገኙም። ባጭሩ ወያኔ ለ25 ዓመታት ለጨረሳቸው ሰዎች ኃላፊነት አለመውሰዱን ስናይ፣ ቴዎድሮስ ያለጊዜው የተፈጠሩ የፍትሕ፣ የዕውነት፣ የነፃነትና የዕኩልነት ሰው እንደነበሩ መገንዘብ ይቻላል።

**10.3 ቴዎድሮስ የጭካኔ እርምጃ የሚወስዱባቸው ምክንያቶች፥**

ዳግማዊ ቴዎድሮስ በተቃዋሚዎቻቸው ላይ የጭካኔ ርምጃዎች እንደወሰዱ በየጦር ግንባሩ በአካል ቅጣት የተቀጡት ሰዎች ማንነት ያሳያል። የጭካኔ ርምጃዎቻቸው መነሻ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ለሰው ሕይዎት የማያስቡ ፍፁም ጨካኝ ስለሆኑ ነው? ወይስ ለዚህ የዳረጓቸው ሌሎች ምክንያቶች መኖር ነው? ብሎ ጠይቆ ዕውነተኛውን ምክንያት መረዳት የቴዎድሮስን ሥብዕና ለመረዳት ያስችላል። ምንም ተባለ ምንም የቴዎድሮስ ጠላቶች ርምጃዎቹን ከቴዎድሮስ ተፈጥሮአዊ ባሕሪ ጋር በማያያዝ ጨካኝ ስለሆኑ ነው ሊሉ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል። የቴዎድሮስ ሥብዕናና ማንነት የሚለካው ግን፣ በጠላቶቻቸው በሚሰጡት ምስክርነት ሳይሆን፣ በዚያን ጊዜ ከነበረው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታና እርሳቸው አልመውት ከተነሱት አገራዊ ራዕይ ጋር በማነፃጸር ነው።

ቴዎድሮስ በተፈጥሮ ባሕሪያቸው ርኅሩኅ ናቸው። ለድሀዎች አሳቢ እና ለሰው ልጅ ዕኩልነት የቆሙ መሆናቸው በወሰዱዋቸው ተጨባጭ ርምጃዎች አሳይተዋል። በሽፍትነታቸው ዘመን፣ነጋዴውን እየዘረፉ ለደሃው ገበሬ የተግባር መገልገያ መሣሪያዎች እንዲገዛ ገንዘብ አከፋፍለዋል። ወታደሮቻቸው የደሀውን ገበሬ ኑሮ እንዳያበሳቁሉ ቋሚ መተዳደሪያ ደመወዝ ቆርጠው ሰጥተዋል። ራሳቸውን ከድሎት አርቀው ደሀው ገበሬ የሚሠራውን ሥራ በመሥራት ራሳቸውን ይረዱ ነበር። ማናቸውንም ሥራ በአካል ሠርተው የሚያሳዩ እንጂ፣ ሠርታችሁ አቅርቡ የሚሉ አልነበሩም።

በጦርነት ጊዜ ቀድመው ገፈታውን የሚጎነጩ እንጂ፣ ከኋላ ሆነው ሂድ ሙት የሚሉ አልነበሩም። ለቃላቸው የሚሞቱ ሐቀኛና ሃይማኖተኛ ነበሩ። ለዚህ በሽፍትነታቸው ጊዜ ስምምነት ገብተው ውሉን ባፈረሱት ሽፍቶች ላይ የወሰዱት ርምጃ ጉልህ ማሳያ ነው። ባሶ ገበያ ላይ ለሽይጭ ቀርበው የነበሩ ባሮችን ነፃ ለቀው ርስ በርሳቸው በፍላጎታቸው እንዲጋቡ ያደረጉትና አንዷን ለወዳጃቸው ለቤል ለሁለቱም አባት ሆነው ማጋባታቸው በሰው ልጅ ዕኩልነት የነበራቸውን ፍፁም እምነት ያሳያል። ፍርድ ሲሰጡ ፍትሐ-ነገሥቱ በሚደነግገው መሠረት የሚመለከታቸው ተወያይተው የጥፋተኝነት ውሣኔ ሳያሰልፉ፣ በግል ተነሳሽነት ውሣኔ አለመስጠታቸው ለሕግና ለፍትሕ የቆሙ መሆኑን ማሳያ ነው።

ይኽ ሁሉም ሆኖ ግን፣ ቴዎድሮስ ጭካኔ የተሞላባቸው የአካል ቅጣትና የስቅላት ቅጣቶችን በተናጠል ወይም ሁሉንም በመቀላቀል ወስነዋል። ለምን? የሚለው ጥያቄ የሚከተሉትን መልሶች እናገኛለን። ቴዎድሮስ ጭካኔ የተሞላባቸው ርምጃዎች የወሰዱት በሚከተሉት ምክንያቶች መደራረብ የተነሳ እንደሆነ በርካታ የታሪክ ተመራማሪዎች ይስማማሉ። እነዚህም፡-

1. ቴዎድሮስ በተቃዋሚዎቻቸው ላይ ጭካኔ የተሞላበት ርምጃ እንዲወስዱ ካስገደዱዋቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው ተቃዋሚዎቻቸው የመሠረቱትን አዲስ የማዕከላዊ ሥልጣን አንቀበልም በማለት ያደረጉት እልህ አስጨራሽ በጦርነት የታገዘ አመጽ ነው። ወሎ የወርቂት አመጽ፣ የዐመዴ በሽር አመጽ፣ የሸዋ የልጅ ሰይፉ ሣህለሥላሴ አመጽ፤ ጎንደር የጋረድ አመጽ፣ ትግሬ የደጃዝማች ንጉሤ አመጽ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።
2. ቴዎድሮስ በአካባቢ ባላባቶችና መሣፍንቶች ተከፋፍላ ሕዝቡ የመከራ ሕይወት የሚገፋባትን ጥንታዊት አገር፣ ወደ ጥንቱ አንድነቷ መልሰው የበለፀገች፣ የታፈረችና የተከበረች አንዲት ኢትዮጵያን የማየት ራዕይ ሰንቀው የተነሱ ንጉሠ-ነገሥት ናቸው። ለዚህም ገና ከጅምሩ አካባቢያዊ ገዥዎችን በመሣሪያ ኃይል ገርተው፣ ማናቸውንም የመገንጠል አዝማሚያ ከጥንስሱ እየቀጩ የመጡ ናቸው። በሌላ በኩል ተቃዋሚዎቻቸው ለዚህ ዓላማቸው ተፃራሪ በመሆን በሚከፍቱባቸው ጦርነት፣ ያን ለመደምሰስ የሚወስዱት የአፀፋ መልስ ከተፈጥሮ ጭካኔ የሚመነጭ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያን አንድነት አረጋግጦ አገሪቱን የታፈረችና የበለጸገች ለማድረግ ካላቸው የጠነከረ የዓላማ ጽናትና ቁርጠኝነት የሚመነጭ ነው።
3. የቴዎድሮስ የኃይል ርምጃ ከተፈጥሮ ጭካኔ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑ ማሳያው ነጥብ፣ በአውሮፓ በመካከለኛው ዘመን የተነሱ የአገር አንድነት የመሠረቱ መሪዎች የተከተሉት መንገድ ከቴዎድሮስ የተለየ አለመሆን ነው። እነዚህ መሪዎች ሲወደሱ እንጂ፣ ሲወቀሱ አይሰማም። ቴዎድሮስን ከነዚህ የተለየ የጭካኔ ተግባር የፈጸሙ ስላልሆነ፣ የጭካኔአቸው ምንጭ የዓላማ ስፋትና ጥልቀት እንጂ፣ የተፈጥሮ አለመሆኑን በርካታዎች ይማማሉ።
4. ለቴዎድሮስ የአካል ቅጣት ውሳኔ ከነዚህ በተጨማሪ የሚያግዙ የወቅቱ ሃይማኖታዊ አመለካከትና የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ፍትሐ-ነገሥት የራሱን አስተዋጽኦ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። ቴዎድሮስ በአዛዛቸው አጥፊዎች ውሣኔ የሚሰጣቸው በፍትሐ ነገሥት ዐዋቂዎች፣ በፍርድ ሸንጎ ጥፋቱ ተዘርዝሮ ከተጣራ በኋላ ነው። ሕጋዊ ሥርዓትን ተከትሎ ነው። ውሣኔው በሕዝብ ድምፅ ጭምር የታገዘ የፍርድ ሂደት የተከተለ ነው። ይህም ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ፣ **« ነፍሳት ሁሉ በበላይ ላሉ ባለሥልጣኖች ይገዛ፣ ከእግዚአብሔር ካልተኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፤ ስለዚህ ባለሥልጣናትን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቃወማሉ።»** ( ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም 1996፣ 168) ይላል። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ለቴዎድሮስ የፍትሐ ነገሥት ተርጓሚዎችና ለራሳቸው አመራር መሠረት በመሆኑ ለቅጣቱ መከበድ የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።
5. በሌላ በኩል ቴዎድሮስ ለሚወስዷቸው የአካል ቅጣት ውሳኔዎች ከላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ ምክንያቶችን የሚያያባብሱ ሁኔታዎች መፈጠርም ተጨማሪ ምክንያቶች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል። ያመኑዋቸው ሰዎች መክዳትና በራሳቸው ላይ ማመጽ፣ የባለቤታቸው የተዋበች መሞትና እርሷን የሚተካ አጋር አለማግኘት ሁኔታዎች ያባባሱ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል።
6. ከዚህ በተረፈ የቴዎድሮስ የዘወትር ምኞት ሥልጣኔ፣ ዕድገትና አንድነት ነበር። ቴዎድሮስ ካንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚፈልጉት ገጸ በረከት፣ ታማኝነት፣ ታታሪነት፣ ሃይማኖተ ጽኑነት ብቻ ነበር። በሌላ በኩል በአገሪቱ ተንሰራፍተው የነበሩት ባላባታዊ ገዥዎች በሕዝቡና በአገሪቱ ላይ የጫኑት የመከራ ቀንበር እንዳይሰበር በየቦታው የከፈቱባቸውን ጦርነት በድል ለመወጣት ከኃይል የተሻለ አማራጭ በዚያን ጊዜ ከቅርብ የሚታይ መፍትሔ አልነበረም። ይህን ደግሞ ዓለም የተጓዘበት በመሆኑ ከቴዎድሮስ ሲደርስ የተለየ ሊሆን አይችልም። ቢስማርክ ጀርመንን፣ ጋሊ ባርዲ ጣሊያንን፣ ናፖሊዮን ፈረንሳይን አንድ ያደረጉት ቴዎድሮስ በተጓዘበት መንገድ ተጉዘው ነው። ይህም በመሆኑ ቴዎድሮስ የዘመናዊት ኢትዮጵያ አንድነት ፋና ወጊ ጀግና አባት የሆኑ የብሩኅ አዕምሮ፣ የሩቅ ራዕይ፣ የአንድነትና የሥላጣኔ ናፋቂ፣ ያንም በኢትዮጵያ ምድር ዕውን ሆኖ እንዲያዩ የሚጥሩ ንጉሠነገሥት ነበሩ። በመሆኑም ትውልዱ ሊመካባቸውና ሊኮራባቸው ከሚገባው መሪዎች አንዱ የነበሩ በመሆናቸው ዓላማና ራዕያቸውን የማስቀጠል ኃላፊነት የተከታዩ ትውልድ ነው።

**ምዕራፍ ስድስት፣**

**11 የዳግማዊ ቴዎድሮስ የተማከለ ዘማናዊ አስተዳደር ለመመሥረት የጣሉት መሠረትና በታሪክ ያላቸው ሚና፤**

**11.1 ቴዎድሮስ ለተማከለ ዘመናዊ አስተዳደር የጣሉት መሠረት፤**

ቴዎድሮስ፣ አንድነቷ የጠበቀ፣ የታፈረች፣ የተከበረችና የበለጸገች ኢትዮጵያን ማዬት ታላቁ ሕልማቸው ነበር። ለዚህ ሕልማቸው ዕውን መሆንም፣ የሰሜን ኢትዮጵያ ባላባታዊ መሣፍንቶች ተራ በተራ ድል ነስተው፣ ለማዕከላዊ አስተዳደር መመሥረ ምቹ የሆነ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ መሠረት ጠንካራ ማዕዘኖች የገነቡ ንጉሠ ነገሥት ናቸው። ከሁሉም በላይ ቴዎድሮስ የአንድ አገር ዕድገትና ሥልጣኔ በተከታታይነት ተጠብቆ ሊዘልቅ የሚችለው፣ ጠንካራ መከላከያ ኃይል ሲኖር መሆኑን ተገንዝበው፣ ይህን ዕውን ለማድረግ ሥራው የአገርን አንድነትና የሕዝብን ሰላም ማስከበር የሆነ የመከላከያ ሠራዊት እንዲገነባ መሠረት ጥለዋል። ሠራዊቱ የሚታጠቀው የጦር መሣሪያም በአገር ቤት መመረት እንዲችል መድፍን ያህል ነገር እንዲሠራ አድርገዋል። ለሕዝቡ አንድነት መጠንከር ሃይማኖት የሚጫወተውን ሚና ተረድተው፣ ሕዝቡ አንድ ሃይማኖት እንዲከተል ከአባ ሰላማ ጋር ስምምነት የፈጠሩ ናቸው። የአገሪቱን አስተዳደር በአውራጃዎች በመከፋፈል፣ ተጠሪነታቸው ለንጉሡ የሆኑ ባለሥላጣኖችን ሾመዋል። ወጥ የሆነ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ዘርግተዋል። በአጠቃላይ ዳግማዊ ቴዎድሮስ የአገሪቱን አንድነት በተማከለ ዘመናዊ አስተዳደር ለመምራት የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናወኑ የዘመናዊት ኢትዮጵያ መሥራች ንጉሠነገሥት ናቸው።

1. የአገሪቱን አንድነት አረጋግጦ፣ የበለጸገችና የተከበረች ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ የሃይማኖት አንድነት አስፈላጊ መሆኑን አምነው ፣ ከአቡነ ሰላማ ጋር መክረውና ተስማምተው ሕዝቡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆን ዓላማና ፍላጎታቸውን ገልጸዋል። ለዚህም የቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት በሁለት ቄሶችና በሦስት ዲያቆናት እንዲከናወን ደንግገው፣ የቀረው በልማት ሥራ ላይ እንዲሠማራ ያወጡት ሕግ እስከ ዛሬ ድርስ የሚሠራበት ሕግ ሆኗል።
2. የነበረውን የተበታተነ የአስተዳደር መዋቅር ሽረው፣ አገሪቱን በታናናሽ አውራጃዎች ከፋፍለው ፍፁም ታማኞቻቸው የሆኑትን በመሾም እንዲያስተዳድሩ አደረጉ፣
3. ዳግማዊ ቴዎድሮስ ላለሙት የአገር አንድነትና ብልጽግና የተማከለ የግር አከፋፈልና አወጣጥ የሚኖረውን ጠቀሜታ ተገንዝበው አዲስ የግብር አከፋፈል ሕግ አወጡ። የሚሰበሰበው ግብር እንደቀድሞው በየአካባቢው ላለው ባላባት ገቢ የሚሆን ሳይሆን፣ ወደ ማዕከላዊ የንጉሡ ግምጃ ቤት እንዲገባ አደረጉ። ይህም የመንግሥቱን አጠቃላይ ገቢ ለመቆጣጠር አስቻለ። ዕድገት የሚታቀደው በሚኖር ገቢ ላይ ተመሥርቶ ነውና፣ ይህ ለቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማዘመን ላቀዱት ዕቅድ ተፈጻሚነት የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ነው። ዘመናዊ አስተዳደርም ያለተማከለ ገቢ አሰባሰብና አወጣጥ የሚታሰብ አይሆንም።
4. ቴዎድሮስ የአገር አንድነትና ብልጽግና ያለጠንካራ መከላከያ ሠራዊት መኖር የማይታሰብ መሆኑን በመገንዘብ ቋሚ የመከላከያ ሠራዊት እንዲኖር መሠረት ጥለዋል። ሠራዊቱም ለኑሮው የሚሆነውን ገቢ የሚያገኘው እንደድሮው በገበሬው ላይ በመሠራት፣ ገበሬውን በመዝረፍና በመቀማት እንዳይሆን፣ ከመንግስት በጀት የሚከፈለው ቋሚ ደመወዝተኛ እንዲሆን አድርገዋል። ቴዎድሮስ ይህን ርምጃ በመውሰዳቸው ላለሙት ዓላማ መሳካት የሚከተሉትን ጥቅሞች አስገኝቷል። (1) ታዛዥነቱ ለንጉሠ ነግሥቱ ብቻ የሆነ ከፍተኛ ቁጥር ያለው በደመወዝ አዳሪ ሠራዊት እንዲኖራቸው አድርጓል፤ (2) በየሥፍራው ያለውን ተቀናቃኞቻቸውን የኢኮኖሚ አቅም በማዳከም ሕዝቡ ለንጉሠ ነገሥቱ ፍላጎት ተገዥ እንዲሆን ተጽዕኖ አሳድሮላቸዋል። (3) በገበሬው ላይ ይደርስ የነበረው የኢኮኖሚ ነጠቃና የሙብት ገፈፋ መጠነኛ የሆነ እፎይታ ሰጥቷል።(ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 260)
5. ቴዎድሮስ በሰዎች ዕኩልነትና ነፃነት የሚያምኑ በመሆናቸው የባርያን ንግድ አስቀርተዋል። የአገሪቱ ዜጎች በፈለጉት የሥራ መሥክ ተሰማርተው እንዲሠሩ የሚያስችል ደንብ አውጥተዋል። ለዕደጥበብ ሙያ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሙያተኞቹ እንዲከበሩና ሙያቸው እንዲስፋፋ የሚያስችል ደንብ አውጥተው ተግባራዊ እንዲሆን ጥረዋል። በየወንዙና በየበሩ የነበረውን የዝርፊያና የቅሚያ ወንጀል እንዲገታ አድርገዋል። « ነጋዴ ይነግድ፣ ገበሬ ይረስ፣ እያንዳንዱ ሰው በየሥራው ይሠማራ፤» ሲሉ ያወጡት አዋጅ የሥራን ክቡርነትና የብልጽግናም መሠረቱ ሥራ መሆኑን የተገነዘቡ መሪ ነበሩ። ቴዎድሮስ ይህን የሥራ አዋጅ እንዳስነገሩ የተወሰኑ ሰዎች ወደ ንጉሡ ቀርበው አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚቸገሩ አቤቱታ አሰሙ። ንጉሡም አቤቱታቸውን ካዳመጡ በኋላ ሥራቸው ምን እንደሆነ ጠየቋቸው። አቤቱታ አቅራቢዎቹም ፤ሥራቸው ዝርፊያና ቅሚያ መሆኑን ነገሯቸው። ቴዎድሮስ መልሰው በሉ ለአቤቱታችሁ ተገቢውን መልስ ለመስጠት እንዲቻል፣ « እንደናንተ ያለ፣ እናንተ ትሠሩት የነበረውን ዝርፊያና ቅሚያ የሚሠሩትን ሰብስባችሁ አምጡልኝ። ከዚያ በኋላ ምን እንደምትሠሩ እነግራችኋለሁ ብለው አሰናበቷቸው።--ወንበዴዎቹ እንደተነገሩት በዝርፊያ ይተዳደሩ የነበሩትን ዘራፊዎች ሁሉ ሰብስበው ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ።»

6. ቴዎድሮስ በዝርፊያ የሚስተዳደሩት ሰዎች መሆናቸውን አምነው ከፊታቸው ተሰባስበው የመጡትን ዘራፊዎች ሁሉም እንዲገደሉ አዘዙ። ይህ እርምጃ በአገሪቱ የንግድና የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ እንቅፋት የነበረውን በማስወድ፣ አንፃራዊ ሰላምና የንግድ እንቅስቃሴ እንዲሰፍን እንዳደረገ ይታመናል። ( እንደላይኛው፣ 261)
7. ቴዎድሮስ አገሪቱ በመንገድ እንድትያያዝ የመንገድ ሥራ ግንባታ አከናውነዋል። ለዚህም ከጋፋት (ደብረታቦር) እስከ መቅደላ (ወሎ) ድረስ ለሶባስቶፎል መጓጓዣ እንዲውል ማድረጋቸው ይታወቃል። ይህ የመንገድ ግንባታ ቴዎድሮስ ላሰቡት የአገር አንድነትና ብልጽግና መሠረት መሆኑን የተገነዘቡ እንደነበሩ ያሳያል።
8. ቴዎድሮስ ሕዝቡ እንደ መልካም ባህል የተቀበላቸውን መጥፎ ልማዶች በመልካም የሥራ ባህል ለመተካት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። አምረው ከተዋጓቸው በጥፎ ልማዶች መካከል፣ ዝርፊያ፣ ቅሚያ፣ ውሸት፣ ቅጥፈት፣ ባርያ ንግድ፣ አንድ ሰው ብዙ ቁባቶችን ማስቀመጥ የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ናቸው። ዝርፊያን ቅሚያን በቅጣት ከመዋጋታቸውም በላይ፣ የሥራ አዋጅ አውጀዋል። ብዙ ቁባቶች ማስቀመጥን በተመለከተ፣«ማንም ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ በአንዲት ሴት ብቻ መወሰን አለበት የሚል ሕግ አውጥተዋል» (ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም 2003፣ 262) ለተግባራዊነቱም ራሳቸውን ከቁባቶቻቸው ሁሉ በመራቅ ባንዲት ሴት ተውስነው ኖረዋል።
9. የቴዎድሮስ የዘውትር ምኞት ሥልጣኔ፣ ዕድገት እና አንድነት ነው። ላሰቡ ዕድገት፣ ሥልጣኔና አንድነት መጠናከር ደግሞ፣ ዕደጥበብ የሚጫወተውን ሚና ተረድተው ትውልዱ ብረት ማውጣት፣ ማቅለጥና መቀጥቀጥ፣ እንዲማር ፣ እንዲሁም መድፍ፣ ጠብመንጃ በኢትዮጵያ እንዲሠራ ጋፋት ላይ የብረት ማቅለጫ በመገንባት መድፍን ያህል ግዙፍ መሣሪያ አሠርተዋል። የዚህ ፍላጎታቸው ከፍተኛ መሆኑ ማሳያው፣ አንድ ወጣት ጀርመን አገር ሂዶ ለስድስት ዓመታት ተምሮ መጣ የሚል መረጃ ይደርሳቸዋል። ቴዎድሮስ ጀርመን አገር ድረስ ሂዶ 6 ዓመት ተምሮ የተመለሰ ሰው አለ መባሉ ስላስደሰታቸው ምን እንደተማረና በምን መልክ አገሩን ሊረዳ እንደሚችል ለማወቅ ሰውየው ወደርሳቸው እንዲመጣ አስጠሩት። የጀርመኑ ተማሪ ቀርቦ ምን እንደተማረ ሲጠይቁት፣ «ፍልስፍና» የሚል መልስ ሰጣቸው። ቴዎድሮስም መልሰው «ለዚህማ ስድስት ዓመት ሙሉ ለምን ደከምክ? ባገራችን ውስጥ ያለው የቤተክህነት ፍልስፍና በዝቶ አላሠራን ብሎ ተቸግረናል፣ » (ገሪማ ታፈረ 2ኛ ዕትም፣ 1996፣ 162-3) በማለት ተምሮት የመጣው የኢትዮጵያን ችግር የሚያቃልል ሳይሆን፣ በነበረው ችግር ላይ ተጨማሪ ችግር የሚፈጥር፣ የብጥብጥ ምንጭ ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ፣ ዳግም ዓይኑን ለማየት የማይፈልጉ መሆኑን ገልጸው ማሰናበታቸው ይታወቃል። ይህ የቴዎድሮስ አቋም ለተግባራዊ ሥራ እንጂ፣ ጊዜ ፈጅና አጨቃጫቂ ለሆነው ፍልስፍና ፍላጎት ያልነበራቸው እንደነበር ያሳያል። ይህ ደግሞ ሃይማኖት ፍልስፍና በመሆኑ ልዩነት በማራባት የገበሬውን የመሥራት አቅም ከማዳከም አልፎ፣ ወደ ጦርነት የሚያመራ፣ ልዩነቶችን የሚቀፈቅፍ፣ የፍልስፍናው አራማጆች የማይሠሩ፣ ኑሮአቸውን በአምራቹ ትከሻ ላይ የጫኑ በመሆናቸው አምረው ይጠሉ ነበር። በሌላ በኩል በፍልስፍናው ረገድ አገሪቱ መሸከም ከምትችለው በላይ ተፈላሳፊዎች ያሏት መሆኑን ቴዎድሮስ ያውቃሉ። በዚህም የተነሳ ሌላ ተጨማሪ ተጠዋሪ በሕዝቡ ትከሻ ላይ እንዲጫን አልፈለጉም።
10. ቴዎድሮስ ለሃይማኖታዊ ስብከት ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የውጭ ዜጎችን ሰብስበው ጋፋት እንዲኖሩ ከፈቀዱ በኋላ ፣እንዲህ አሏቸው፤« በአገሬ ውስጥ የሚያስፈልገኝ የወንጌል ሰባኪ ሳይሆን፣ የእጅ ሥራ የሚያውቅ ሰው ነው፤ የምትረዱኝ ወንጀል በመስበክ ብቻ የሆነ እንደሆነ፣ ባገሬ ብዙ ሊቃውንት፣ ካህናት ስላሉ፣ በዚህ በኩል ያለው አገልግሎት የሚያሳስብ ስላልሆነ፣ በእጅ ሥራ በኩል እርዱኝ፤» (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም ፣ 1996 165) በማለት የሰጡዋቸው ልመናን ያቀላቀል ትዕዛዝ፣ «ሹም ለመነ አዘዘ ነውና»፣ ፍላጎታቸው በእደጥበብ በኩል ትውልዱ እንዲበረታ ያላቸውን መሆኑን አጉልቶ ያሳያል። ዕውነት ነው፣ ብረትን አቅልጦ መገልገል ያልቻለ ትውልድ ሥልጣኔን ጨብጧል ለመለት አያስደፍርም። የአንድ አገር ኢኮኖሚ አደገ ማለት የሚቻለው ኢኮኖሚው በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ሲመራ ነው። ይህ ደግሞ ካለብረታ ብረት እንዱስትሪ መስፋፋትና ካለኤሌክትሪክ ኃይል የሚታሰብ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ይህን ቴዎድሮስ በዚያን ጊዜ የተረዱ መሪ ነበሩ። በመሆኑም እነዚህን ጋፋት ላይ እንዲቀመጡ ያደረጓቸውን የውጪ ሰዎች መድፍ እንዲሠሩ ጠየቋቸው። ሰዎቹም ከሙያው ጋር ትውውቅ ባይኖራቸውም በንጉሡ ተጽዕኖ መድፍ ለመሥራት ጥረት ማድረግ ጀመሩ። በዚህም ኢትዮጵያውያን ጥበቡን እንዲማሩ አደረጉ። ይህን ከፈረንጆቹ ጋር ሆነው የመድፍ አሠራሩን እንዲማሩ ከተደረጉት መካከል፣ ፊታውራሪ ውድነህ ሙላቴ የተባለው ጎጃሜና ሞሪስ መኮንን ይገኙበታል።(እንደላይኛው)
11. ከሁሉም በላይ በግራኝ እና በጋላ(ኦሮሞ) ወረራዎችና እነዚህን ወረራዎች ተከትሎ በተከሰተው ዘመነ መሣፍንት መስፋፋት ክብርና ሥልጣኑ ጥያቄ ውስጥ ወድቆ የነበረው የንጉሠ-ነገሥቱን መብት፣ ሥልጣን፣ የአንድነት ምልክትና የሥልጣን ምንጭነቱን መልሶ እንዲቀዳጅ በማድረግ የአገሪቱ አንድነት በተሻለ መሠረት ላይ እንዲገነባ ያደረጉ የኢትዮጲያ አንድነት ትንሣዔ አብሳሪ ንጉሠ ነገሥት ናቸው።

**11.2 የቴዎድሮስ የውጭ ፖሊሲ፦**

ቴዎድሮስ በኖሩበት ዘመን ከዓለማችን ኃያላን ከሚባሉት አንዷ ኦቶማን ቱርክ ነበረች። በመሆኑም የመካከለኛው ምሥራቅ፣ የሰሜን አፍሪካ፣ የምሥራቅ አፍሪካና የደቡባዊ አውሮፓ አገሮች በቱርክ ቁጥጥር ሥር ይገዙ የነበሩበት ዘመን ነበር።። ይህም ስለሆነ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ባለቤትነቷን ያጣችበት ዘመን ነበር። ኦቶማን ቱርክ የምፅዋንና የዳሕላክን ደሴቶች ተቆጣጥሮ የጦር ሠፈሩ አድርጎ አገሪቱ ከውጭው ዓለም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳይኖራት አፍኖ የያዘበት ዘመን ነበር። ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ ባላት የጂኦፖለቲካ አቀማመጥ በዘመኑ የነበሩት ኃያላን ኃይሎች በቁጥጥራቸው ሥራ ለማዋል እሽቅድምድም የያዙበት ዘመን መግቢያ ነበር። ሜዲተራንናንና ቀይ ባሕርን ለማገኛኘት የስዊዝ ቦይ ቁፋሮው ተጀምሮ ወደ መጠናቀቂያው የተቃረበበት ዘመን ነበር። በአንድ ቃል የአፍሪካ ቅርምት ዋዜማ ዘመን ነበር።

ከሁሉም በላይ በግብፅ ከዲቭ ሞሐመድ የሚመራ አዲስ መንግሥት ተመሥርቷል። ከዲቭ ሞሐመድ ሥልጣን እንደያዘ፣ የአገሪቱን ግዛት ማስፋትና ታላቅ ኢምፓየር የመገንባት ዓላማ ይዞ ተነሳ። ለዚህ ዓላማው መሟላትም በ1839 ዓም (1847) ሱዳንን ወሮ የግዛቱ አካል አደረገ። በማከታተልም በ1860 ዓም (1868) ቱርክ የምፅዋን ወደብ ለግብፅ በመስጠቷ ከዲቭ ሞሐመድ የቀይ ባሕር በርና ከኢትዮጵያ ጋር የደንበር ንክኪን መሠረት ጣለ። «ጅራቷ ያደርሳል ካናቷ» የሆነለት ከዲቭ ሞሐመድ፣ ምፅዋን መሠረቱ በማድረግ ወደ ደቡባዊ ቀይባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ይዞታውን በማስፋት የታጁራን ሰርጥና አካባቢውን፣ ዘይላንና በርበራን ያዘ። ከበርበራና ከዘይላ በመነሳት ሐረርን በመቆጣጠር እስከ 1872ዓም(1880) ድረስ ሐረርን ይዞ መቆየቱ ይታወዳል።(ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 263)

ይህ የግብፅ የመስፋፋት ዕቅድ ያሳሰባቸው ቴዎድሮስ፣ መጭውን ወረራ ለማክሸፍ መላ ማለት ነበረባቸው። በአገር ውስጥ ያሉትን ተቃዋሚዎቻቸውን ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ በሚቻላቸው ሁሉ በመቆጣጠር፣ የተወሰነ ትኩረታቸውን ወደ ውጭ እንዲያደርጉ ግድ አላቸው። የትኩረታቸው ዒላማም በቱርክ ተቀጽላ ቁጥጥር ሥር ያለውን የግብፅን ሠራዊት ከቀይባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ገፍትሮ ማስወጣት የሚል ነው። ኢትዮጵያ የቀይባሕር ባለቤትነቷን መልሳ ማረጋገጥ እንዳለባት ቁርጠኛ ውሣኔ አደረጉ። ይህ ውሳኔአቸው፣ በዚያን ጊዜ የቀይባሕርን ጥቅም (የወደብን ጥቅም) ከተረዱ መሪዎች አንዱ ቴዎድሮስ እንደነበሩ ያስገነዝባል። በሌላ አባባል፣ ቴዎድሮስ በአገሪቱ የውጭ ፖሊሲ ውስጥ፣ ቀይ ባሕር ያለውን ከፍተኛ ሚና በውል የተረዱ እንደነበሩ ወደቦቹን ለመቆጣጠር ያሳዩት ፍልጎት ያመለክታል። ይህ ፍላጎታቸው ግን፣ በብቸኝነት ሊሳካ እንደማይችል ተገነዘቡ። ለዓላማቸው መሳካት ክርስቲያን የሆኑ መንግሥታት ዕርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ላፍታም አልተጠራጠሩም። የቀይባሕርን ምዕራባዊ ዳርቻ መልሶ የኢትዮጵያ ለማድረግ ክርስቲያን ከሆኑ መንግሥታት ጋር በማበር የሃይማኖት ጦርነት ማድረግ ተገቢ እንደሆነ አመኑ። ቴዎድሮስ ከዚህ አቋም ላይ ለመድረስ የቻሉት በሸፍትነታቸው ጊዜም ሆነ፣ በኋላ የደንቢያና የቋራ ገዥ በነበሩበት ወቅት ከድርቡሾች ጋር ያደረጉት ተከታታይ ጦርነት ከድንበር ማስፋት በተጓዳኝ የሃይማኖትም ጭምር ስለነበር፣ ለዚህ ዓይነቱ አመለካከት መስረጽ አጋጣሚ እንደፈጠረላቸው መገንዘብ ይቻላል።

ለዚህ ፍላጎታቸው ዕውን መሆንም ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ መንግሥታት ጋር ግንኙነት ለመመሥረት ፈለጉ። ለዚሁ ዓላማ መሳካት ሲሉ እኤአ ከ1855 ጀምሮ የእንግሊዝ ቆንስል ከነበረው ዋልተር ፕላውደን ጋር የጠቀ ግንኙነት መሠረቱ። ፕላውደን ከቴዎድሮስ ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች፣ ለቴዎድሮስ ሀሳብ ቀና አመለካከት ያዘ። ይህም በመሆኑ ቴዎድሮስ ዓላማቸው በቀላሉ የሚሳካ መስሎ ታያቸው። ምክንያቱም ፕላውደን በወቅቱ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለነበረው ሎርድ ጆርጅ ክላርደን አሳውቆት ስለነበር፣ እርሱም ሀሳቡን የሚደግፈው መሆን ገልጦለት ስለነበረ፣ ይህንም ቴዎድሮስ በፕላውደን አማካኝነት በመስማታቸው ነው። (ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 263)

ሆኖም፣ ሎርድ ክላርደንና ፕላውደን ያራምዱት የነበረውን የቴዎድሮስን ፍላጎት የማሟላት ዕቅድ፣ በግብፅ የእንግሊዝ ቆንስል የነበረውና የእንግሊዝ የውጭ ፖሊሲ የምሥራቅ አገሮች አዋቂ ተብሎ የሚጠራው ሎርድ ብሩስ ተቃዋሚ ሆኖ ቆመ። ክላርደን፣ ኢትዮጵያ የምፅዋን ወደብ ማግኘት አለባት የሚል አቋም ነበረው። የእንግሊዝ በምሥራቅ አገሮች ፖለቲካ አዋቂ የሆነው ዲፕሎማቷ ብሩስ፣ የምፅዋን ለኢትዮጵያ መመለስ ተገቢ መሆኑን አምኖ፣ አገሩንም ያሳመነ ቢሆንም፣ እንግሊዝ በዚህ አቋሟ እንዳትቀጥል የሚያስገድዳት ሁኔታ ተፈጠረ። ይኸም፣ ሩሲያ በባልካን አገሮች እና በመካከለኛው ምሥራቅ እግሯን ለመትከል በማሰቧ ምክንያት ፣ ይህን የሩሲያን ፍላጎት ለመከላከል እንግሊዝ በኢትዮጵያ የምፅዋን መመለስ አቋም ለወጠች። ይህም ለኢትዮጵያ ስትል ከቱርክ ጋር ቅራኔ ከምትገባ፣ ከቱርክ ጋር ሆና የሩሲያን በአካባቢው የመስፋፋት ፍላጎት መቀጨት ለብሔራዊ ጥቅሟ ዘላቂነት የሚያዋጣ እንደሆነ አመነች። ይህም በመሆኑ፣ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ክርስቲያን አገር ስለሆነች፣ በክርስቲያኗ የእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ እስላሟን ቱርክን ወግቼ የወደብ ባለቤት እሆናለሁ በማለት የደከሙበት ዓላማ፣ በቋሚው ብሔራዊ ጥቅም ጊዜአዊው የቴዎድሮስ ወዳጅነት ተለወጠ።(ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም፣ 2003፣ 264)

ቋሚ ጥቅም እንጂ፣ ቋሚ ወዳጅ አለመኖሩ ያልተገለጸላጠው ቴዎድሮስ፣ እንግሊዝ ክርስቲያኗን ኢትዮጵያ ገፍታ፣ ከእስላሟ ቱርክ ጋር ግንኙነት መመሥረት ለቴዎድሮስ ሊቀበሉት የማይችሉት ሆነባቸው። ይህም ወደ ውዝግብ አመራቸው። ቴዎድሮስ በእንግሊዝ ዕርዳታ የባሕር በር አገኛለሁ የሚለው ዓላማቸው ሟሸሸ። ያም ሆኖ፣ ቴዎድሮስ በእንግሊዝ ዕርዳታ ጠናካራ ኢትዮጵያን እመሠርታለው የሚለው ዓላማቸው ጨርሶ ያልጠፋ በመሆኑ፣ ፕላውደን በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ቆንስል ሆኖ መመደብ ለፍላጎታቸው ማንሰራራት ምክንያት ሆነ። ፕላውደን፣ የቴዎድሮስን ፍላጎት ለማሟላት ከልብ ጣረ። የርሱና የቴዎድሮስም ወዳጅነት ጠነከረ። ይህ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ፕላውደን ታመመ። ለሕክምና ወደ አገሩ መሄድ እንዳለበት ቴዎድሮስን ፈቃድ ጠየቀ። የጠየቀውን ፈቃድ አገኝቶ ወደ ምፅዋ ሲጓዝ፣ በቴዎድሮስ ላይ ያመጸው ጋረድ ክንፉ እኤአ 1860 ሊሚሊሞ ላይ ይዞ ገደለው። የወዳጃቸው የፕላውደን በጋረድ መገደል ከመጠን በላይ ያበሳጫቸው ቴዎድሮስ በጋረድ ላይ ዘምተው እርሱንም ሆነ ተከታዩን የሰሜን ገበሬ ክፉኛ ቀጡት። የፕላውደን መሞትም ለእንግሊዝና ለቴዎድሮስ ግንኙነት መሻከር ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ሆነ።(እንደላይኛው፣ 264—5)

ከፕላውደን መገደል በኋላ፣ እንግሊዝ ሻምበል ካሜሩንን የኢትዮጵያ ቆንስል አድርጋ ሾመች። ቴዎድሮስም በዚህ ሰው አማካኝነት ያቀድኩት የአገር ግንባታና የቀይባሕር ባለቤትነት ይረጋገጣል በሚል ተስፋ፣ የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ። በመሆኑም ቴዎድሮስ ከፍ ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው፣ የእንግሊዝ በቱርክ ላይ ያላትን አቋም መለወጥ ሳይገነዘቡ፣ እኤአ ጥቅምት 30 ቀን 1862 ለንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ጻፉ። የቴዎድሮስ ደብዳቤ ሙሉ ቃል እንዲህ የሚል ነው።

> **«-------አያቶቼ ፣ ያገሬ መሪዎች ፈጣሪያችንን ስላሳዘኑት፣ ይኸው እስካሁን ድረስ መንግሥታችን በቱርክና በጋላ እጅ ወድቆ ይገኛል። ዛሬ ግን ፈጣሪየ እኔን ስወለድ ጀምሮ ከትቢያ አንስቶ በአባቶቼ መንግሥት ሥልጣን ሰጥቶኛል። በአምላክ ርዳታ አገሪቱን ከጋላ ነፃ አውጥቻታለሁ። ግን ቱርክ ከአያቶቼ ምድር ለቀው ለመውጣት እምቢ ብለዋል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ዕርዳታ ልዋጋቸው ተነስቻለሁ።**
>
> **«ሚስተር ፕላውደንና እንዲሁም ሊቀመኳስ ዮሐንስ(ቤል) ታላቋ የብሪታንያ መሪ የክርስቲያኖች ሁሉ ጉዳይ ጉዳዮ እንደሆነ አረጋግጠውልኛል። የንግሥትነተዎን ወዳጅነት ለመሻት በተነሳሁበት ወቅት መልዕክተኞችዎ ሞቱ፣ እኔን ሊጎዱኝ የፈለጉ ጠላቶቼ ገደሏቸው። ግን እኔ በእግዚአብሔር ኃይል ጠላቶቼን እስከ መጨረሻው ሰው ድረስ፣ ከነሱም ውስጥ የገዛ ዘመዶቼን ጭምር በመግደል ተበቅየላቸዋለሁ። ንግሥትነተዎ በአምላክ ኃይል በጎ ፈቃደዎ እንዲሆን ተስፋ አድርጋለሁ።**
>
> **« ቱርኮች የባሕር ጠረፉን ይዘው መልዕክተኞቼ እንዳይተላለፉ ያስቸግራሉ። ቆንስል ካሜሩን ወደ እኔ መጥቶ በእግዚአብሔር ዕርዳታ ደብዳቤዎንና የወዳጅነት ስጦታዎን በሰጠኝ ጊዜ፣ ንግሥትነተዎ ጤና መሆነዎንና ስለወዳጅነተዎ በማወቄ በጣም ደስ ብሎኛል። ከፍ ላለው ስጦታዬ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።**
>
> **« በባሕር ጠረፍ እንዳልተላለፍ የሚከለክሉኝ ቱርኮች መልዕክተኛዬና ቆንስል ካሜሩንን እንዲሁ ስጦታዬን ይይዟቸዋል። ለእኔ ማንም ሳይነግረኝ ወዳልታወቀ ቦታ ወስደው ያስሯቸው ይሆናል ብዬ እሰጋለሁ። ቆንስል ካሜሩንን ከመልሰዎ ጋር በሰላም ይመልሰው፤ ግን እርሰዎ እስላም ሊጨቁነኝ ሲፈልግ ምርኩዜ እንዲሆኑኝ እለምነዎታለሁ።» (ዓለማየሁ አበበ፣ ትርጉም ፣2003፣ 266)**

ከዚህ የቴዎድሮስ ደብዳቤ በተጨማሪ፣ ካሜሩንን፣ ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ቴዎድሮስ መኃንዲሶች፣ የጦር መሳሪያ ሙያተኞች፣ ሐኪሞች እንዲልኩላቸው የሚፈልጉ መሆኑን በጽሑፍ አስገብቷል። ይሁን እንጂ፣ ለቴዎድሮስ ጥያቄዎች በአዎንታዊ መልኩ ይመለከተው የነበረው ክላርደን ተነስቶ፣ በምትኩ ሎርድ ራሰል ተተክቶ ስለነበር የቴዎድሮስ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ብቻ ሳይሆን፣ አሉታዊ መልስ ለመስጠት የፈለገ የለም። ቴዎድሮስም ለጻፉት ደብዳቤ መልስ በመጠባበቅ ላይ እያሉ፣ ያለርሳቸው ዕውቅና ቆንስል ካሜሩንን ከኢትዮጵያ ለቆ ወደ ምፅዋ እንዲሄድ ትዕዛዝ ደረሰው።

ለጠየቁት ጥያቄ ምንም ዓይነት መልስ ከእንግሊዝ መንግሥት ሳይሰጣቸው፣ የመልዕክቱ አቀባባይ ሆኖ ያገለግል የነበረው ካሜሩን ሳያውቁት ወደ ምፅዋ እንዲሄድ መደረጉ ቴዎድሮስን ከመጠን በላይ አናደደ። በመሆኑም እኤአ 1864 ቴዎድሮስ «አገሬን ለመጉዳት ስትዶልት ከርመሃል» በማለት ከሰው አሰሩት። ከእርሱም ጋር 40 ያህል የውጭ አገር ዜጎች እንዲታሰሩ ሆነ። ይህ ዕርምጃ በቴዎድሮስና በእንግሊዝ መንግሥት መካከል የሻከረውን ግንኙነት በማከረር ወደ ጦርነት ፍጥጫ አመራቸው።

ካሜሩን እንደታሰረ፣ የእንግሊዝ መንግሥት በንግግር ለመፍታት ሙከራ አደረገ። ለንግግሩም በኤደን የቅኝ ግዛት የፖለቲካ አማካሪ የሆነው ሆርሙዝድ ራሣም ወደ ቴዎድሮስ ተላከ። ራሣም በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል ወደ ኢትዮጵያ መግባት ባለመቻሉ፣ በሱዳን በኩል አድርጎ እኤአ ኅዳር ወር 1865 መተማ ገባ። ጥር 1866 ጎጃም ውስጥ ከቴዎድሮስ ጋር ተገናኘ። ከእንግሊዝ መንግሥት ለቴዎድሮስ የተጻፈውን ደብዳቤ ሰጠ።

ደብዳቤው ግን ቴዎድሮስ የታሰሩትን እስረኞች ከለቀቁ ከእንግሊዝ መንግሥት በምትኩ ይኸን ያገኛሉ የሚል፣ በጉጉት ይጠባበቁት ስለነበረው እርዳታ የሚለው አንዳችም ነገር የለም። የተስፋ ፍንጭም የለውም። ደብዳቤው በያዘው መልዕክት የተበሳጩት ቴዎድሮስ፣ ለራሣም እንዲህ አሉት፤ **«የታሰሩት አውሮፓውያን የሚፈቱት፤ እንግሊዝ ጦር መሣሪያ የመሥራት ችሎታ ያላቸው ሠራተኞች ስትልክና የመሣሪያ ፋብሪካ ለማቋቋም የምትረዳ ከሆነ ነው።»** በማለት ለራሣም ካስረዱት በኋላ፣ ለዚህ አጥጋቢ መልስ እስኪ መጣ ድረስ ራሣም በመያዣ መልክ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚቆይ አስረዱት።( ዓለማየሁ አበበ ፣ትርጉም፣ 2003፣ 276)

የእንግሊዝ ዲፕሎማቶች ካሜሩንን፣ ራሣምንና መሰሎቻቸውን ሰብስበው በመቅደላ አምባ ላይ መታሠር፣ የእንግሊዝን መንግሥት ክብርና ዝና የሚያዋርድ ሆኖ ተቆጠረ። የሕዝብ ኃላፊነት ያለው መንግሥት ደግሞ ለዜጎቹ መብትና ክብር መጠበቅ አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ያደርጋል። በመሆኑም ፣ የታሠሩትን ዜጎቹን ለማስፈታት የእንግሊዝ መንግሥት በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ቢጠይቅ፣ የቴዎድሮስ መልስ አሉታዊ ሆነ። እንግሊዝ በዓለም ያላትን ክብርና ዝና ለመጠበቅ ስትል ሕንድ ላይ ከሠፈረው ጦሯ የተወሰነው ክፍል፣ በጄኔራል ናፒየር የሚመራ ተጉዞ እስረኞቹን እንዲያስፈታ ትዕዛዝ ሰጠች። ዘመቻውም **«የታሰሩ አውሮፓውያንን ማስፈታት»** የሚል መጠሪያ ተሰጠው። የዘመቻው ግብም **«የታሰሩ አውሮፓውያንን በማስፈታት ፣እንግሊዝ በቀይ ባሕር ቀበሌ የነበራትን ክብር ማስጠበቅ ነው።»** ይህ የዘመቻ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት የስዊዝ ካናል ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ስለነበር ፣የቀይ ባሕር አካባቢ የዓለም የጂኦ ፖለቲካ ዕምብርት የሆነበት ነበር። እኤአ 1867 የእንግሊዝ መንግሥት በጄኔራል ናፒየር የሚመራ ወታደራዊ ኃይል ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘምት ወሰነ። የዘመቻው መዘጋጃና መናኻሪያም ቦምቤይ እንዲሆን ተወሰነ። ለዘመቻው ማስፈጸሚያ ምክርቤቱ ሁለት ሚሊዮን ፓውንድ ፈቀደ።(ዓለማየሁ አበበ፣ትርጉም፣2003፣277)

እኤአ ጥቅምት 21 ቀን 1867 በናፒየር የሚመራው የእንግሊዝ ጦር ዘይላ ገባ። የሠራዊቱ የሰው ኃይል አንዳንድ መረጃዎች 26,000(ሃያ ስድስት ሺ) ሲሉ፣ ሌሎች ይኸን ቁጥር ወደ 32,000(ሰላሳ ሁለት ሺ) ያደርሱታል። በአጠቃላይ የቴዎድሮስን ጦር መቅደላ ላይ ለመግጠም ኢትዮጵያ ውስጥ የገባው የእንግሊዝ ዘማች ኃይል 40,000(አርባ ሺ) እንደሚደርስ ይታመናል። ለዘመቻው በአጠቃላይ የወጣው ወጭ ዘጠኝ ሚሊዮን ፓውንድ ነው (እንደላይኛው)። ናፒየር ይኸን ያህል ጦር አዘጋጅቶ ከሩቅ አገር ሲመጣ፣ ቴዎድሮስ የነበራቸው ኃይል በመካከለኛ የሥልጣን ዘመናቸው ያስከትሉት ከነበረው ወደ 60,000(ስልሳ ሺ) ይገመት ከነበረው ሠራዊታቸው፣ ናፒየርን ለመግጠም በሚዘጋጁበት ሰዓት፣ ከጎናቸው የተሰለፈው ታማኝ ጦራቸው ከ10,000(አሥር ሺ) የሚበልጥ አልነበረም።(ባሕሩ ዘውዴ፣2003፣42)

ለናፒየር ዘመቻ ውጤታማ መሆን፣ የእንግሊዝ መንግሥት በቴዎድሮስ አገዛዝ ላይ ያመጹትን የሰሜን ኢትዮጵያ ባላባቶችን በጥቅም ከጎኑ ማሰለፍ እንዳለበት በማመን፣ የትግሬውን ካሣ ምርጫንና የላስታውን ዋግሹም ጎበዜ ገብረመድኅንን በልዩ ልዩ ጥቅሞች ደልሎ ከጎኑ አሰልፏል። የቦታው ርቀት ዕርዳታ ለመስጠት አላስቻላቸውም እንጂ፣ የሸዋው ምኒልክም የናፒየር ተባባሪነታቸውን በደብዳቤ ገልጸዋል።

በመሆኑም ያለዳች ችግር በካሣ ምርጫ በሚቀርብለት መረጃ፣ ሥንቅ፣ የሰው ኃይልና ማጓጓዣ በመጠቀም ናፒየር ከምፅዋ እስከ መቅደላ ባለው ሠፊና ተራራማ ቦታ አቆራርጦ ደላንታ ገባ። መጋቢት 21 ቀን 1860 ዓም የናፒየር ጦር ተከዜን ተሻገረ። በዚህ ወቅት ቴዎድሮስ መቅደላ ወጥተው፣ ለራሳም እንዲህ የሚል መልዕክት ላኩበት።

> **« አንተን እዚህ ያሰርኩህ እንግሊዞች ወደ እኔ እንዲመጡ ነው፤ በመምጣታቸውም እደሰታለሁ፤ ድል ቢያደርጉኝም ፤ወይም ድል ባደርጋቸው፣ እኔ ምንጊዜም ያንተ ወዳጅ ነኝ፤ ካንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ።»** (ገሪማ ታፈረ፣ 2ኛ ዕትም፣ 1996፣ 208)

የናፒየር ሠራዊት እየገፋ ወደ መቅደላ ሲቃረብ፣ ለራሣም በድጋሚ እንዲህ አሉት።

> **« ምንም እንኳን ጥቁር ብሆን፣ እንግሊዝ ዝቅ አድርገው እንደማይገምቱኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሁላችንም አንድ ዓይነት ችሎታና ዕውቀት ስለሰጠን።»** (እንደላይኛው፣ 209)

ለሁለቱም የቴዎድሮስ አስተያየቶች ራሣም ምን መልስ እንደሰጠ የሚያመላክቱ መረጃዎች በዚህ ወቅት ይህ ጸሐፊ አላገኘም። ያም ሆኖ ግን፣ በመቅደላ ጦርነት ዋዜማ ላይ ከአንባው ላይ ታስረው የነበሩት የቴዎድሮስ እስረኞች ያልተለመደ ጩኸት አሰሙ። ቴዎድሮስ የጩኹበት ምክንያት ምንድነው ? ብለው ታሳሪዎቹን ጠየቁ። እስረኞቹ ባንድ ቃል « እንዲምሩን ብለን ነው» አሏቸው።

ቴዎድሮስ የጠያቂዎቹ ዓላማ ከፍርሃት በመነጨ ምክንያት ይምረንና፣ ይፈታናል ከሚል እሳቤ የተነሳ ጩኸት መሆኑ ስለገባቸው፣ «እኔ አንድነቱ የመይሣው ልጅ፣ እንግሊዝ መጣ ሲሏችሁ፣ ይፈራል መስሏችሁ ነው? አልምርሽም፤ ጠላቴን በፊቴ አድርጌ ነው የምሄደው፤» ብለው የታሳሪዎቹ ወንጀል እየተነበበ፣ ከባድ ወንጀል የፈጸሙት በግራ፣ ቀላል ወንጀል የፈጸሙት በስተቀኝ እንዲቆሙ አዘዙ።

በዚህም መሠረት በግራ 282 ፣ በቀኝ 318 ታሳሪዎች ተሰለፉ። ታሳሪዎቹ በዚህ ሁኔታ ከተለዩ በኋላ፣ በግራ በኩል የተሰለፉት 282ቱ እንዲገደሉ ወስነው በቀኝ በኩል የተሰለፉትን 318ቱን ማሩዋቸው።

ቴዎድሮስ የዚህ ዓይነቱን እርምጃ ለመውሰድ ያስገደዳቸው ወይም የገፋፋቸው፣ ከታሣሪዎቹ አንዱ የሆነ፣ «ቢፈቱን ይፍቱን፣ እስከ ዛሬ የተሰቃየነው ይበቃል፤ አሁንስ የሚያስፈታን መንግሥት መጥቷልና እርስዎን የምንለምንበት ምክንያት የለም» ብሎ ለገናው ከወራሪው ጦር ጋር ያለውን ግንኙነትና ቴዎድሮስም ተሸናፊ እንደሚሆኑ በልበሙሉነት በመናገሩ የቴዎድሮስን ስሜት ክፉኛ ስለነካ ነው። ለዚህ ሰው አስተያየትም ቴዎድሮስ «እንግሊዝ እስኪያስፈታሽ አሁን ያለኝ ጊዜ ላንች ሳይሆነኝም አይቀርም» በማለት በግራ የቆሙትን ሁሉ እንዲገደሉ አዘዙ። በትዕዛዙም መሠረት ተፈጸመ። (እንደላይኛው ፣ 213)

ከነዚህ መቅደላ ላይ ከታሰሩት አንዱ የዐፄ ዮሐንስ 4ኛ አጎት ራስ አርኣያ ነበሩ። ታሳሪዎቹ በቀኝና በግራ እንዲሰለፉ ሲያዙ በቀኝ ከተሰለፉት አንዱ ሆኑ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ አርኣያን አስጠርተው፣ «አንተ የበደልከኝ ነገር የለም፤ መልካም ተዋጊና ጀግና ነህ፣ ትሸፍታለህ ብየ ብጠረጥርህ ነው ያሰርኩህ » በማለት በነፃ ለቀቋቸው። ደጃዝማች አርኣያም ለተደረገላቸው ምሕረት አመስግነው፣ «የዛሬን ጦርነት አብሬዎት ልዋልና ተመልሼ ልታሠር፣» የሚል ጥያቄ አቀረቡ። ቴዎድሮስ አርኣያ ላቀረቡት የአብሬዎት ልዋጋ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ አልሰጡም። ምክንያቱ ግልጽ ነው። የእህታቸው ልጅ ካሣ ምርጫ ናፒየርን እየመራ እንደመጣ አያወቁ፣ አርኣያ ከእህቱ ልጅ ከካሣ ምርጫ፣ ለቴዎድሮስ ይቆማል ብለው ሊያስቡ የሚያስችል አሳማኝ ሁኔታ አለመኖር ዋናው ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል።

ቴዎድሮስ የናፒየርን ሠራዊት በተለመደው የደፈጣ የማጥቃት ሥልታቸው ገጥመው ለድል ያበቃኛል ብለው ያዘጋጁትን የጦር ሥልት ተቀናቃኞቻቸው ቀድመው ለናፒየር በመንገራቸው ዕቅዳቸው ከሸፈባቸው። በመሆኑም ሚያዝያ 3 ቀን 1860 ዓም «አሮጌ» ላይ በተደረገው ጦርነት ናፒየር በተወሰነ ኃይል ብቻ መቅደላን በመድፍ ደበደበ። ለዚህ ድብደባ የተሰለፈው የእንግሊዝ ተዋጊ ኃይል 200 ብቻ ነበር። በዚህ የመጀመሪያው የቴዎድሮስና የናፒየር የአሮጌ ጦርነት 700 የቴዎድሮስ ወታደሮች ሲገደሉ፣ 1500 መቁሰላቸው ተመዝግቧል። የቴዎድሮስ ታማኝ የጦር ሰው የሆነው ገብርዬ(ገብረእግዚአብሔ ጎሹ) ለአገሩና ለንጉሡ ነገሥቱ ያለውን ፍቅርና ታማኝነት አንድም ቀን ሳያጓድል በክብር የተሰዋው በዚህ የአሮጌ ጦርነት ሚያዝያ 3 ቀን 1860 ነው። ይህ ለቴዎድሮስ ከባድ ሀዘን እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። በመሆኑም ቴዎድሮስ በታሪክ ልዩ ቦታ ያለውን የመጨረሻውን ፍላጎታቸውንና ምኞታቸውን የገለጹበትን ደብዳቤ ለናፒየር ጻፉ።

ቴዎድሮስ ለናፒየር የጻፉት ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነው።

> **«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ፤ በሦስትነት ባንድነቱ በክርስቶስ ያመነው ካሣ መቸም ያገሬ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል እኔ ካልወረድሁላችሁ ሸሽታችሁን አትተውም። ክርስቲያኑ ሁሉ ጉልበት አለኝ መስሎኝ ካረመኔ አገር አግብቸው ወንድ የሌላት ቆንጆ አለች፣ ወንድ የነበራት ቆንጆ ነበረች፣ ትላንትናም የሞተባት ትኖራለች፤ ሽማግሌ ልጅ የሌለው ባልቴት ልጅ የሌላት እኔ የምጦራቸው ብዙ በከተማየ አሉ። እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ፍቀዱላቸው የአረመኔ አገር ነውና፤ ያገሬ ሰው ገብር ሥራት ግባ ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በሥራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ። እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች አንድ እርሳስ ፈርተው ጥለውኝ ሸሹ፤ ብተቃጧቸው ከርጡ ሰዎች ጋራ አልነበርሁም፣ ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ሥታገል ውዬ ነው። ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዞአል፣ እስልሞአል እያለ አሥሩን ምክንያት ይሰጠኝ ነበር። እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም ይሥጠው ፤ እንደወደደ ይሁን፤ እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ሁሉን ልገዛ ሀሣብ ነበረኝ።እግዚአብሔር ቢነሣኝ ልሞት አሣቤ ይህ ነበረ። ከተወለድሁኝ እስታሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበረ ሰዎች ሢሸሹ ተነስቸ ማረጋጋት ልማድ ነበረኝ ጨለማ ከለከለኝ። ትናንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ። እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን አስለቅቃለሁ መስሎኝ ነበር።ወንድ ያቀፈ ወንድ ተመልሶ አያቅፍም።»** (ባሕሩ ዘውዴ፣ 2003፣ 45-6)

ቴዎድሮስ በአሮጌ ጦርነትና ውጤቱ ጎሊናቸው የተነካ መሆኑን ለናፒየር በጻፉት በዚህ ደብዳቤ በግልጽ ይነበባል። ይህ የቴዎድሮስ የመጨረሻ ስንብት የሆነ ደብዳቤ የነበራቸውን፣ ቁጭት፣ እልከ፣ የዓላማ ጽናት፣ ቁርጠኝነትና የሩቅ ራይዕ ባለቤት የነበሩ መሆኑን የሚያሳይ ኑዛዜ ነው። በዚህ የቴዎድሮስ የመጨረሻ ደብዳቤ የሚከተሉትን ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ዕውነታዎች እናገኛለን።

**አንደኛ፦ « መቸም ያገሬ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል እኔ ካልወረድሁላችሁ ሸሸታችሁን አትተውም።»** ይህ ሀሳብ የሚነግረን ቴዎድሮስ ያገራቸው ሰው የጠላቸውና በእግዚአብሔር ኃይል እርሳቸው ከሥልጣናቸው ካልወረዱ ከፍራትና ከሽሽት አይቆሙም፣ በእኔ ምክንያት ፈሪና ሽሽታ ሆነዋል የሚል መልዕክት የያዘ ነው። ባንድ ቃል ሕዝባቸው ዓላማና ፍላጎታቸውን ባለመረዳቱና የሚያደርጉትን በመጥላቱ እርሳቸውን በመጥላት ከጎናቸው ርቆ ለጠላት ያጋላጣቸው መሆኑን በመፀፀት የገለጹበት ነው።

**ሁለተኛ፦ « ክርስቲያኑ ሁሉ ጉልበት አለኝ መስሎኝ ካረመኔ አገር አግብቸው --»** ይህ አባባላቸው እርሳቸውና የሚመሩት ሕዝብ ክርስቲያን ስለሆነ፣ ሃይማኖት ወደ ሌለው አገር ስወስደው ለሃይማኖቱ ሲል ጠንክሮ ይዋጋል መስሎኝ ነበር፤ ግን አልሆነም ክርስቲያኑ ጉልበትና ኃይል ይሆናል ብለው ያሉት በተቃራኒው መሆኑን ያሳዩበት ነው ፣ ይህም ለመጠቃታቸው አንዱ ምክንያት እንደሆነ ያሳያል።

**ሦስተኛ፦ «ያገሬ ሰው ገብር፣ ሥራት ግባ ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በሥራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ።»** ይህ ያገራቸው ሕዝብ በሕግ የተወሰነ ግብር ለመንግሥት እንዲከፍል በማድረጋቸው የጠላቸው መሆኑንና በዚህም ምክንያት ከጎናቸው አለመቆሙን ሲያስረዱ፣ የናፒየር ጦር በሥርዓት የተደራጀና በሕግ የሚገዛ በመሆኑ እርሳቸውን ለማሸነፍ ምክንያቱ በሕግ መገዛቱና በሥርዓት መመራቱ እንደሆነ ያሳዩበት ነው። ይህን ደግሞ ደባርቅ ላይ ከድርቢሾች ጋር በተዋጉበት ጊዜ የድርቡሽ ጦር በወታደራዊ አሰላለፉና በመሣሪያው የበላይነት ያጠቃቸው መሆኑን ስለተገነዘቡ፣ ሠራዊታቸው ሥርዓት እንዲኖረው፣ አሰላለፉ እንዲያምርና ዘመናዊ የጦር መሣሪያ አስፈላጊ መሆኑን ያጤኑበትን አጋጣሚ የፈጠረላቸው እንደነበር ይታወሳል። ከዚያ ትምህርት ቀስመውም ሠራዊታቸው ሥርዓት እንዲይዝ፣ ሕዝቡ ግብር እንዲከፍል ደንብ ማውጣታቸውን ባለመቀበሉ፣ ለደረሰባቸው ሽንፈት ምክንያት እንደሆነ በቁጭት የገለጹበት ነው። ዓላማቸው ትክክል እያለ ሰሚና ተከታይ አለማግኘታቸው ያሳደረባቸውን ቁጭት ገላጭ ነው።

**አራተኛ፣ « እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች አንድ እርሳስ ፈርተው ጥለውኝ ሸሹ፤ ብትቃወሟቸው ከሮጡ ሰዎች ጋራ አልነበርሁም፣ ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ሥታገል ውዬ ነው።»** በእሮጌው ጦርነት አብረዋቸው የተሰለፉት ሰዎች ሞትን ፈርተው ሳይዋጉ መሸሻቸው፣ ቀድመው ለሽንፈት የተዘጋጁ መሆን፤ ተመተው ሳይሆን፣ በመቃጣት ወይም በማስፈራራት ብቻ የሸሹ ሰዎች መኖራቸውን ፣እርሳቸው ግን ከነዚህ ዓይነቶቹ ሲቃጧቸው ከሚሸሹ ሰዎች ጋር አብረው ተሰልፈው እንዳልነበረ ያስረዱበት ነው። እርሳቸው ባልሰላ፣ ዘመናዊ ባልሆነ መድፍ ሲዋጉ መዋላቸውን ለናፒየር የገለጹበት ነው።

**አምስተኛ፦ «እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ሁሉን ልገዛ ሀሣብ ነበረኝ። እግዚአብሔር ቢነሣኝ ልሞት አሣቤ ይህ ነበረ።»** ይህ አባባላቸው ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመግዛት፣ ኢየሩሳሌምን ጨምሮ የኢትዮጵያ አካል ለማድረግ የነበራቸውን ዓላማ እና ፍላጎት በግልጽ ያስቀመጡበት አባባል ነው። ሀሳባቸው ቢሳካ ኢትዮጵያንና ኢሩሳሌምን በአንድነት ለመግዛት፤ ካልሆነ በዓላማቸው ገፍተው ለመሞት ቁርጥ ውሣኔአቸው እንደነበር የመጨረሻ ቃላቸውን የሰጡበት ቋሚ ምስክርነት ነው።

**ስድስተኛ፦ «ከተወለድሁኝ እስታሁን ወንድ እጄን ጨብጦት አያውቅም ነበረ፣ ሰዎች ሢሸሹ ተነስቸ ማረጋጋት ልማድ ነበረኝ ጨለማ ከለከለኝ።»** ይህ አባባል ቴዎድሮስ በሕይዎት ዘመናቸው ተሸንፈው እጃቸውን ተይዘው የማያውቁ መሆኑን፣ በሚያደርጓቸው ጦርነቶች አብረዋቸው የተሰለፉ ሰዎች ሲፈቱና ሲሸሹ የማረጋጋትና የማበረታታት ሥራ ይሠሩ የነበሩ ጀግና እንደነበሩ፣ የእሮጌው ጦርነት ግን ይህን የተለመደ ተግባራቸው እየተወጡ እያለ ጨለማው የከለከላቸው መሆኑን በቁጭት የገለጹበት ነው።

**ሰባተኛ፦ «ትናንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ። እንኳን የሀበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን አስለቅቃለሁ መስሎኝ ነበር። ወንድ ያቀፈ ወንድ ተመልሶ አያቅፍም።»** የእሮጌው ጦርነት ከምንጊዜውም የከበደ ጭንቀት የጣለባቸው መሆኑንና ይህ ዓይነቱ በሌሎች ላይ እንዳይደርስ የተመኙበት ነው። የኢትዮጵያ አንድነት ጠላት የሆነውን ሀበሻ ቀርቶ፣ ኢየሩሳሌም ዘምተው ቱርኮችን ድል የማድረግ ዓላማ እንደነበራቸው፣ ምንጊዜም የድል ባለቤት የሚሆኑ እንደሆነ የመንፈስ ስንቅ የነበራቸው መሆኑን ያስረዳል። በመሆኑም ታላላቅ ጀግኖችን የታቀፈና ያንበረከከ የካሣ (ቴዎድሮስ) ክንድ በሌሎች እቅፍ ወይም ክንድ ውስጥ ሊወድቅ ወይም ሊገባ አይቻለውም። በማለት እጃቸውን ለጠላት የማይሰጡ መሆናቸውን ያሳዩበት ታላቅ የሕይዎት ዋጋ የተከፈለበት ቃል ነው።

ቴዎድሮስ እኤአ ሚያዝያ 11 ቀን 1868 አስረዋቸው የነበሩትን አውሮፓውያን ፈተው የናፒየርን ሠራዊት እንዲቀላቀሉ አዘዙ። የናፒየር ጦርም ሚያዝያ 13 ቀን 1868 የመቅደላን ምሽግ በመድፍ ደበደበ። የቴዎድሮስ ሠራዊት ከእሮጌ ጦርነት በኋላ የተመናመነ በመሆኑ፣ ሁሉም ባላባቶች ቴዎድሮስን ከወራሪው የእንግሊዝ ጦር በላይ ፈርቶና ጠልቶ፣ ለወራሪው በማደር፣ ብቻቸውን አቁመው ለጥቃት እንዲጋለጡ ብዙ ያሤሩ በመሆናቸው፣ ለቴዎድሮስ ካለ ቆራጡ እሳቸውነት በቀር ሌላ ከጎናቸው የቆሙት ጥቂት ታማኞቻቸው ብቻ ነበሩ። እነዚህም ባለቀ ሰዓት አጓጉል ሞት እንዲሞቱ ቴዎድሮስ አልፈለጉም። በመሆኑም መቅደላን ለቀው ወደ ፈለጉት ቦታ እንዲሄዱ አዘዙዋቸው። **«ወንድ ያቀፈ ተመልሶ ወንድ አያቅፍም»፣** ጀግኖችን ሲያስገብርና ሲያንበረክክ የኖረ ሰው በሌሎች በቴክኖሎጂና በሥርዓት በተገዛ ሠራዊት አሸናፊ ለሆነ ኃይል እጁን አይሰጥም፤ ብለው ለራሳቸው ቃል በገቡት መሠረት ሽጉጣቸውን እንደ መልካም ወይን ተጎንጭተው ታሪክ የማይሽረው፣ የጀግንነት፣ የኩራትና የአትንኩኝ ባይነት ሞትን ሞቱ።

ከዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ አለ። አንደኛው ቴዎድሮስ ለዓላማቸው ባጭር መቀጨትና ለሕይዎታቸው መጥፋትም ምክንያት የሆኑትን አውሮፓውያን እስረኞችን በምን ምክንያት በነፃ እንዲለቀቁ ፈቀዱ? የሚለው ነው። የቴዎድሮስ የዓላማ ሰውነት፣ ጽናት፣ ሐቀኝነት፣ ቆራጥነት፣ ብልኅነት፣ ሕዝባዊነትና አርቆ ተመልካችነት ጎልቶ የሚታየው አውሮፓውያንን ያላንዳች ችግር ፈትተው የመስደዳቸው ጉዳይ ነው። አውሮፓውያኑን ፈትተው እንዲሰዱ ትዕዛዝ ሲሰጡ፣ ለምን ይለቃቀቃሉ፣ ይገደሉ እንጂ፣ የሚል ምክር የሰጡ ተከታዮቻቸው እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ። ቴዎድሮስ ግን የሰጡት መልስ፣ እኔ አገሬን አሰለጥናለሁ፣ አንድ አደርጋለሁ፣ ሥርዓት እዘረጋለሁ ብየ የመረረ እርማጃ ወስጃለሁ። አሁን ግን ደግሜ እነዚህን ሰዎች በመግደል ወገኔ በባዕዳን እጅ እንዲጨፈጨፍ አልፈቅድም ብለው ያላንዳች ችግር ተፈተው እንዲሄዱ ማድረጋቸው ይታወቃል። ይህ ቴዎድሮስ ለትውልድ አሳቢ፣ መጭውን ተመልካች እንጂ፣ «እኔ ከሞትኩ---» ምናባቱ የሚል የከንቱዎች አስተሳሰብ ተከታይ አለመሆናቸውን ያሳያል። ይህ ውሣኔ አቸው ለትውልድ ያላቸው ጭንቀትና በቀልተኛ አለመሆናቸውን ያሳያል። በጥቅሉ ይህ ውሣኔ ለናፒየር ከጻፉት የመጨረሻ ደብዳቤአቸው ጋር ተጣምሮ ሲመዘን፣ የቴዎድሮስ የፍትሕ፣ የዓላማ ጽናትና ለኢትዮጵያ የነበራቸው መልካም የሩቅ ብሩኅ ራዕይ በግልጽ የሚያመለክት ነው።

### 11.3 ዳግማዊ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያላቸው ሚና፡-

ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያላቸው ሚና እጅግ የላቀ ነው።

(1) የኢትዮጵያ አንድነት ትንሣኤ ሲነሳ ቀድመው ከፊት የሚመጡት ቴዎድሮስ ናቸው።

(2) የዘመናዊ ውትድርና በኢትዮጵያ ሲወሳ ቀድሞ ተጠቃሹ ቴዎድሮስ ናቸው።

(3) የተማከለ የግብር አሰባሰብ ሲጠቀስ በመጀመሪያው ረድፍ የሚቆሙት ቴዎድሮስ ናቸው።

(4) ዘውድ የኢትዮጵያ የአንድነት ምልክት፣ የሥልጣን ምጭነቱን መልሶ እንዲይዝና የዘውዱን ክብር፣ ጥቅምና ሙብት ዳግም ያቀዳጁ ቴዎድሮስ ናቸው።

(5) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት የቅዳሴ አገልግሎት በሁለት ቄሶችና በሦስት ዲያቆኖች እንዲመራ ያደረጉ ቴዎድሮስ ናቸው።

(6) በአጠቃላይ ከላይ የተማከለ ዘመናዊ አስተዳደርን ለመመሥረት የወሰዷቸው ርምጃዎች ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪክ ያላቸውን ሚና አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው።

### 11.4 ትውልዱ ከዳግማዊ ቴዎድሮስ የሚማረው ቋሚ ትምህርት፣

- **ጀግንነት፤** ቴዎድሮስ ከሽፍትነት እስከ ሕልፈተ ሞታቸው ድረስ ካደረጓቸው ከ40 በላይ ጦርነቶች ተሸንፈው የሸሹት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ደባርቅ ላይ የቱርክ ተላላኪ ከሆኑት ሱዳኖች ጋር ባደረጉት ጦርነት፣ በመሣሪያ የበላይነትና በወታደራዊ አሰላለፍና ሥልጠና ተበልጠው ለመሸሽ ተገደዋል። የዘመናዊ የጦር መሣሪያንና የሰለጠነ ወታደርን አስፈላጊነት የተረዱት ከዚህ ጦርነት መሸሽ በኋላ ነው። ወታደራቸውን ሥርዓት ለማስያዝና ዘመናዊ ጦር መሣሪያ ለማሠራት ጥረት ያደረጉትም ከዚህ ቀን በኋላ ነው። ለቴዎድሮስ የድል ባለቤት መሆን ወሣኙን ሚና የተጫዎተው፣ ጀግንነታቸው ነው፣ ደፋር፣ ብልኅና አስተዋይ ናቸው። ይህ ባሕሪያቸው ለጠላት እጅን ከመስጠት ራስን በራስ ማጥፋት የተሻለ እንደሚሆን ዐውቀው ራሳቸውን በራሳቸው ገድለዋል። ይህን በማድረጋቸውም የአገሪቱ ክብር በዓለም ላይ ከፍ ብሎ እንዲነገር፣ ኩራትና ጀግንነት የኢትዮጵያውያን መለያ መታወቂያ እንዲሆን አድርገዋል።
- **ብልኅት፥** ቴዎድሮስ ብልኅ እና አስተዋይ ናቸው። በመሣፍንቶች ተከፋፍላ የነበረችን ኢትዮጵያ አንድ ያደረጉት በጀግንነታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በብልኅታቸው ጭምር ነው። የጦር አሰላለፋቸው፣ ጠላት ነው ያሉትን ከፋፍሎ የማጥቃት ሥልታቸው፤ የቦታና የጊዜ አመራረጣቸው፣ ኢትዮጵያን ለማበልጸግና ለማዘመን ለዕድጥበብ የሰጡት ግምት ከፍተኛነት፣ ለአንድ ሀገር ታላቅነት የወታደራዊ ሥልጠና ትጥቅና ሥነሥርዓት ያለውን ጥቅም ተረድተው በዚህ ረገድ ያሳዩት ጥረት ከብልኅነታቸው የሚመነጩ ናቸው።
- **ቆራጥነት፡-** ለማንኛውም ነገር ቆራጥ መሆን ያስፈልጋል። ያልቆረጠ ካሰበው ግብ አይደርስም፣ ከግብ ለመድረስ ቆርጦ መንቀሳቀስን ይጠይቃል። በዚህ ረገድ ቴዎድሮስ የጀመሩትን ነገር ከግቡ ለማድረስ እንቅልፍ የማይወስዳቸው፣ ድሎትን የማይሹ፣ ሞትን የማይፈሩ ነበሩ። ከዓላማቸው ተፃራሪ ለሆኑት ለሕይዎታቸው እንደማይሳሱ ሁሉ፣ ለራሳቸውም ሕይዎት የሳሱ አልነበሩም። « አያሌ ጀግኖችን በእቅፉ ሥር ሲያውል የነበረ ጀግና በሌሎች እቅፍ ሥር አይውልም» በማለት ራሳቸው ለማጥፋት የበቁት በቆራጥነታቸው ነው።

- **ሐቀኝነት፡-** ቴዎድሮስ ሐቀኛ ናቸው። ዋሾ ሰው አይወዱም፣ ዕውነት ተናጋሪና ለዕውነት ሟች ናቸው። እርሳቸው የማይፈልጉትን ነገር በሌሎች ላይ ማድረግን አይሹም ነበር። ገድለዋል፣ ራሳቸውንም ገደሉ። ፍርድ ዕኩል ነው። የገደሉት ለዓላማቸው ነው። ራሳቸውንም የገደሉት ለዓላማቸው ጽናትና ትክክለኛነት ነው።
- **ዕኩልነት፡-** ቴዎድሮስ በሰዎች ዕኩልነት ያምናሉ፤ ለሥራ ከፍተኛ ከበሬታ የሰጡ ናቸው። ባርነትን ማስቀረታቸው፣ የዕደጠበብ ሙያተኞችን ማክበራቸው ለዕኩልነት ያላቸውን አቋም በግልጽ ያሳያል።
- **ታታሪነት፡-** ቴዎድሮስ እጅግ ታታሪ ሠራተኛ ነበሩ፣ ያርሱ፣ ይጎለጉሉ፣ ይነግዱ ነበር። ለሠራተኛ ሰው ክብርና አድናቆት ይሰጡ ነበር፤
- **አንድነት፡-** ቴዎድሮስ የሕዝብና የአገርን አንድነት አጥብቀው የሚወዱ ናቸው። ለዚህም በሕይዎት ዘመናቸው አንድም ቀን ትጥቃቸውን ሳይፈቱ ከቦታ ቦታ ተንከራተው የኢትዮጵያን ዳግም አንድነት ትንሣዔ አብስረው ያለፉት። የአገሪቱና የሕዝቡ አንድነት በፖለቲካ፣ በአስተዳደርና በሃይማኖት መለያየት እንዳይኖር የሁሉም አንድነት መሠረት ጥለው ያለፉ መሪ ናቸው።
- **ጽናት፡-** ጽናት የቴዎድሮስ መለያ ነው። ላሰቡት፣ ላቀዱት ነገር ሳያወላውሉ ወደፊት መግፋት፣የጽናታቸው መሠረትም የዓላማቸው ትክክለኛነት ከቆራጥነታቸው ጋር መቀናጀት ነው። ራሳቸውን በራሳቸው የማጥፋታቸው ሚስጢር የዓላማ ጽናታቸውን ያሳያል።
- **ራስን ለሕዝብና ለአገር ጥቅም ማስቀደም፡-** ቴዎድሮስ ለአገራቸውና ለወገናቸው ደኅንነትና ብልጽግና ሲሉ የግል ድሎትንና ዝናን የማይሹ፣ ለራቸው ከሠራዊታቸው የተለየ ጥቅምና መብት የሌላቸው ሠርተው የሚያሠሩ ነበሩ።
- **ጥበብን ናፋቂ ፡-** ቴዎድሮስ ጥበብን አፍቃሪ ነበሩ፤ ለአዲስ ሀሳብና አስተያየት ኅሊናቸው ክፍት ነበር፣ የፈጠራ ሥራ ያበረታቱ ነበር፤
- **ለአገርና ለትውልድ ክብር መቆም፡-** ቴዎድሮስ ለአገርና ለወገን ክብር ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ መሪ ናቸው። አንድነትን በትግላቸው አረጋግጠዋል። ለአገራቸውና ለትውልዱ ክብር ሲሉም ራሳቸውን በራሳቸው አጥፍተዋል።
- **ሃይማኖተ ጽኑነት፡-** የተቀበሉትን የተዋሕዶ ሃይማኖት ቀናና ጽግማ አክባሪ ነበሩ። ሁሉም ክርስቲያን ባንድ ወንድ ወይም ሴት እንዲወሰን ለሚለው ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ ቁባቶቻቸውን ሁሉ አሰናብተው ባንዲ ሴት ጸንተው ኖረዋል። ሃይማኖቱ እስካሁን ጸንቶ ያለውን የአገልግሎት ሥርዓት ደንግገዋል።

**11.5 የታሪክ ተመራማሪዎች ስለቴዎድሮስ ምን ይላሉ?**

1. **ፕሮፌሰር ዶናልድ ክራሚ፡-** ቴዎድሮስ « የዘመናዊ ሥልጣኔ ሐሳብ የገባው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር።» (ባሕሩ ዘውዴ፣ 2003፣ 31)
2. **ቫልድማየር፡- ቴዎድሮስ፣** « ኃይልና ታላቅነት ሳያንሰው፣ የምቾትና የቅምጥል ኑሮ የማያታልለው እንዲህ ያለ ንጉሥ ከቶ የት ይገኛል? የሁላችንም እምነት እግዚአብሔር ኃይሉን የለገሠው የሕዝቡንም ቁሣዊና መንፈሣዊ ደኅንነት ለማረጋገጥ የታጬ መሣሪያ መሆኑ ነው።» ( ባሕሩ ዘውዴ፣ 2003፣ 41)
3. **ቴዎድሮስ ለአገራቸው ዕውቀት መስፋፋት የነበራቸውን ጉጉት ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ በማለት ነበር የገለጹት።**
   (1) ጥር 1858፣« የኢትዮጵያ ሰዎች ድንቁርነታችን ዕውርነታችን ሳይሰሙት አይቀርም።»
   (2) መጋቢት 1858፣ « አሁንም እኔ የምፈልገው ዕውር ነኝና ዓይኔ እንዲበራ ጥበብ ነው።»
   (3) ሚያዝያ 1858፣ « የኢትዮጵያ ሰዎች ዕውር ነኝ፤ ዓይናችንን ያበሩልን ፤ እግዚአብሔር በሰማይ ያብራለዎ!»
   (4) ሚያዝያ 1859፣ «ከብት አለመፈለጌ ክብር ሆኜ አይደለም፤ ዕውር አህያ ነኝና ለጥበብ ዓይኔን ትከፍቱልኝ ብየ ነው እንጂ፣ በእግዚአብሔር ኃይል፤» (ባሕሩ ዘውዴ፣ 2003፣ 39-40)

4 **ተክለጻድቅ መኩሪያ፡-** ቴዎድሮስ፣« ሞትን የናቁ፣ ድሎትን የራቁ» ናቸው ሲሉ ይገልጿቸዋል።

ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደግ!

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያዊነት ክብርና ኩራት!



**ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ (አባ ታጠቅ)**

**(ከ፲፰፻፲፪ - ሚያዝያ ፮ ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም.)**

**ኢትዮጵያ በጀግኖች እና ቆራጥ ልጆቿ መስዋዕትነት ለዘለዓለም ፀንታ ትኖራለች!**

## ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት